# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

## መግቢያ

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
የመ.ሣ.ቍ. 1252
ስልክ 518233
አዲስ አበባ

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መግቢያ - የ60 ቀን ጥናት

መጽሐፍ ቅዱስ ታላቅና አስፈላጊ መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በ1500 ዓመታት ውስጥ ወደ 40 በሚደርሱ ሰዎች በተለይ በሁለት ቋንቋዎች ማለትም ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ፥ አዲስ ኪዳንም በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን፥ ከአሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ የዮሐንስ ራእይ ድረስ ያሉት መጻሕፍት፥ ዓላማቸውና ግባቸው አንድ ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔር ሕዝቡን በኢየሱስ ክርስቶስ በሚገኘው እምነት በማዳን እንዲከበር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ወይም በከፊል ከ2000 ቋንቋዎች በላይ ተተርጉሞ ይገኛል። በአማርኛ በ1953 ዓ.ም. በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የታተመ አለ፥ ደግሞ «ቀለል ባለ አማርኛ» የተተረጎመ በ1980 ዓ.ም. ታትሞ ይገኛል። በሌሎችም በርካታ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

ከዚህ ታላቅ መጽሐፍ መንፈሳዊ በረከትንና እውቀትን ለማስገኘት ይቻል ዘንድ፥በተለይም እግዚአብሔር ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ እስከ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና እስከ ሐዋርያት ዘመን ድረስ በዓለምና በሕዝቡ ታሪክ ዋና እንቅስቃሴዎች ራሱን እንዴት እንደገለጠና የክርስቲያን እምነት ዋና ዋና ትምህርት ምን እንደሆን በማጠቃለል ይህ የጥናት መጽሐፍ ተዘጋጅቶአል።


ገጽ

ክፍል 1 የደኅንነት ጎህ - - 4

ክፍል 2 የአዳኙ መምጣት - - 25


ክፍል 3 የድል ብሥራት - - 46

የጥናት መልሶች - - 67

ካርታዎች - - 76

መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ - - 78

በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር - - 78

---

በዚህ የጥናት መጽሐፍ በአግባቡ ለመገልገል የሚከተሉትን ጉዳዮች ማወቅ ያስፈልጋል ፦

1. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች</u>፤ የተጠቀሱትን ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ያስፈልጋል።

2. <u>ማስታወሻዎች</u>፤ የ1953 ዕትምን ትርጉም ያመለክታሉ፥ ሆኖም አስፈላጊ ሲሆን የ1980ን ትርጉም ጭምር ይጠቅሳሉ።

3. <u>የጥያቄዎች መልስ</u>፤ በተሰጠው አንቀጽ መሠረት እንጂ በፊት ከነበረው ከአንባቢው ጥናትና እውቀት አኳያ አይሁን። በየጥናቱ መልሶችን ከመጻፍህ በፊት ማስታወሻዎችን አንብብና ከጻፍካቸው በኋላ በመጽሐፉ መጨረሻ የሚገኙትን መሪ መልሶች ከመልሶችህ ጋር አነጻጽር።


# ክፍል 1 የደኅንነት ጎህ



«እውነትን ታውቃላችሁ፤ እውነት ነጻ ያወጣችኋል።»


| | | | ገጽ |
|---|---|---|---|
| **በመጀመሪያ** | | | |
| 1. | ኦሪት ዘፍጥረት 1 | እግዚአብሔርና ፍጥረቱ | 5 |
| 2. | ኦሪት ዘፍጥረት 2 | ሰው በዓለም ላይ | 6 |
| 3. | ኦሪት ዘፍጥረት 3 | ውድቀትና ውጤቱ | 7 |
| **አባቶች** | | | |
| 4. | ኦሪት ዘፍጥረት 12፥1-8፤ 15፥1-7፤ 17፥1-11 | የቃል ኪዳን መመሥረት | 8 |
| 5. | ኦሪት ዘፍጥረት 28፥10-22፤ 32፥22-32 | አዲስ ስም | 9 |
| **ሕዝብ** | | | |
| 6. | ኦሪት ዘጸአት 3፥1-12 | የነፃ አውጭ ጥሪ | 10 |
| 7. | ኦሪት ዘጸአት 12፥1-14:24-33 | የማይረሳ ሌሊት | 11 |
| 8. | ኦሪት ዘጸአት 20፥1-21 | የእግዚአብሔር ሕግ | 12 |
| 9. | ኦሪት ዘጸአት 40፥17-38 | የማደሪያው ድንኳን | 13 |
| **ሀገር** | | | |
| 10. | ኢያሱ 1፥1-11 | ወደ ተስፋው ሀገር መግባት | 14 |
| **ነገሥታት** | | | |
| 11. | 1 ሳሙኤል 16፥1-13 | የንጉሥ መመረጥ | 15 |
| 12. | 2 ሳሙኤል 7 | ለንጉሥ የተሰጠ የተስፋ ቃል | 16 |
| 13. | መዝሙር 50(51) | የንስሐ ጸሎት | 17 |
| 14. | 1 ነገሥት 8፥1-21 | የእግዚአብሔር ቤት | 18 |
| **መከፋፈል** | | | |
| 15. | 1 ነገሥት 18፥17-40 | የባዕድ አምልኮ ከንቱነት | 19 |
| 16. | ኢሳይያስ 52፥13-53፥12 | የሚላክ አገልጋይ | 20 |
| 17. | 2 ነገሥት 22፥1-23፥7፤ 23፥24-26 | የቃል ኪዳን መታደስ | 21 |
| **ምርኮ** | | | |
| 18. | 2 ዜና መዋዕል 36፥5-23 | ቃል ኪዳንን መሻርና ውጤቱ | 22 |
| 19. | ሕዝቅኤል 36፥16-38 | የሕዝብ መመለስ | 23 |
| **ከምርኮ መመለስ** | | | |
| 20. | ዕዝራ 3 | አዲሱ ቤተ መቅደስ | 24 |

## 1. እግዚአብሔርና ፍጥረቱ



መግቢያ፤ «ኦሪት» ማለት ሕግ ማለት ነው፤ «ኦሪት ዘፍጥረት» ከአምስቱ የኦሪት መጻሕፍት የመጀመሪያው ነው። ኦሪት ዘፍጥረት ከዓለም መፈጠር ጀምሮ እስከ ያዕቆብና ዮሴፍ ወደ ግብጽ መውረድ ድረስ ይተርካል። እንግዲህ መጽሐፉ በመጀመሪያ የተዘጋጀው እግዚአብሔር የዓለም ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን፥ ከጉስቍልናቸውና ከግብጽ ባርነታቸው ነፃ ያወጣቸው የሕዝብነታቸውም መሥራች መሆኑን ለሚያውቁ ነው።

ጸሎት፤ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ከማንበብህ በፊት ምሥጢሩን ለመረዳት እንድትበቃና በቃሉም መሠረት ለመመላለስ እንድትችል እግዚአብሔርን ለምን።

ንባብ፤ ምዕራፉን አንድ ጊዜ በጥንቃቄ ዝግ ብለህ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. በእያንዳንዱ ቀን የተፈጠሩትን ፍጥረታት ዘርዝር።

1. ____________________
2. ____________________
3. ____________________
4. ____________________
5. ____________________
6. ____________________

ከዚህ ቅደም ተከተል ስለ እግዚአብሔር ሥራ ምን ታስተውላለህ?

____________________

2. ከዚህ ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔር፥ ሀ) ህላዌ (መኖር)፥ ለ) ኃያልነት፥ ሐ) እንዲሁም ዓለምን ለምን እንደፈጠረ ምን ትረዳለህ?

____________________

____________________

____________________

3. በቍጥር 26-31 መሠረት በምድር ላይ ስለ ሰው፥ ሀ) ተፈጥሮአዊ ባሕርይ፥ ለ) ሥልጣንና ሥራ ምን ታስተውላለህ?

____________________

____________________

____________________

4. የዚህ ምዕራፍ ጥናት፥ ሀ) ስለ ፍጥረታት ያለህ አመለካከት፥ ለ) ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት ላይ ምን ለውጥ ያመጣል?

____________________

____________________

ምስጋና፤ የዓለምንና የራስህን ፈጣሪ በልብህ አመስግን።


ማስታወሻ፤

ቍ.1 በመጀመሪያ እግዚአብሔር ፈጠረ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መኖር ያውጃል እንጂ አይከራከርበትም። ሮሜ 1፥20-26። እንዲሁም የሚታየው ሁሉ በማይታየው በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠረ ይገልጣል። ዕብራውያን 11፥3።

ቍ.5 ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንድ ቀን፤ ብዙዎቹ ሊቃውንት «ቀን» ሲል መደበኛውን 24 ሰዓት ያመለክታል ሲሉ አንዳንድ ሊቃውንት «ዘመን ነው» ብለው ይተረጕማሉ። የቀሩት ደግሞ የታሪክ ማስረጃን ሳይክዱ፥ የደራሲው ዓላማ አንባቢዎች በየቀኑ የተፈጠሩትን ፍጥረታት እያስተዋሉ እግዚአብሔርን በማመስገን እንዲኖሩና በሰባተኛው ቀን ዐርፈው እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ መሆኑን በማመናቸው በጽሑፉ አቀራረብ ይታያል ይላሉ።

ቍ.26 በመልካችን እንደ ምሳሌአችን፤ ይህ ሐረግ የሰውን መንፈሳዊና ነፍሳዊ ባሕርይ እንጂ ሥጋዊውን ተፈጥሮ አያመለክትም። ዮሐንስ 4፥24። ሰው በፍጥረት ላይ ያለው ሥልጣን እውን ሊሆን የበቃው በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠሩ ነውና።

## 2. ሰው በዓለም ላይ



**መግቢያ፤** ይህ ምዕራፍ የምዕራፍ አንድ ማሟያ ነው። ምዕራፍ አንድ እግዚአብሔር ዓለምን እንዴትና ለምን እንደፈጠረ ሲገልጥ ምዕራፍ ሁለት አንዳንድ ዝርዝሮችን እያብራራ ሰው ምን ያህል በረከት እንደተቀበለና በእግዚአብሔር ዓለም መኖር እንዴት እንደሚገባው ያስረዳል።

**ራስን ማዘጋጀት፤** ተፈጥሮን በማስተዋል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በዚህ ዓለም ለመመላለስ እንድትችል የፍጥረታትን ባለቤት ለምን።

**ንባብ፤** ምዕራፉን ሁለት ጊዜ አንብብ።

**ጥያቄ፤**

1. በዚህ ምዕራፍ መሠረት እግዚአብሔር ለሰው ያዘጋጃቸውን መልካም ነገሮች ዘርዝር (ቍ.1-3፤8-25)።

___

___

___

2. ሰው ሰባተኛውን ቀን እንዴት ማክበር ይገባዋል (ቍ.1-3)?

___

___

3. ቍጥር ሰባት የምዕራፍ አንድ ቍ.27ን ትምህርት ስለ ሰው ሁኔታ እንዴት ያብራራል?

___

___

4. በገነት መካከል የሚገኙት ሁለት ዛፎች የሚያመለክቱት ምንድን ነው (ቍ.9፤16፤17)?

___

___

5. ከቍ.20-25 ስለ ዘመኑ ጋብቻ የምታገኛቸው መሠረተ ሀሳቦች ምን ምን ናቸው?

___

___

___

___

___

**ምስጋና፤** እግዚአብሔር ያደረገልህን በጎ ነገር ሁሉ ልብ በማድረግ አመስግነው።

**ማስታወሻ፤**

**ቍ.3 ቀደሰው፤** ሰው በእግዚአብሔር መልክ ስለ ተፈጠረ አርአያውን መከተል ይገባዋል። ዘጸአት 20፥8-11።

**ቍ.9** መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀው ዛፍ የቆመው ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማክበር እንዳለበት ለማሳየት እንጂ ለፈተና አይደለም። የትኩሳት መለኪያ የሰውን ሁኔታ እንደሚያሳይ ሁሉ፥ ይህም ዛፍ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነት ምን ዓይነት መልክ እንደነበረው ያሳያል።

**ቍ.20 አዳም...ስም አወጣላቸው፤** በዚህ ተግባሩም እግዚአብሔር የሰጠውን ሥልጣን አረጋግጧል። ዘፍጥረት 1፥28።

**ቍ.20-25** የምዕራፍ 1፥27ን ሀሳብ ያብራራል፥ ወንድንና ሴትን አስመልክቶም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይገልጣሉ። ማቴዎስ 19፥4-6።

## 3. ውድቀትና ውጤቱ



<u>መግቢያ</u>፤ ይህን ምዕራፍ ካልተረዳህ ጠቅላላውን መጽሐፍ ቅዱስና የዓለምን ሁኔታ ማስተዋል አትችልም። በዚህ ምዕራፍ የዓለምን ሥነ ምግባርና መንፈሳዊ ሁኔታ በሰው ጉልበት ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት ብቻ አይበቃም።

<u>ጸሎት</u>፤ ይህን ምዕራፍ በማንበብ የሰውን አፈጣጠር ለማስተዋል እንድትችል እግዚአብሔርን ለምን።

<u>ንባብ</u>፤ ምዕራፉን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ሰይጣን ሴቲቱን ያታለለበትን (የፈተነበትን) ቅደም ተከተል ዘርዝር (ቍ.1-6)።

2. ሰው በኃጢአት እንደወደቀ ምን ሆነ (ቍ.7-13፡23)?

3. ውድቀት (ቍ.14-19)፥ ሀ) በሰውና በሰይጣን መካከል፥ ለ) በሴት ላይ፥ ሐ) በወንድ ላይ የሚያስከትለው የዘወትር ውጤት ምንድን ነው?

4. ሀ)በቍ.15 አዳም ለወደፊት ስለሚፈጸመው ዓቢይ ጉዳይ ምን የተረዳ ይመስልሃል? ለ) ይህ ግንዛቤው እንዴት ተገለጠ (ቍ.20)?

5. ምንም እንኳ ሰው በኃጢአት ቢወድቅ፥ እግዚአብሔር ሰውን ዘወትር ለመባረክ እቅድ እንዳለው በምን ሁኔታ ተገለጠ (ቍ.15፡21-24)?

6. የአዳምንና የሔዋንን ውድቀት ከሕይወትህ ጋር እንዴት ታዛምደዋለህ?

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.22 «ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ»</u>፤ ምጸት ይመስላል።

<u>ቍ.24 የሕይወት ዛፍ</u>፤ ተጠበቀ እንጂ አልተቈረጠም።

<u>ኪሩቤል</u>፤ በመሠዊያው ቦታ የሚገኙ መላእክት ወይም ምስሎች። ዘጸአት 25፥22።

<u>እንደ እሳት ...ሰይፍ</u>፤ ለእግዚአብሔር መኖር መከሠቻ በመሆን ቆመዋል።

## 4. የቃል ኪዳን መመሥረት

ኦሪት ዘፍጥረት 12፥1-8፤ 15፥1-7፤ 17፥1-11



መግቢያ፤ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከዔደን ገነት አስወጣ። ከውድቀታቸው የተነሣም የበኵር ልጃቸው ቃየን (ቃየል) ታናሽ ወንድሙን አቤልን ገደለው (ም.4)። ዘራቸው በየትውልዱ ከእግዚአብሔር እየራቀ በመሔዱ በመጨረሻ እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ በጥፋት ውኃ ቀጣቸው፤ ነገር ግን ኖኅንና ቤተ ሰቡን በመርከብ አዳናቸው (ም.6-8)። ሰዎች ከዚህ ሁሉ ጥፋት ምንም ሳይማሩ ከተማ ከትመው በትዕቢታቸው ግንብ አበጁ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ በተናቸው (ም.11፥1-9)።

እግዚአብሔር ከክርስቶስ ልደት በፊት 2000 ዓመታት ገደማ ለሕዝቡ ታላቅ አባት የሚሆነውንና በእርሱ አማካይነትም ዓለሙን ሁሉ የሚያድንበትን አብርሃምን መረጠው።

ጸሎት፤ በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል ያለውን ቃል ኪዳን እንድታስተውል እግዚአብሔርን ለምን።

ንባብ፤ የተሰጡትን ሦስት አንቀጾች በጥንቃቄ አንድ ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ሀ) አብራም አገሩንና ቤተ ሰቡን ለመተው ሲታዘዝ ምን ተስፋ ተሰጠው (12፥1-3)? ለ) ወደ ከነዓንስ ሲገባ ምን ተስፋ ተሰጠው (12፥7)? ሐ) አብራም ወዲያው ምን አደረገ (12፥7)?

2. ሀ) አብራም በተለይ የተቸገረበት ምን ነበር (15፥2)? ለ) የአብራም የጽድቅ መሠረት ምን ነበር (15፥6)?

3. ሀ) በቃል ኪዳኑ ውስጥ ለአብርሃም ምን ተስፋ ተሰጠው (17፥4-8)? ለ) ቃል ኪዳኑን ለመጠበቅ ምን ማድረግ ነበረበት (17፥9-11)?

4. የእግዚአብሔርን ድምጽ ስትሰማ ምን ታደርጋለህ?

ማስታወሻ፤

12፥1 አገርህ፤ የከለዳውያን ዑር። ዘፍጥረት 11፥31፤ የሐዋርያት ሥራ 7፥2:3።

12፥5 ከነዓን፤ ከብዙ ዓመታት በኋላ የእስራኤል ሕዝብ የወረሰው አገር።

15፥6 ከክርስቶስ በፊት እንደ አብርሃም የተመላለሱት ሁሉ ልክ እንደ ዛሬው በእምነት ይጸድቁ ነበር። ሮሜ 4፥3-5:11፤ ገላትያ 3፥6።

17፥5 አብራም፤ ማለት «ታላቅ አባት» ሲሆን አብርሃም ማለት «የብዙ ሕዝብ አባት» ማለት ነው።

17፥10 ወንድ ሁሉ ይገረዝ፤ ይህ ምልክት የቃል ኪዳን ተስፋ ሁሉ የሚፈጸመው በአብርሃም ዘር መሆኑንና ይህ ዘር ለእግዚአብሔር የተለየ እንደሚሆን ያሳያል። ዘፍጥረት 3፥15፤ ገላትያ 3፥16:29።

## 5. <u>አዲስ ስም</u>

<u>ኦሪት ዘፍጥረት 28፥10-22፤32፥22-32</u>



<u>መግቢያ</u>፤ ቃል ኪዳኑን ከተቀበለ በኋላ አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፥ ይስሐቅ ያዕቆብን፥ ያዕቆብም አሥራ ሁለቱን የአባቶችን አለቆች ወለደ። እነዚህ የእስራኤል ሕዝብ አባቶች ሁሉበድንኳን እየኖሩ መንጐቻቸውን በከነዓን አገር ያሰማሩ ነበር። ያዕቆብ አባቱንና መንትያ ወንድሙን ዔሳውን ካታለለ በኋላ ከቤቱ መሸሽ ግድ ሆነበትና በጕዞ ላይ ሳለ እግዚአብሔር ተገለጠለት። ከዚያም ለሃያ ዓመታት ከከነዓን ውጭ ከቆየ በኋላ፥ ወደ አገሩ ሲመለስ እንደገና እግዚአብሔር ተገናኝቶት አዲስ ስም ሰጠው።

<u>ጸሎት</u>፤ እግዚአብሔር የተከታዮቹን የሕይወት ታሪክ ለማንበብ ስላደለህ አመስግነው።

<u>ንባብ</u>፤ ሁለቱን አንቀጾች አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ሀ) ያዕቆብ ሕልም ሲያይ በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ ነበር (28፥10-12)? ለ) እግዚአብሔር ለያዕቆብ ራሱን እንዴት ገለጠ (ቍ.12-13)? ሐ) ለያዕቆብስ ምን ተስፋ ተሰጠው (ቍ.14-15)? መ) ከእንቅልፉ ሲነቃ ያዕቆብ ምን አደረገ (ቍ.15-22)?

2. ሀ) የያዕቆብ ሁኔታ በያቦቅ ወንዝ እንዴት ነበር (32፥22-24)? ለ) በዚያ ሌሊት ምን ሆነለት (ቍ.24-29)? ሐ) ለያዕቆብ የተሰጠው አዲሱ ስም ምንን ያመለክታል (ቍ.28)?

3. የራስህ «ቤቴል» ና የራስህ «አዲስ ስም» አለህን? ትግልህ እንዴት ነው?

<u>ምስጋና</u>፤ እግዚአብሔር በሕይወትህ ያደረገውን ድንቅ ሥራ በማሰብ አመስግነው።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>28፥13-15</u>፤ ለያዕቆብና ለአብርሃም (በዘፍጥረት 12፥3:7፤17፥4)፥ ለይስሐቅም (በዘፍጥረት 26፥2-5) የተሰጡት የተስፋ ቃላት ይመሳሰላሉ። እያንዳንዱ ትውልድም ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘትና ለግሉ የተስፋ ቃላትን መቀበል ያስፈልገዋል።

<u>28፥19</u>፤ «ቤቴል» ወይም «ቤትኤል» ማለት የእግዚአብሔር (ኤል) ቤት ማለት ነው።

<u>32፥24 አንድ ሰው . . . ይታገለው ነበር</u>፤ በዚህ እግዚአብሔር በያዕቆብ ጠባይና ተግባር (ለምሳሌ :- አባቱንና ወንድሙን በማታለሉ) አለመደሰቱን ገለጠ። ያዕቆብ ይህንኑ አውቆ ምንም እንኳን እግሩን ቢደነዝዘው እንዲባረክ ያለማቋረጥ ትግሉን ቀጠለ (ቍ.26)።

<u>32፥27፤ እስራኤል</u>፤ አንዳንዶች ስሙ «እግዚአብሔር (ኤል) ይታገላል» ሌሎች ደግሞ «ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ» ብለው ይተረጕሙታል። ያም ሆነ ይህ አዲሱ ስሙ በሕይወቱ ትልቅ ለውጥን አምጥቷል፤ የእግዚአብሔርን አድራጎትና የያዕቆብን የትግል መልስም ያመለክታል።

## 6. የነፃ አውጭ ጥሪ

**ኦሪት ዘጸአት 3፥1-12**



መግቢያ፤ ያዕቆብ አዲሱን ስም ከተቀበለ በኋላ በረሀብ ምክንያት ከቤተ ሰቡ ጋር ወደ ግብጽ መሰደድ ግዴታ ሆነበት። ከስደቱ በፊት ከአሥራ ሁለቱ ልጆች አንዱ ዮሴፍ በወንድሞቹ ተሸጦ በግብጽ ሀገር ባርያ ሆነ። እግዚአብሔር ግን ከዮሴፍ ጋር ነበርና የግብጽ ንጉሥ የፈርዖን ጠቅላይ ሚኒስተር እስኪሆን ድረስ ባረከው። በእግዚአብሔር ጸጋ ዮሴፍ በወንድሞቹ ላይ ቂም አልያዘምና አባቱና ወንድሞቹ ሲመጡ ማረፊያ ቦታን አዘጋጀላቸው (ዘፍጥረት 37-50)።

ከዘመናት በኋላ ግብጻውያን እስኪፈሩአቸውና እስኪጨክኑባቸው ድረስ የእስራኤላውያን ዘር እየበዛ ሄደ (ዘጸአት 1)። እግዚአብሔር ሥቃያቸውን አይቶ ከመከራ ነፃ የሚያወጣቸውን ሰው ሙሴን አዘጋጀ። ሙሴ ከአሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች አንዱ ከሆነው ከሌዊ ነገድ ቢወለድም በፈርዖን ቤተ መንግሥት አርባ ዓመት ኖረ። ሆኖም ከዕለታት አንድ ቀን ከወገኖቹ አንዱን ለመርዳት በወሰደው እርምጃ የተነሣ ከግብጽ መሸሽ ግድ ሆኖበት፥ በምድረ በዳ በጎችን እየጠበቀ አርባ ዓመታትን አሳለፈ (ዘጸአት 2)።

ጸልይና አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. የሙሴን እድገትና የሕይወቱን ውጣ ውረድ ስትመለከተው እግዚአብሔር ሳይገለጥለት እረኛ ሆኖ በመቈየቱ የተደሰተ ይመስልሃልን?
2. ሀ) እግዚአብሔር ራሱን ለሙሴ እንዴት ገለጠ? ለ) ሙሴ ምን ተሰማው? ሐ) አንተስ በእግዚአብሔር ፊት ስትገኝ ምን ይሰማሃል?

3. እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው መልእክት፥ ሀ) ስለ እግዚአብሔር፥ ለ) ስለ ሙሴ (ቍ.10-12) ምን ይገልጣል?

4. ለዚህ ኀላፊነት የሙሴ ችሎታ፥ ዝግጅትና ብቃት እንዴት ነበር?

5. እግዚአብሔር የሰጠህ ሙያ ወይም ኀላፊነት ምንድን ነው? ለዚህ እንዴት አበቃህ?

ማስገንዘቢያ፤ ስለ እግዚአብሔር ቸርነትና ስለ ሰጠህ ኀላፊነት ወይም ለወደፊት ስለሚሰጥህ ተግባር አሰላስል።

ማስታወሻ፤


ቍ.1 ዮቶር፤ ከአብርሃም ልጅ ከምድያም ዘር። ዘፍጥረት 25፥1-2።

ቍ.2 የእግዚአብሔር መልአክ፤ እግዚአብሔር በሰው መልክ ሲገለጥ። ዘፍጥረት 18፥1-2።

ቍ.6 በጥናት 5 ያለውን የዘፍጥረት 28፥13-15 ማስታወሻ ተመልከት።

## 7. የማይረሳ ሌሊት

**ኦሪት ዘጸአት 12፥1-14፡24-33፡43-44**



መግቢያ፤ ሙሴ ከወንድሙ ከአሮን ጋር ወደ ግብጽ ወረደ፤ ነገር ግን ቀደም ሲል እግዚአብሔር እንዳስጠነቀቃቸው (ዘጸአት 3፥19)፥ፈርዖን የእስራኤልን ሕዝብ ለመልቀቅ ፈቃደኛ አልነበረም። አገሩ በከፉና በተለያየ መቅሠፍት ቢመታም እስከ አሥረኛውና የመጨረሻው መቅሠፍት ድረስ ፈርዖን ልቡን አደነደነ።

ጸሎት፤ የእስራኤልን ሕዝብ መከራና እግዚአብሔር እንዴት እንዳዳናቸው እንድታስተውል ጠይቅ።

ንባብ፤ አንቀጾቹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. እስራኤላውያን፥ ሀ) በጠቦት ደም (ቊ.3-7)፥ ለ) በጠቦት ሥጋ (ቊ.8-10) ምን ለማድረግ ታዘዙ?

2. ይህ ደም ለምን ይበጃል (ቊ.12፡13)?

3. ፈርዖንና ግብጻውያን የዚህን ሌሊት ድርጊት አይተው ምን አደረጉ (ቊ.29-33)?

4. በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ለፋሲካ በዓል ምን ስፍራ ተሰጠ (ቊ.14፥24-27)?

5. በአንተ አስተያየት የክርስቲያን ዋና በዓል ለምን ፋሲካ ተባለ? 1ቆሮንቶስ 5፥7 አንብብ።

6. ኢየሱስ ክርስቶስ የአንተ «ፋሲካ» የሆነው እንዴት ነው?

ምስጋና፤ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት ከፍርድ ነፃ ስላወጣህ አመስግነው።

ማስታወሻ፤


ቊ.2 ይህ ወር የወሮች መጀመሪያ ይሁናችሁ፤ እንደ አይሁድ አቆጣጠር የመጀመሪያ ወራቸው ከእኛ ሚያዝያና ግንቦት ጋር ይገናኛል። እነርሱ አሁንም የፋሲካን በዓል በዚህ ወር በ14ኛው ቀን ያከብራሉ።

ቊ.43 « ፋሲካ» ማለት « አለፈ» ወይም « አይቶ አለፈ» ማለት ነው።

## 8. የእግዚአብሔር ሕግ

**ኦሪት ዘጸአት 20፥1-27**

<u>መግቢያ፤</u> «ዘጸአት» ማለት የመውጣት ማለት ነው። በመሆኑም መጽሐፉ የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ የባርነት ኑሮ እንዴት ነፃ እንደወጡና፥ በምድረ በዳ እግዚአብሔር እንዴት እንደመራቸው፥እንደ ተገናኛቸውና ሕግንም እንደሰጣቸው ይተርካል።



ከግብጽ ሲወጡ በተአምር ቀይ ባሕርን ተሻገሩ (ም.15)፥ ዕለት ዕለትም ከሰማይ መና የተባለውን ምግብ እየተቀበሉ (ም.16)፥ መንገዳቸውን ቀጥለው በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ሲና ተራራ ደረሱ፤ በዚሁም ስፍራ ከነጐድጓድና ከመብረቅ፥ ከከባድም ደመና፥ እንዲሁም እጅግ ከበረታ ከቀንደ መለከት ድምጽ መካከል በተራራው ላይ እግዚአብሔር ተናገራቸው (ዘጸአት 19፥16-19)።

<u>ጸሎት፤</u> «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው።» የሚለውን ጥቅስ በማሰላሰል ጸልይ። መዝሙረ ዳዊት 118(119)፥105።

<u>ንባብ፤</u> አንቀጹን አንድ ጊዜ በጥንቃቄ አንብብ።

<u>ጥያቄ፤</u>

1. ሀ) እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ምን አድርጎ ነበር (ቊ.2)? ለ) ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ የሚያበቃቸው ዋና ምክንያት ምንድን ነው (ቊ.2)? ሐ) ሌላስ ምን ምክንያት አለ (ቊ.5-7:11:12)?

---

---

---

2. በቊ.3-11 ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ታስተውላለህ?

---

---

---

3. የእግዚአብሔር ሕዝብ ማኅበራዊ ኑሮ ምን ዓይነት መሆን አለበት (ቊ.8-10:12-16)?

---

---

4. እነዚህ ትእዛዛት አፍአዊ አሽታን ብቻ ሳይሆን የልብ አሽታን እንደሚጠይቁ እንዴት መለየት ይቻላል (2:17)?

---

---

5. በእነዚህ ትእዛዛት መሠረት ከእግዚአብሔር ባሕርይና ከሕዝቡ አኗኗር የተነሣ፥ ሀ) በሕይወትህ፥ ለ) በቤተ ክርስቲያንህ፥ ሐ) በአገርህ ላይ ምን ለውጥ ያስፈልጋል?

---

---

---

<u>ጸሎት፤</u> እግዚአብሔርን እያከበርህ በንጹህ ልብ በዓለም ውስጥ እንደሚገባህ ለመኖር እንድትበቃ ጠይቅ።

<u>ማስታወሻ፤</u>

<u>ቊ.5 የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤</u> ሰው በኅብረት ለመኖር በመፈጠሩ እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ የአንድ ትውልድ ድርጊት በሚመጣው ትውልድ ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል።

<u>ቊ.8</u> በ2ኛው ጥናት የዘፍጥረት 2፥3 ማስታወሻ ተመልከት።

<u>ቊ.10</u> የእንስሳት መብት እንደተጠበቀ ማስተዋል ይገባናል።

<u>ቊ.12</u> በዘመናችን በመምህራን፥ በአሠሪዎችና በሥነ ሥርዓት አስከባሪዎች የሚፈጸመው ሥራ በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ በተለይ በወላጆች ይከናወን ነበር።

## 9. የማደሪያው ድንኳን

<u>መግቢያ</u>፤ በሲና ተራራ እግዚአብሔር «የማደሪያው ድንኳን» እንዲዘጋጅ ዕቅዱን ወይም ንድፉን ለሙሴ ሰጠ። እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ በዓመቱ ማደሪያው ተተከለ፤ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን እስከ ሠራበት ወቅት ድረስም ዋና የአምልኮ ማዕከል ሆነ።

<u>ጸሎት</u>፤ ለእግዚአብሔር አምልኮ የተወሰነና የተቀደሰ ስፍራ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ በዘወትር ኑሮህ እንድታስተውል ጌታን ለምን።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ በጥንቃቄ አንብብ።


<u>ጥያቄ</u>፤

1. «እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው» የሚለው ሐረግ በዚህ አንቀጽ ስንት ጊዜ ተደጋገመ? የሐረጉ መደጋገም ምንን ያመለክታል?

______________________________

2. በንድፉ ላይ የተመለከቱት ቍጥሮች የሚያመለክቱትን ቁም ነገር ዘርዝር።

1. (ቍ.17)
2. (ቍ.20)
3. (ቍ.21)
4. (ቍ.22)
5. (ቍ.24)
6. (ቍ.26)
7. (ቍ.28)
8. (ቍ.29)
9. (ቍ.30)
10. (ቍ.33)
11. (ቍ.33)




3. ሀ) ሁሉ በቅደም ተከተል ከተፈጸመ በኋላ ምን ሆነ (33-38)? ለ) ይህ ክንዋኔ የሚያመለክተው ምንን ነው?

______________________________

______________________________

______________________________

4. አንተ በምትሳተፍበት አምልኮ የእግዚአብሔር ሥርዓት እንደ ቃሉ ሙሉ በሙሉ ይፈጸማልን? በዚህ ሥርዓት እግዚአብሔር ራሱ ይገኝበታልን?

______________________________

______________________________

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.20 ጽላቱ</u>፤ ዐሠርቱ ቃላት የተጻፈባቸው ሁለቱ ድንጋዮች ምስክሩም ይባላሉ (ቍ.21)።

<u>ታቦት</u>፤ በወርቅ የተለበጠ ከእንጨት የተሠራ የጽላቱ ማኖሪያ ሳጥን፤ እግዚአብሔር ከታቦቱ በላይ ሙሴን ያነጋግር ነበር (ዘጸአት 25፥10:11:22)።

<u>የስርየት መክደኛ</u>፤ ሰው ሕግን ስለሚተላለፍ ስርየት ያስፈልገዋልና በጋጢአት ስርየት ቀን የመሥዋዕት ደም በመክደኛው ላይ ይረጭ ነበር (ዘጸአት 25፥17፤ ዘሌዋውያን 16፥11-15)።

## 10. ወደ ተስፋው ሀገር መግባት





<u>መግቢያ</u>፤ ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ በምድረ በዳ ለአርባ ዓመት ከመራ በኋላ አረፈና በእርሱ ፈንታ ረዳቱ ኢያሱ መሪ ሆኖ ከነዓንን ለመውረስ በእግዚአብሔር ተመረጠ።

<u>ጸሎት</u>፤ ከኢያሱ የአርአያነት ሕይወት መረዳት የሚገባህን እንድታስተውል ጠይቅ።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ በጥንቃቄ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ኢያሱ አርባ ዓመት ሙሴን ካገለገለ በኋላ በታላቁ የሕዝብ መሪ ሞት ስሜቱ ምን ያህል የተነካ ይመስልሃል?

2. በዚህ አንቀጽ እግዚአብሔር ኢያሱን ስንት ጊዜ አዘዘው? ____________

3. ትእዛዛትን እንዲፈጽም ምን ተስፋ ተሰጠው (ቍ.3-6)?

4. የእግዚአብሔርን ፈቃድ በትክክል እንዲከተል ምን ትእዛዝ ተሰጠው (ቍ.7-9)?

5. ኢያሱ የእግዚአብሔርን አደራ ከተቀበለ በኋላ ምን አደረገ (ቍ.10-11)?

6. ለኢያሱ ከተሰጡት ትእዛዛት መካከል የትኞቹ ለሕይወትህ ይስማማሉ?

<u>ጸሎት</u>፤ እግዚአብሔር የሰጠህን ሥራና አገልግሎት በይበልጥ ለመፈጸም እንድትችል ምን ማድረግ እንደሚገባህ በማሰላሰል ጸልይ።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.1 ኢያሱ</u>፤ በአማሌቃውያን ላይ የተካሄደውን ጦርነት የመራ (ዘጸአት 17፥8-13)፥ ከሙሴ ጋር ጽላትን ለመቀበል ወደ ሲና ተራራ የወጣ (ዘጸአት 24፥13፤32፥17)፥ አገሩን ለመሰለል ከተመረጡት አሥራ ሁለቱ ሰላዮች አንዱ የነበረ (ዘኊልቍ ም.13-14)፥ በሙሴ ምትክ ኀላፊነቱን እንዲሸከም የተተካ (ዘዳ.31) የእስራኤል መሪ ነው። ይህንም ኀላፊነት ሲረከብም የሰባ ዓመት ሰው ነበር።

<u>ቍ.6 «ለአባቶቻችሁ ... የማልሁላቸውን ምድር»</u>፤ በጥናት 5 ያለውን የዘፍጥረት 28፥13-15 ማስታወሻ ተመልከት።

## 11. የንጉሥ መመረጥ

1 ሳሙኤል 16፥1-13



<u>መግቢያ</u>፤ ኢያሱ ከሞተ በኋላ ብዙውን ጊዜ የእስራኤል ሕዝቦች እግዚአብሔርን ማገልገል ትተው ሌሎች አማልክትን በመከተላቸው እግዚአብሔርን አስቆጡት፤ በዚህም ምክንያት በጠላቶቻቸው ተሸንፈው ከቀንበራቸው በታች ወደቁ። ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው ሲጮሁ ግን እንደእነ ጌዴዎንና ሶምሶን የመሳሰሉትን መሳፍንት እንዲታደጉአቸው አስነሣላቸው (መሳፍንት ም.6-8፤13-16)። በዚህ ዘመን ከአሕዛብ ወገን የሆነችው፥ የዳዊት ቅድመ አያት ሩት ወደ ቤተልሔም ለመኖር መጣች። ከመሳፍንቱ የመጨረሻው ሳሙኤል ነበረና ሕዝቡ ንጉሥ ሲፈልግ ሳኦልን ቀባ። ሳኦል በትረ መንግሥቱን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ቢጀምርም መጨረሻው ግን ሳያምር ቀረ። (1 ሳሙኤል ም. 8-15)።

<u>ጸሎት</u>፤ «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ እኖራለሁ» መዝሙረ ዳዊት የ118(119)፥11ን ጸሎት ጸልይ።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. በዚህ ጊዜ የሳሙኤል አስተያየት ስለ ሳኦል እንዴት ነበር (ቊ.1-4)?

2. የዳዊት ቤተ ሰቦች ስለ ታናሽ ልጃቸው ምን ዓይነት አስተያየት ነበራቸው (ቊ.5:11፤17፥28:29) ተመልከት?

3. ሀ) ዳዊት የተመረጠውና ወንድሞቹ የተተዉት በምን መሠረት ነው (ቊ.7)? ለ) ይህ አነሣሥ በአንተ አስተሳሰብ እንደምን ይታያል?

4. ዳዊት ከተቀባ በኋላ ምን ሆነለት?

5. እግዚአብሔር ላቀደልህ ሥራ በጎ ነገር የሚያመቻችልህ ስለ መሆኑ ይህ ታሪክ ምን ተስፋ ይሰጥሃል?


<u>ጸሎት</u>፤ ፈቃዱን ለሕይወትህ ገልጦ በመንፈሱ እንዲሞላህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቊ.1 እሴይ</u>፤ ሩት 4፥13-22ን ተመልከት።

## 12. ለንጉሥ የተሰጠ የተስፋ ቃል






<u>መግቢያ</u>፤ ዳዊት ለወደፊት የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ከተቀባ በኋላ ትንሽ ጊዜ ቆይቶ ግዙፍ የነበረውን ጐልያድን ገደለና ወደ ሳኦል አገልግሎት ገባ (1 ሳሙኤል 17)። ሳኦል ቂምና ቅናት ሲያድርበት ግን ዳዊት ሸሸ። ሳኦል ከሞተ በኋላ ዳዊት መጀመሪያ ለሰባት ዓመታት በራሱ ነገድ በይሁዳ ላይ፥ ከሰባት ዓመታት በኋላም በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ላይ ነገሠ። ጽዮን የተባለችውን የኢየሩሳሌምን አምባ ይዞ መናገሻ ከተማው ካደረጋት በኋላ በእስራኤል ዙሪያ የነበሩትን የእስራኤል ጠላቶች ሁሉ አሸነፈ።

<u>ጸሎት</u>፤ እግዚአብሔር በዳዊት በኩል ለመፈጸም ያቀደውን አሳብ እንድታስተውል ጌታን ለምን።

<u>ንባብ</u>፤ ምዕራፉን አንድ ጊዜ ዝግ ብለህ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ሀ) አሁንም ዳዊት ለማድረግ የሚፈልገው ምንድን ነው? ለ) ለምን (ቍ.1-2)?

2. እግዚአብሔር ለዳዊት ምን አድርጎለት ነበር (ቍ.8-9)?

3. እግዚአብሔር ስለ፥ ሀ) እስራኤል (ቍ.10-11)፥ ለ) ዳዊት ቤተ ሰብ (ቍ.11-16)፥ ሐ) ቤተ መቅደስ (ቍ.13) ምን የተስፋ ቃል ሰጠ?

4. ዳዊት ይህን ሁሉ ከሰማ በኋላ ከጸለያቸው ጸሎቶች ዋና ዋናዎቹ ምን ምን ነበሩ (ቍ.18-29)?

5. የቍ.16 የተስፋው ቃል ስለ መፈጸሙ ምን ይታይሃል?

<u>ምስጋና</u>፤ በተለይ ከዳዊት ሐረገ ትውልድ በተገኘው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ለዘመናት ባልታሰበው መንገድ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን እውን በማድረጉ አመስግነው።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.6 በድንኳንህ . . . እሄድ ነበር</u>፤ ታቦቱ እግዚአብሔር በምድር ላይ የመገለጡ ምልክት ነበር። እንዲሁም ቍ.2፤ ዘጸአት 25፥22 እና 9ኛውን ጥናት ተመልከት።

<u>ቍ.18 ንጉሥ ዳዊት ገባ በእግዚአብሔርም ፊት ተቀምጦ . . .</u>፤ ማለት ወደ ኢየሩሳሌም ባመጣው ታቦት ድንኳን ፊት ተቀመጠ ማለት ነው (2 ሳሙኤል 6)።

## 13. <u>የንስሐ ጸሎት</u>





<u>መግቢያ</u>፤ እግዚአብሔር «እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ» ብሎ መሰከረለት (የሐዋርያት ሥራ 13፥22፤ 1ሳሙኤል 13፥14)። ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዳዊት ሕይወት ከማናቸውም ሌላ ሰው ይልቅ በብዛት ይተርካል። ዳዊት ከብዙዎቹ መሪዎች ለየት ያለ የጦር ሰውና ንጉሥ (አስተዳዳሪ) ነበረ፥ ምናልባትም በዓለም ታሪክ የሚያክለው አይገኝም። ከዚህም ጋር መዝሙረኛና ባለቅኔ በመሆኑ በመዝሙራቱ የሰውን ሃሳብና ስሜት ሁሉ ይነካል። ዳዊት ግን ከመኰንኖቹ የአንዱን ሚስት ከደፈረ በኋላ ጥፋቱን ለመሸፈን ባልዋ እንዲገደል አደረገ፤ በጽኑ ፍትወተ ሥጋ ተቀስፎ ተይዞ ነበርና። በደሉን ሲረዳ ግን ወዲያውኑ ኃጢአቱን አውቆ ምህረትን ለመነ።

<u>ጸሎት</u>፤ የንስሐ መግባትንና የምስጋናን መንገድ እንድታስተውል ጌታን ለምን።

<u>ንባብ</u>፤ መዝሙሩን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ሀ) ዳዊት መጥፎ አድራጎቱ ሲሰማው ጥፋቱን በምን ዓይነት ቃላት ገለጸ (ቊ.1-5)? ለ) ምንም እንኳን ዳዊት በሰው ላይ መጥፎ ነገር ቢሠራ ዋነኛው ተበዳይ ማነው (ቊ.4)? ሐ) ኃጢአት የመጣው ከምን ጊዜ ጀምሮ ነው (ቊ.5)?

___

___

___

2. ከኃጢአት ይቅርታ ጋር ዳዊት የሚጠይቀው ምንድን ነው (ቊ.2:7-11)?

___

___

___

3. ዳዊት ይቅርታን ከተቀበለና የልብ መታደስን ካገኘ በኋላ ምን ሠራ (ቊ.12-15)?

___

___

___

4. እግዚአብሔር የሚፈልገው መሥዋዕት ምን ዓይነት ነው (ቊ.16-19)?

___

___

___

<u>የኃጢአት ይቅርታ</u>፤ መዝሙሩን ሁሉ አንብበህ ኃጢአትህን ሁሉ እየተናዘዝህ እግዚአብሔር ለአንተ ላደረገው ጸጋና ምሕረት ሁሉ አመስግነው።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቊ.5</u> ይህ ጥቅስ የሰው ተፈጥሮ ከመጀመሪያ ጀምሮ በአዳም መተላለፍ መበከሉን እንጂ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመሠረቱ ኃጢአት መሆኑን አያስተምርም።

<u>ቊ.7 ሂሶጵ</u>፤ ቅጠል ሲሆን በብሉይ ኪዳን ዘመን በማንጻት ሥርዓት ይጠቀሙበት ነበረና ከኃጢአት መንጻትን ያመለክታል። ዘሌዋውያን 14፥6-7።

<u>ቊ.10 ፍጠርልኝ</u>፤ በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ብቻ የሚፈጸም ድርጊት።

## 14. <u>የእግዚአብሔር ቤት</u>

1 ነገሥት 8፥1-21



<u>መግቢያ</u]፤ ዳዊት ከሞተ በኋላ ልጁ ሰሎሞን መንግሥቱን ይዞ በተሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት ቤተ መቅደስን መሥራት ጀመረ። ሥራው ከተጀመረ ከሰባት ዓመታት በኋላ በ960 ዓመታት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንዳለቀ ይገመታል። ይህ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከማንኛቸውም የላቀ ከፍተኛ የሥራ ውጤት ነበር። የእስራኤል ሕዝብ ዋና ማምለኪያና የተስፋቸው ማእከልም ነበር።

<u>ራስን ማዘጋጀት</u>፤ በዚያ ዘመንም ሆነ አሁን የማምለኪያን ስፍራ አስፈላጊነት ለመረዳት እንድትችል ጸልይ።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ሀ) ሰሎሞን ታቦቱን የት አኖረ (ቍ.1-6)? ለ) በታቦቱ ውስጥ ምን ነበረ (ቍ.9)? ሐ) ታቦቱ በቦታው ሲቆም ምን ሆነ (ቍ.10)?

2. ቍ.12-21ን አንብበህ የቤተ መቅደስን ዓላማና ጥቅም በራስህ አባባል ግለጥ።

3. ቤተ መቅደስ፥ ሀ) ለእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት ምን ያህል ይጠቅማል (ቍ.10-13፡27)፥ ለ) ስሙን ምን ያህል ያስጠራል (ቍ.14-20)፥ ሐ) ለቃል ኪዳን ሥርዓት ማስፈጸሚያ ምን ያህል ያገለግላል?

4. ሀ) ለእግዚአብሔር አምልኮ በውኑ ሕንፃ ያስፈልጋልን? ለ) ዛሬ ለአምልኮ የሕንፃ አገልግሎት ምንድን ነው? ሐ) ከእግዚአብሔር ሕዝብና ከሕንፃው የትኛው ይበልጣል?

<u>ማስታወሻ</u>፤


<u>ቍ.4 የእግዚአብሔር ታቦት</u>፤ ጥናት 9ንና ማስታወሻውን ተመልከት።

<u>ቍ.6 በቅድስተ ቅዱሳን</u>፤ በመገናኛው ድንኳን (ቍ.3) እንደ ነበረው በቤተ መቅደስም ሁለት ክፍሎች ነበሩ፤ በቅድስት ገበታው፥ መቅረዝና የወርቅ መሠዊያ ሲኖሩ በመጋረጃው ውስጥ በቅድስተ ቅዱሳን የእግዚአብሔርን ህልውና የሚያመለክተው ታቦት ብቻ ይገኝ ነበር። ጥናት 9ን ተመልከት።

<u>ቍ.13 ቤት በእውነት ሠራሁልህ</u>፤ እግዚአብሔርን የትም ቦታ ለማምለክ እንችላለን፤ ሆኖም ግን የተወሰነና የታወቀ ቦታ ለአምልኮ ይረዳል። በብሉይ ኪዳን ዘመን እንኳን በቍ.27 እንደተገለጠው ቤተ መቅደስ ለእግዚአብሔር ሕዝብ በረከት መቀበያ ቦታ እንጂ፥ እግዚአብሔር በቅርብ እንዲገኝ አስፈላጊ የሆን መድረክ አልነበረም።

## 15. የባዕድ አምልኮ ከንቱነት

**1 ነገሥት 18፥16-40**



መግቢያ፤ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ካነፀ በኋላ የባዕዳን አገሮች ሴቶችን በማፍቀር ለአማልክቶቻቸው በመስገዱ እግዚአብሔርን አስቆጣ (1 ነገሥት 11፥1-6)። ከሰሎሞን መኰንኖች አንዱ የነበረው ኢዮርብዓም በሰሎሞን ልጅ በሮብዓም ላይ ከእስራኤል ነገዶች አሥሩን አሳደመና በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ «እስራኤል» ተብሎ የሚታወቀውን የሰሜንን መንግሥት መሠረተ። የይሁዳና የብንያም ነገዶች ግን ለዳዊት ዘር ታማኞች በመሆን «ይሁዳ» የተባለውን የደቡብ መንግሥት ከመናገሻ ከተማው ከኢየሩሳሌም ጋር አጸኑ።

የእስራኤል መንግሥት ከመጀመሪያው ጀምሮ ባዕድ አምልኮን ተከተለ። በአክአብም ዘመን መናገሻ ከተማው ሰማርያ ነበረና እግዚአብሔር በ«ልምላሜ አምላክ» በበዓል ላይ እንዲመሰክር ታላቁን ነቢይ ኤልያስን አስነሣ።

ጸሎት፤ ማናቸውንም ባዕድ አምልኮ፥ ባሕርይና ልማድ በአግባቡ ለመቃወም እንድትችል ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. በአክአብ ዘመን፥ ሀ)የቤተ መንግሥት (ቊ.17-19)፥ ለ) የሕዝብ አምልኮ (ቊ.21) እንዴት ነበር?

________________________________________________

________________________________________________

2. ለመጀመሪያው የኤልያስ ጥያቄ የሕዝቡ መልስ ምን ነበር (ቊ.21)?

________________________________________________

3. ለሁለተኛው ጥያቄስ ምን መልስ ሰጡ (ቊ.22-24)?

________________________________________________

4. እሳቱ ከወረደ በኋላስ ምን አደረጉ (ቊ.39:40)?

________________________________________________

5. ኤልያስ በጸሎቱ እንደገለጠው ዓላማው ምን ነበር (ቊ.36:37)?

________________________________________________

________________________________________________

6. ሀ) ዛሬ አንተ ባዕድ አምልኮን እንዴት ትቃወማለህ? ለ) ቤተ ክርስቲያንስ?

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

ማስታወሻ፤

ቊ.17 እስራኤልን የምትገለባብጥ፤ የዚህ ክስ ምክንያት ኤልያስ ዝናብ እንዳይዘንብ መጸለዩ ነበር። 1ነገሥት 8፥35፤ 17፥1፤ ያዕቆብ 5፥17።

ቊ.18 በዐሊም፤ የበዐል ምስሎች።

ቊ.19 ኤልዛቤል፤ የጢሮስ ንጉሥ ልጅ ሆና ከአገርዋ የበዐልን አምልኮ ወደ እስራኤል አመጣች፥ ደግሞም በይሁዳ ንግሥት በሆነች በልጅዋ በጎቶልያ (በዐታልያ) አማካይነት ይህን አምልኮ ወደ ደቡብ መንግሥት አስገባች።

ዐፀድ፤ የበዐል «ሚስት» ምስሎች።


ቊ.29፤ መሥዋዕተ ሠርክ፤ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ከሰዓት በኋላ ይሠዋ ነበር።

ቊ.30፤ የእግዚአብሔር መሠዊያ፤ በዚህ ዘመን የነበረው ውስብስብ ሁኔታ የእስራኤል ሕዝብ በተራራዎች ላይ ለእግዚአብሔርና ለበዐል መሠዋታቸው ነበር።

ቊ.31 አሥራ ሁለቱን ድንጋዮች፤ ኤልያስ አሥራ ሁለቱን ነገዶች እንደ አንድ ሕዝብ አሁንም ይቈጥራቸው ነበር።

ቊ.40 ቊ.4 እና ዘዳግም 13፥1-5ን ተመልከት።

## 16. <u>የሚሳክ አገልጋይ</u> <u>ኢሳይያስ 52፥13-15፤53፥1-12</u>



<u>መግቢያ</u>፤ እግዚአብሔር በብዙ ነቢያት ለእስራኤልና ለይሁዳ መንግሥታት ተናገረ። በሰሜን መንግሥት ምንም እንኳ እግዚአብሔር በቀርሜሎስ ተራራ ኃይሉን ቢገልጥ ቤተ መንግሥቱና ሕዝቡ የኤልያስንና የተከታዩን የኤልሳዕ አገልግሎት አልተቀበሉም። በመጨረሻ 723 ዓመታት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሁኔታው እየባሰ ሲሔድ ጠቅላላው ሕዝብ ተማርከው ከአገራቸው ወደ አሦር ተወሰዱ። የይሁዳ መንግሥት ግን እንደ እስራኤል መንግሥት እውነተኛውን አምልኮ ቶሎ አልተወም ነበር። ለደቡብ መንግሥት ከተላኩ ነቢያት ሁሉ በይበልጥ የታወቀውና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከሌሎች ነቢያት ይልቅ በእጅጉ የተጠቀሰው ኢሳይያስ ነበር። እርሱም የእስራኤል መንግሥት ሲማረክ በኢየሩሳሌም ይኖር ነበር። ለአዳም (ዘፍጥረት 3፥15)፥ ለአብርሃም (ዘፍጥረት 12፥3)፥ ለሙሴ (ዘዳግም 18፥15-19) እና ለዳዊት (2 ሳሙኤል 7፥16) በተሰጡ የተስፋ ቃላት መሠረት ስለሚመጣው ስለ እግዚአብሔር አገልጋይ ትንቢት ተናገረ።

<u>ራስን ማዘጋጀት</u>፤ የመንፈሳዊውን ሕይወት ጉድለትና የመንግሥትን ድክመት በማስተዋል ቀደም ሲል የተሰጠውን የተስፋ ቃል በግንዛቤ ውስጥ አስገብተህ በኢሳይያስ ዘመን የምዕመናን ሕይወት እንዴት እንደነበር አሰላስል።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ባሪያ (አገልጋይን)፥ ሀ) ባሕርይና ሁኔታ (52፥13-53፥9)፥ ለ) አሟሟት (52፥14፤53፥4-9፡12)፥ ሐ) ፈቃድ (ለመሥዋዕትነት ፈቃድ 53፥12) እንዴት ይገልጣል?

2. ኢሳይያስ የአገልጋዩን የመሥዋዕትነት ዓላማ ለመግለጽ ሲል የዘረዘራቸውን ቃላትና ሐረጎች አመልክት (53፥4-12)።

3. አገልጋዩ ሕይወቱን ከሠዋ በኋላ ምን ይሆናል (52፥15፤53፥10-12)?

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ትንቢት እንዴት እንደፈጸመውና በመፈጸም ላይም እንደሚገኝ አስተውል።


<u>ማስታወሻ</u>

<u>53፥11 ብዙዎችን ያጸድቃል</u>፤ በሕግ ፊት ያለወቀሳ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

<u>53፥12 ከኃያላን ጋር ምርኮን ይከፋፈላል</u>፤ ድል ከነሣ በኋላ አንድ ድል አድራጊ እንደሚያደርገው ሁሉ።

## 17. የቃል ኪዳን መታደስ

**2 ነገሥት 22፥1-23፥7 እና 23፥24-26**



መግቢያ፤ በይሁዳ መንግሥት አንዳንዶች ነገሥታት ሕግን ሲያከብሩ ሌሎች ባዕድ አምልኮን ተከተሉ። ይህ ሁሉ ከሆን በኋላ አንድ ታማኝ ንጉሥ ተሐድሶ አድርጎ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ቃል ኪዳን አደሰው። የመጨረሻውም ንጉሥ ቃል ኪዳኑን ይፈጽም ዘንድ የይሁዳን ሕዝብ ያደፋፈረው ከእልከኞቹ ነገሥታት ከምናሴና ከአሞን በኋላ የነገሠው ኢዮስያስ ነበረ።

ጸሎት፤ የታዛዥ ሰዎችን መልካም አርአያ ተገንዝበህ በጽድቅ እንድትመላለስ የእግዚአብሔርን ጸጋ ከእግዚአብሔር ለምን።

ንባብ፤ አንቀጾቹን አንድ ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ሀ) ኢዮስያስን ወደ ተሐድሶ የመሩት ድርጊቶች ምን ነበሩ (22፥1-7)? ለ) በመጨረሻስ ተሐድሶን እንዲጀምር ያደረገው ነገር ምን ነበር (22፥8-10)?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

2. የሕጉን መጽሐፍ ሲሰማ ምን አደረገ (22፥11-13)? ለምን?

________________________________________

________________________________________

3. ንጉሡ ተሐድሶን ለማካሔድ ምን አደረገ (23፥1-7:24)?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

4. አንተ ለምትገኝበት ቤተ ክርስቲያን ለሚያስፈልገው ለውጥ ከዚህ ታሪክ ምን አርአያነት ታገኛለህ?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ማስገንዘቢያ፤ ሕይወትን ለማደስ (ለመለወጥ)፥ ሀ) በቤተ ክርስቲያን፥ ለ) በግል ሕይወትህ የእግዚአብሔር ቃል ኃያልነት ምን ያህል እንደሆነ አሰላስል።

ማስታወሻ፤

22፥3፤ በአሥራ ስምንተኛው ዓመት ...፤ የሃያ ስድስት ዓመት ሰው ነበረ። 2ዜና መዋዕል 34፥1-3 የኢዮስያስን መንፈሳዊ ዕድገት ይገልጣል። በዚህ ዘመን የአሦር መንግሥት ኃይል ስለ ደከመ ኢዮስያስ ያለ ውጭ ተጽዕኖ ቃል ኪዳኑን ለማደስ ነፃነት አገኘ።

22፥8 የሕጉን መጽሐፍ፤ መጽሐፉ «ኦሪት ዘዳግም» የነበረ ይመስላል። 23፥2 ተመልከት።

22፥14 ወደ ነቢይቱ ወደ ሕልዳና ሔዱ፤ ኢዮስያስ በቤተ መንግሥት ውስጥ የነበሩትን ነቢያትና አማካሪዎች አላመነም።

23፥24 ተራፊም፤ በቤት የሚገኙ የአምልኮ ምስሎች።

## 18. <u>ቃል ኪዳንን መሻርና ውጤቱ</u>

**2ዜና መዋዕል 36፥5-23**



<u>መግቢያ</u>፤ ምንም እንኳ አልፎ አልፎ እንደ እነ ኢዮስያስ ያሉት ነገሥታት ቃል ኪዳኑን ቢያድሱ፥ እንዲሁም እንደ ኢሳይያስና ኤርምያስ ያሉት ነቢያት ቢያስተምሩም የይሁዳ ቤተ መንግሥትና ሕዝብ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ግንኙነት በመሻር ባዕድ አምልኮን ተከተሉ፤ በዙሪያቸው ከነበሩት አረማውያን መንግሥታት ጋርም ስምምነት ፈጠሩ።

በ612 ዓመታት ከክርስቶስ ልደት በፊት የባቢሎን መንግሥት አሦርን አሸንፎ መናገሻ ከተማውን ነነዌን ያዘ። በ605 ዓመታት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የግብጽን ፈርዖን ኒካውን ድል ነሣ።

ሁለቱ የዜና መዋዕል መጻሕፍት እንደ 1 እና 2 ሳሙኤልና እንደ 1 እና 2 ነገሥት መጻሕፍት ከሳኦል ጀምሮ እስከ ኢየሩሳሌም መፍረስ ድረስ የነበረውን ዘመን ይተርካሉ። ትኩረታቸው ግን በተለይ በይሁዳ መንግሥት ላይ ሲሆን ለቤተ መቅደሱና ለአምልኮቱ አጽንኦት ይሰጣሉ።

<u>ጸሎት</u>፤ በዓለም ታሪክ ጥናት ሂደት የሚገኘውን በረከት ለማስተዋል እንድትችል ጸልይ።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ሀ) የሴዴቅያስ (ቍ.11-13)፥ ለ) የካህናቱና የሕዝቡ አካሔድ እንዴት ነበረ (ቍ.14-16)?

2. እግዚአብሔር እንዴት ቀጣቸው (ቍ.17-20)?

3. በዚህ ዘመን የኤርምያስ አገልግሎት ምን ነበረ (ቍ.12:21:22)?

4. ከዚህ አንቀጽ በሕዝቡ ላይ እግዚአብሔር ስለ ነበረው ቅናት ምን ትማራለህ (ቍ.12:15:16:17 :21-23)?

5. አንተ ከእግዚአብሔር መንገድ በወጣህ ጊዜ የደረሰብህን ስብራትና (የመንፈስ ስብራት) እግዚአብሔርም ያደረገልህን ምሕረት ግለጽ።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.21 ሴዴቅያስ</u>፤ ከ597-587 ዓመታት ከክርስቶስ በፊት የነገሠ የኢዮስያስ ሦስተኛ ልጅና የይሁዳ መጨረሻ ንጉሥ ነው።

**ሕዝቅኤል 36፥16-38**

## 19. የሕዝብ መመለስ



<u>መግቢያ</u>፤ ኢየሩሳሌም በአረማውያን እጅ ተይዛ በነበረበት ጊዜ ቤተ መቅደሱ ፈርሶ ነበር። ከሕዝቡም አብዛኛዎቹ በባቢሎን አገር በምርኮ መጀመሪያ በተስፋ በኋላም ያለተስፋ የሕይወት ዘመናቸውን ያሳልፉ ነበር። ከኢየሩሳሌም ርቀው ሲኖሩ በእነዚህ 70 ዓመታት ውስጥ ወደ አገራቸው እንዲመለሱና የእስራኤልን ኑሮና አምልኮ እንዲያድሱ እግዚአብሔር አንድ የዘር ግንድ አዘጋጀ። ከምርኮኞቹ መካከል ሕዝቡ የትላንት ታሪካቸውን እንዲያስተውሉ፥ ወደ አገራቸው የመመለስ ተስፋ እንዲኖራቸውና ከኃጢአታቸውም ነጽተው በቅድስና መንገድ እንዲራመዱ እግዚአብሔር ሁለት ዐበይት ነቢያትን፥ ማለትም ሕዝቅኤልንና ዳንኤልን አስነሣ።

<u>ጸሎት</u>፤ ሰው ወደ በረከት የሚመለስበትን መንገድ እንድታስተውል ጌታን ለምን።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. አንቀጹን እንደገና አንብበህ ከተነገሩት ትንቢቶች ዋነኞቹን ዘርዝር።

____________________

____________________

____________________

____________________

2. አንቀጹ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከምርኮ ለማሰባሰብ ስለተገፋፋበት ምክንያት ምን ይገልጣል (ቍ.16-24:32:36)?

____________________

____________________

____________________

3. ሀ) ሕዝቡ በግል ሕይወቱ ለውጥ ለምን ያስፈልገዋል (ቍ.25-27)? ለ) አንተስ እንዲህ ዓይነቱን ለውጥ በሕይወትህ ታውቃለህን?

____________________

____________________

____________________

4. ወደ አገራቸው ለሚመለሱ አይሁድ ምን ተስፋ ተሰጣቸው (ቍ.28-38)?

____________________

____________________

5. አንድ ክርስቲያን እነዚህን የተስፋ ቃላት በሕይወት ጕዞው እንዴት ሊጠቀምባቸው ይችላል?

____________________

____________________

____________________

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ ሰው ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ ስለሚታይበት ለውጥ አሰላስል።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.25 ውኃ ... ቍ.27 መንፈስ ...</u>፤ ጌታችን ሰው «ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» ሲል ኒቆዲሞስን ወደዚህ አንቀጽ ያመለከተው ይመስላል። ዮሐንስ ወንጌል 3፥5 እና 10ን ተመልከት።


<u>ቍ.26 ልብ</u>፤ የስሜት እምብርትነት ብቻ ሳይሆን የሰውን አእምሮና ፈቃድ ያጠቃልላል።

<u>መንፈስ</u>፤ ሰውን የሚያንቀሳቅስና ስሜቱን፥ አሳቡንና አካሔዱን የሚገዛ ነው።

<u>የሥጋ ልብ</u>፤ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የሚታደስ፥ የሚለወጥና የሚታዘዝ ነው።

## 20. <u>አዲሱ ቤተ መቅደስ</u>





<u>መግቢያ</u>፤ የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ ባቢሎንን ሲይዝ ቤተ መቅደሱ እንደገና እንዲሠራ ከእስራኤል ሕዝብ ፈቃደኞች የሆኑትን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ አዘዘ፤ 70 ዓመታት ከመጀመሪያው ምርኮ በኋላ በ538 ዓመታት ከክርስቶስ ልደት በፊት 42360 አይሁድ ተመለሱና በ516 ቤተ መቅደሱን ለመጨረስ በቁ። በየጊዜው ልዩ ልዩ አይሁድ ተመለሱ። ከእነዚህም ውስጥ በተለይ የታወቁት ዕዝራና ነህምያ ነበሩ። እነርሱ የተመለሱበት ዘመንም ከ458-445 ክልል ውስጥ እንደሆነ ይገመታል።

ኢየሩሳሌም በፋርስ መንግሥት (እስከ 331 ዓመታት ከክርስቶስ በፊት)፥ በግሪክ መንግሥት (እስከ 63) እና፥ በሮም መንግሥት እስከ ጌታችንና ሐዋርያት ዘመን ድረስ ተገዥ ሆና ነበር።

<u>ጸሎት</u>፤ በእግዚአብሔር ጸጋ የታደሱትን ሰዎች ሕይወት ለማስተዋል እንድትበቃ ጸልይ።

<u>ንባብ</u>፤ ምዕራፉን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ሀ) የሕዝቡ ሁኔታ እንዴት ነበረ (ቍ.1:3)? ለ) ሥራውን የመሩት ሁለቱ ሰዎች እነማን ነበሩ?

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

2. ኢየሩሳሌም ከደረሱ በኋላ በሁለቱ የመጀመሪያ ዓመታት ምን ለማድረግ ቻሉ (ቍ.1-3:9:10)?

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

3. ሀ) እንደገና ማምለክና መሥዋዕት ማቅረብ ሲጀምሩ መመሪያቸው ምን ነበረ (ቍ.2:4:10)? ለ) ይህ ለአንተ ምን አርአያነት አለው?

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

4. ሀ) በሕዝቡ መካከል ይነበቡ የነበሩት ስሜቶች ምን ዓይነት ነበሩ (ቍ.11-13)? ለ) ለምን? ሐ) በፊት ከተቀበልከው ኀላፊነት የአሁኑ ዝቅተኛ ቢሆን ምን ይሰማሃል?

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________


______________________________

<u>ልመና</u>፤ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ስትገኝ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ታማኝ እንድትሆን ጸልይ።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.4 የዳስ በዓል</u>፤ ወይም የአዝመራ መሰብሰቢያ በዓል። በዚህ በዓል አይሁድ አባቶቻቸው በምድረ በዳ እንዴት እንዳለፉ ለመዘከር በድንኳንና በዳስ በመኖር ሳምንቱን ያሳልፉ ነበር።

# ክፍል 2 የአዳኙ መምጣት





| | | | ገጽ |
|---|---|---|---|
| | **የመሢሕ አመጣጥ** | | |
| 21. | ማቴዎስ 1፥1:17-25 | የአዳኙ ብሥራተ ልደት | 25 |
| 22. | ማርቆስ 1፥1-20 | የአገልግሎት መግቢያ | 26 |
| | **የመንግሥተ ሰማያት አዋጅ** | | |
| 23. | ዮሐንስ 3፥1-19 | ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት | 27 |
| 24. | ማቴዎስ 5፥1-17 | የአዲሱ ዜጋ ጠባይ | 28 |
| 25. | ማቴዎስ 6፥1-18 | የዜጋው ሃይማኖት | 29 |
| 26. | ማቴዎስ 6፥19-34 | የዜጋው የዕለት ተዕለት ኑሮ | 30 |
| 27. | ማቴዎስ 7፥13-29 | የዜጋው የዕለት ተዕለት ምርጫ | 31 |
| 28. | ማቴዎስ 8፥23-9፥8 | የሰው ልጅ ሥልጣን | 32 |
| 29. | ማቴዎስ 13፥1-23 | መንግሥቱ የተስፋፋበት ስልት | 33 |
| 30. | ዮሐንስ 6፥1-15:35:36 | የይፋ አገልግሎት አክሊል | 34 |
| | **ለሕማማት መዘጋጀት** | | |
| 31. | ማቴዎስ 16፥13-28 | መንግሥቱና መስቀሉ | 35 |
| 32. | ሉቃስ 10፥25-37 | ሕግና ባልንጀራ | 36 |
| 33. | ዮሐንስ 10፥11-31 | መልካም እረኛውና በጎቹ | 37 |
| 34. | ማቴዎስ 21፥1-17 | ወደ መጨረሻው መቅረብ | 38 |
| 35. | ሉቃስ 22፥7-23 | የመጨረሻው እራት | 39 |
| 36. | ዮሐንስ 14፥1-27 | መንገዱና አጽናኙ | 40 |
| | **የደኅንነት መፈጸም** | | |
| 37. | ማቴዎስ 26፥47-68 | እስራትና ፍርድ | 41 |
| 38. | ማቴዎስ 27፥24-44 | ክህደትና ስቅለት | 42 |
| 39. | ማቴዎስ 27፥45-66 | ሕማምና ሞት | 43 |
| 40. | ማቴዎስ 28 | ድልና ታላቁ ተልእኮ | 44 |

## 21. <u>የአዳኙ ብሥራተ ልደት</u> — <u>ማቴዎስ 1፥1፡17-25</u>



<u>መግቢያ</u>፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን በተሰጠው ተስፋ መሠረት ከዘፍጥረት ጀምሮ የተተነበየለት መሢሕ ወደ ዓለም መጣ (የ16ኛውን ጥናት መግቢያ ተመልከት)። «መሢሕ» በዕብራይስጥ፥ «ክርስቶስ» በግሪክ ሲሆን፥ ትርጒሙም የተቀባ ማለት ነው። በቃሉ መሠረት «እግዚአብሔር ኢየሱስን ቀባ» ሲባል የዓለም አዳኝ እንዲሆን ሾመው፥ ለኀላፊነቱም ሥልጣንና ኃይልን ሰጠው ማለት ነው።

<u>ጸሎት</u>፤ ጌታ ኢየሱስ ማን እንደሆነ ለማስተዋል እንድትችል ጸልይ።

<u>ንባብ</u>፤ የተመለከቱትን ጥቅሶች በጥንቃቄ ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. በዚህ የትውልድ ሐረግ መሠረት በተለይ የተጠቀሱት ሁለቱ የኢየሱስ ቀደምት አባቶች እነማን ናቸው (ቊ.1፡17)? በአንተ አስተያየት የትውልድ ሐረጉ ዝርዝር በተለይ በእነዚህ ላይ ለምን አጽንኦት ያደርጋል?

____________________

____________________

2. በዚህ ጊዜ በዮሴፍና በማርያም መካከል ያለው ኅብረት እንዴት ነው?

____________________

3. ዮሴፍ ምን ለማድረግ አሰበ? በኋላ ግን ምን ሆነ?

____________________

____________________

4. ስለ ኢየሱስ ልደትና ማንነት፥ ሀ) ከመልአኩ መልእክት፥ ለ) ከተጠቀሰው ከኢሳይያስ ትንቢት (ቊ.23) ፦ ምን ትረዳለህ?

____________________

____________________

____________________

____________________

5. ኢየሱስ ለምን መጣ (ቊ.21)?

____________________

6. ስለ ኢየሱስ ልደት ስታስብ ምን ታስተውላለህ?

____________________

____________________

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ አብርሃም ቃል ኪዳንን ከተቀበለ ከ2000 ዓመታትና ዳዊት ከነገሠ ከ1000 ዓመታት በፊት፥ በመጨረሻ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በዚህ ዓለም በመመላለሱ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ እውን ሆነ።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ማቴዎስ</u>፤ ይህ ወንጌል ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በአንዱ በማቴዎስ፤ ለአይሁድ ሕዝብ በተለይ እንደተጻፈ በቤተ ክርስቲያን መምህራን ከጥንት ጀምሮ ቢታመንም አንዳንዶች ከማቴዎስ በኋላ በሌላ ሰው እንደተጠናቀቀ ያስባሉ።

<u>ቊ.1 ዳዊት</u>፤ በትውልድ ሐረግ ሁለት ጊዜ «ንጉሥ ዳዊት» ተብሏል (ቊ.6፡7)፥ እንዲሁም ዮሴፍ «የዳዊት ልጅ» ተብሎ ይጠራል (ቊ.20)። 12ኛውን ጥናት ተመልከት።

<u>ቊ.18 ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ</u>፤ በአይሁድ ልማድ መሠረት ምንም እንኳን አብረው ባይኖሩም እንደ ባልና ሚስት ይቈጠሩና ይከበሩ ነበር (ቊ.19 እና 20 ተመልከት)።

<u>ቊ.21 ኢየሱስ</u>፤ ስሙ «አዳኝ» ማለት ነው።

<u>ቊ.23</u> ኢሳይያስ 7፥14ን ይጠቅሳል።

## 22. የአገልግሎት መግቢያ

**ማርቆስ 1፡1-20**



መግቢያ፤ ኢየሱስ በዳዊት ከተማ በቤተልሔም ተወልዶ፥ ከኢየሩሳሌም ርቆ በሚገኘው በናዝሬት አደገ፥ ሠላሳ ዓመት እስኪሞላው ድረስም በዚያው ኖረ። በዚህ ዘመን እስራኤል በሮሜ መንግሥት ቅኝ ግዛት ሥር ነበረች። ከመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ነቢይ ከሚልክያስ ጀምሮ እስከ መጥምቁ ዮሐንስ ድረስ የእስራኤል ሕዝብ ለ400 ዓመታት በዝምታ ታልፈው ነበር፤ ነገር ግን ማንም ሳያስበው ግን መጥምቁ ዮሐንስ በምድረ በዳ እየሰበከ መጣ።

ራስን ማዘጋጀት፤ ኢየሱስ አገልግሎቱን ሲጀምር በራሱ አኗኗር ምን ያህል ለውጥ እንዳመጣ እንድታስተውል ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ዮሐንስ በስብከቱ ያመለከተው ምን ነበር (ቍ.4-8)?

2. ኢየሱስ ኃጢአት የሌለበት ሲሆን ከኃጢአተኞች ጋር ለምን ተጠመቀ?

3. ኢየሱስ በይፋ ለማገልገል እንዴት ዝግጁ ሆነ (ቍ.9-13)?

4. በሦስቱ መለኮታውያን አካላት ያለው አንድነትና ሦስትነት በክርስቶስ ጥምቀት እንዴት ተገለጠ (ቍ.1:9-11)?

5. የእግዚአብሔር መንግሥት፥ ሀ) አዋጅ፥ ለ) ሥራ ምንድን ነው (ቍ.14-20)?

ማስገንዘቢያ፤ ኢየሱስ፥ ሀ) ከናዝሬት ሲወጣ፥ ለ) ሲጠመቅ፥ ሐ) በምድረ በዳ ሲመላለስ ስሜቱ እንዴት እንደነበረ አስተውል።

ማስታወሻ፤

ማርቆስ፤ ጌታ ኢየሱስን በአካል አውቆት እንደነበረ ለማስተዋል እንችላለን፤ በማርቆስ 14፥51-52 የሚገኘው «ጕበዝ» ማርቆስ ራሱ እንደሆነ አያሌ ሊቃውንት ይመሰክራሉ። ማርቆስ የጴጥሮስን ስብከትና ትረካ መሠረት በማድረግ ወንጌሉን ለሮሜ ሰዎች እንደጻፈ ይታሰባል።


ቍ.23 ማርቆስ የሚልክያስን 3፥1 እና የኢሳይያስን 40፥3 የትንቢት ቃላት እያገናዘበ ጽፎአል።

ቍ.4 ንስሐ፤ አካሔድን ሁሉ የሚያስተካክል የአስተሳሰብ ለውጥ።

ቍ.14 ዮሐንስ የታሰረው ከኢየሱስ ጥምቀት በኋላ ባሉት ወራት ውስጥ ነበረ።

## 23. <u>ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት</u>

<u>ዮሐንስ 3፥1-19</u>



<u>መግቢያ</u>፤ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ከተማ በታላላቅ በዓላት ላይ ይገኝ ነበር። ከጥምቀቱ በኋላ በአይሁድ ፋሲካ ሰሞን ብዙ ተአምራትን አደረገ (ዮሐንስ 2፥23)።

<u>ጸሎት</u>፤ ሰው ወደ መንግሥቱ እንዴት መግባት እንደሚችል እንድታስተውል እግዚአብሔርን ጠይቅ።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ይህ የሃይማኖት ሊቅ የጐደለው ምን ነበር (ቍ.3-6፡9-13፡18፡19)?

2. ዳግመኛ መወለድ ከየት ይመጣል (ቍ.5፡8 እና ማስታወሻውን ተመልከት)?

3. ሰው ዳግመኛ እንደተወለደ በምን ይታወቃል (ቍ.8፡16)?

4. ሰው ልቡን ወደ ክርስቶስ ሲመልስ ሊያምንባቸው የሚገባው ዐበይት የእምነት መሠረቶች ምን ምን ናቸው (ቍ.14-16)?

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት ሰው በተሰቀለው በክርስቶስ ተስፋውን ሁሉ ሲጥል በሕይወቱ ውስጥ ምን ለውጥ ይታያል? በአንተ ዘንድ ይህ ለውጥ ይታያልን?

<u>ምስጋና</u>፤ አንድያ ልጁን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመስጠት ስለ ገለጠው ፍቅሩና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ እግዚአብሔርን አመስግን።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.1 ፈሪሳውያን</u>፤ በአይሁድ ዘንድ የሙሴን ሕግ በጥብቅ ያከብሩ የነበሩ የሃይማኖት መሪዎች ናቸው።

<u>ቍ.5 ከውኃና ከመንፈስ</u>፤ ሁለቱ ቃላት የዳግመኛ መወለድን መንትያ መግለጫዎች ፦ መንጻትንና መታደስን ያመለክታሉ። በ19ኛው ጥናት የሕዝቅኤል 36፥25-27 ማስታወሻን ተመልከት።


<u>ቍ.12 ስለ ምድራዊ ነገር</u>፤ ዳግመኛ መወለድ መሠረቱ ከሰማይ ቢሆንም እንኳን በምድር ስለሚፈጸም «ምድራዊ ነገር» ተብሏል።

<u>ቍ.14 ሙሴ ... እባብን እንደሰቀለ</u>፤ ዘኍልቍ 21፥5-9 ተመልከት።

<u>ቍ.15 በእርሱ የሚያምን</u>፤ እንደ ዮሐንስ 1፥12፡13 እና 1 ዮሐንስ 5፥1 አንቀጹ ማመን ዳግመኛ መወለድን እንደሚከተል ወይም ጐን ለጐን እንደሚሔድ ያሳያል።

## 24. የአዲሱ ዜጋ ጠባይ





<u>መግቢያ</u>፤ ኢየሱስ ሰዎችን ንስሐ እንዲገቡና እንዲያምኑ ወደ አዲስ ሕይወት ሲጠራቸው፥ የመንግሥቱ ዜጋዎች ስለ ሆኑ ዕለታዊ ሕይወታቸው እንዴት መሆን እንደሚገባው በግልጥ ያስተምር ነበር።

<u>ጸሎት</u>፤ የመንግሥቱ ዜጋ ሆነህ ስትኖር በሕይወትህ ምን ጉድለት እንዳለ ለማየት እንድትችል እግዚአብሔር ዓይኖችህን እንዲከፍትልህ ለምን።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ሀ) የአዲሱ ዜጋ ጠባያት ምንድን ናቸው (ቍ.1-11)? ለ) የእነዚህ ጠባያት ተቃራኒዎችስ ምንድን ናቸው?

2. ለዜጋው ምን ተስፋ ተሰጠው (ቍ.2-12)?

3. የመንግሥተ ሰማያት ዜጋ በዚህ ዓለም ሲኖር ኀላፊነቱ ምንድን ነው (ቍ.13-16)?

4. ጌታ ኢየሱስ ትምህርቱን ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር እንዴት ያገናኘዋል (ቍ.17)?

5. በሕይወትህ ውስጥ የሚገኙትን መልካም ሆነ መጥፎ ጠባያት በቍ.1(ሀ)ና (ለ) ጥያቄ መልሶች ላይ የሚገኙትን ዝርዝሮች እየለየህ አስምር።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ በመለስተኛ መጠን እንኳ የመንግሥቱ ዓይነተኛ መለያዎች የሚገኙት ዳግመኛ በመወለድ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ አዲሱ ዜጋ በነዚህ ባሕርያት ውስጥ እያደገ መሔድ ይኖርበታል።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.3 በመንፈስ ድሆች</u>፤ በራሳቸው ሥራ፥ ጠባይ፥ ወዘተ እንዳይታበዩ ነው እንጂ የተፈጥሮ ድክመትን አያመለክትም። መዝ.50(51)፥17፤ ማቴ.11፥25፤18፥1-3 ተመልከት።

<u>ቍ.4 የሚያዝኑ</u>፤ በራሳቸውና በዓለም ዘንድ ስለሚገኘው ክፋት።

<u>ቍ.5 የዋሆች</u>፤ ማቴ.11፥28-29 ተመልከት።

<u>ቍ.8 እግዚአብሔርን ያዩታልና</u>፤ ዮሐ.14፥9፤ 1ዮሐ.3፥2-3 ተመልከት።

## 25. የዜጋው ሃይማኖት

ማቴዎስ 6፥1-18




መግቢያ፤ ኢየሱስ ሕግና ነቢያት ስለ መፈጸማቸው ሲያብራራ ከባልንጀራ ጋር በሰላም ለመኖር ስድስት ምሳሌዎችን ሰጠ። (5፥17-48)። ቀጥሎም የመንግሥቱ ዜጋ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት መራመድ እንደሚገባው ገለጠ።

ጸሎት፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰሚነትን የሚያስገኙትን ባሕርያትና ድርጊቶች ሁኔታ በበለጠ እንድታስተውል ጌታን ለምን።

ንባብ፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. በዚህ አንቀጽ ጌታችን ያስተማራቸው ሦስቱ የአይሁድ የግል ሃይማኖት ባሕርያት ወይም ድርጊቶች ምንድን ናቸው?

2. ሀ) ለእውነተኛ ሃይማኖት ድርጊት፥ ለ) ለታይታ የሚደረግ ሥርዓት ዋጋ ከየት ይሰጣል?

3. ሀ) የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ወደ ማን ይጸልያል (ቍ.9)? ለ) ለጸሎት ራሱን እንዴት ያዘጋጃል (ቍ.6)? ሐ) በጸሎቱ ምን እንቅፋት ሊገጥመው ይችላል (ቍ.5፡7፡8፡14፡15)? መ) የአንተ ጸሎትስ ልምድ ከእነዚህ ጋር እንዴት ይገናኛል?

4. የ«አቡነ ዘበሰማያት»ን ሰባት ጥያቄዎች ዘርዝር። ቅደም ተከተላቸውንም ከራስህ የዘወትር ጸሎት ጋር አነጻጽር።

ማስገንዘቢያ፤ በምጽዋት፥ በጸሎትና በጾም ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደምትገናኝ አሰላስል።

ማስታወሻ፤

ቍ.1 ምጽዋት፤ ቃሉ በግሪክ ቋንቋ ማንኛውንም መልካም ሥራ ያመለክታል።

ቍ.6 እልፍኝህ፤ ቃሉ ሰው ሀብቱን ወይም ንብረቱን የሚያስቀምጥበትን የውስጥ ክፍል ያመለክታል።

ቍ.13 ፈተና፤ በዚህ አገባቡ ኃጢአት ለመሥራት አይደለም፤ ነገር ግን አዲሱ ዜጋ ለእግዚአብሔር ሥራ ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።

## 26. <u>የዜጋው የዕለት ተዕለት ኑሮ</u>





<u>መግቢያ</u>፤ ኢየሱስ የዜጋውን (የክርስቲያን) ባሕርይ (5፥1-16)፥ ከባልንጀራውና (5፥17-48) ከእግዚአብሔር ጋር (6፥1-18) ያለውን ግንኙነት ካብራራ በኋላ፥ መንግሥቱ የሰውን ሁለንተናዊ ሕይወት ስለሚመለከት ስለ ዕለት ሲሳይ አስተማረ።

<u>ራስን ማዘጋጀት</u>፤ በክርስቶስ ትምህርት መሠረት ስለ ገንዘብና ስለ ሀብት ያለህን አስተያየት ለመለወጥ ዝግጁ እንድትሆን ጸልይ።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ሀ) ሰው ስለ ገንዘብ ለመወሰን የሚያስፈልጉት ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው (ቍ.19-21፡22-23፡24)? ለ) የእነዚህ ነገሮች የውሳኔ ውጤትስ ምን ይሆናል (ቍ.19-24)?

2. ስለ ዕለት ኑሮ መጨነቅ ዓይነተኛ የእምነት ጉድለት መሆኑ እንዴት ይታያል (ቍ.31-32)?

3. በሰማያዊ አባታችን እንድናምን ጌታችን ምን አራት ምክንያቶችን ያቀርባል (ቍ.25-30)?

4. እንግዲህ ዜጋው ለዕለት ተዕለት ኑሮው የሚያስፈልገውን እንዴት መከታተል ይገባዋል (ቍ.33፡34)?

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት ስለ ትዳር (ኑሮ) ያለህን አስተያየት እንዴት ትለውጣለህ?

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ እግዚአብሔር አባትህ ስለ መሆኑ አሰላስል።

<u>ማስታወሻ</u>፤


<u>ቍ.22 ዓይን</u>፤ አስተያየት የሕይወትን ሁኔታ ሁሉ ይወስናል።

<u>ቍ.25 ስለዚህ ...</u>፤ ጌታችን የሥሥትን ጠንቅ (ክፋት) ከገለጠ በኋላ በሰው ዘንድ በዕለት ኑሮ ምክንያት ስለሚደርስ ጭንቀት ያስተምራል።

<u>ቍ.33</u> በጥቅሱ የተገለጡትን ሐሳቦች ቅደም ተከተል ከቍ.10 እና 11 ጋር አነጻጽር።

<u>ቍ.34</u> ማንኛውም ክርስቲያን ችግር ሊያጋጥመው ይችላል፥ ሆኖም ወደፊት ስለሚያጋጥመው ችግር ሳይጨነቅ፥ የዕለት ተዕለት ተግባሩን ማከናወን ይኖርበታል።

## 27. <u>የዜጋው ዕለት ተዕለት ምርጫ</u> <u>ማቴዎስ 7፥13-29</u>



<u>መግቢያ</u>፤ ጌታችንበ7፥1-12የመንግሥቱዜጋዎችበወንድሞቻቸውና በእህቶቻቸው ላይ እንዳይፈርዱ እውነተኛንና ሐሰተኛን ሰዎች፥ እንደዚሁም ትክክለኛንና ሐሰተኛን ትምህርት መለየት እንዴት እንደሚችሉ ያስተምራል። ቀጥሎም ይህን «የተራራው ስብከት» የሚባለውን ታላቅ ትምህርት በአንዳንድ ከባድ ማስጠንቀቂያዎች ይደመድመዋል።

<u>ጸሎት</u>፤ የኢየሱስን ድምጽ ሰምተህ ወዲያው ለመታዘዝ ዝግጁ እንድትሆን ለምን።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. የመንታ መንገዶቹን፥ ሀ) በር፥ ለ)መመላለሻ፥ ሐ) መዳረሻ፥ መ) ደንበኞች (አባላት) አነጻጽር (ቍ.13-14)።

2. በአኗኗር፥ ሀ) ስለ ደጁ ጠባብነት፥ ለ) ስለ መንገዱ ቀጭንነት ምን ተገንዝበሃል?

3. የሐሰተኞች ነቢያት ወይም መምህራን፥ ሀ) መልክ፥ ለ) ጠባይ፥ ሐ) ትምህርት፥ መ) የሥራ ፍሬ፥ ሠ) የመጨረሻ ውጤት ምንድን ነው (ቍ.15-23)?

4. የሁለቱን ቤቶች ምሳሌ ተመልክተህ ከእግዚአብሔር አዲስ ሕይወትን በተቀበለውና በዘልማድ ሃይማኖትን በሚከተለው ሰው መካከል ያለውን ልዩነት ግለጥ።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ ሁለት ደጆች፥ ሁለት መንገዶችና ሁለት ቤቶች ብቻ ስለሚገኙ ሌላ ሦስተኛና ምቹ ጐዳና መፈለግ ከንቱ መሆኑን አሰ .።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.15</u> እነዚህ ሐሰተኞች ሰው እውነተኛውን ደጅ በቀላሉ እንዳይመለከት ይጋርዳሉ።

<u>ቍ.21-23</u> የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸምና በጠባብ መንገድ መመላለስ እንጂ በክርስቶስ ስም ማስተማርና ተአምራትን ማድረግ በክርስቶስ ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት ዋስትና አይሰጥም።

## 28. <u>የሰው ልጅ ሥልጣን</u>

**ማቴዎስ 8፥23-34፤ 9፥1-8**



<u>መግቢያ</u>፤ ከሙሴ፥ ከብሉይ ኪዳን ነቢያትና ከጌታችን በኋላ ከመጡት የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ በላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአገልግሎቱ ዘመን ሁሉ ተአምራትን፥ ድንቆችንና ምልክቶችን እያደረገ ሥልጣኑን፥ ባሕርዩንና ተልዕኮውን ገለጠ።

<u>ጸሎት</u>፤ የጌታችንየኢየሱስክርስቶስን ሥልጣንአስተውለህበሕይወትህእንድታሳየው ጸልይ።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. በእነዚህ ታሪኮች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣኑን ያሳየው በምን ላይ ነው? አራት ነገሮችን ዘርዝር።

2. ይህ አንቀጽ ስለ ክርስቶስ፥ ሀ)ማንነት (8፥26:29፤9፥2:6)፥ ለ) ባሕርይ (8፥23:24፤9፥2:4) ምን ያስተምራል?

3. ከዚህ አንቀጽ፥ ሀ) ስለ ሰው ክቡርነት (8፥31:32)፥ ለ) ስለ ሥጋዊና መንፈሣዊ ደኅንነት (9፥2-6) ምን ትማራለህ?

4. ሰዎች የኢየሱስን ኃይል አይተው ምን አደረጉ (8፥27:33:34፤9፥3:8)?

5. ሀ) በምን መንገድ የክርስቶስን ኃይል ለማየት ወይም ለማወቅ ተስፋ ታደርጋለህ? ለ) ይህ እንዲሆን የአንተ ፈንታ ምንድን ነው (ስለ 9፥2 አሰላስል)?

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም ዛሬም ለዘላለም ያው ነው» ዕብራውያን 13፥8።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>8፥26 እምነት የጐደላችሁ</u>፤ ማቴዎስ 6፥30ን ተመልከት።

<u>8፥29 ጊዜው ሳይደርስ ልታሠቃየን ወደዚህ መጣህን</u>፤ ያዕቆብ 2፥20ን ተመልከት።

<u>8፥32</u> ሁለቱ ሰዎች የመንጋውን ጥፋት አይተው አጋንንት ከእነርሱ እንደወጡ በግልጥ ሊያውቁ ይችላሉ።

<u>9፥1 የገዛ ከተማው</u>፤ ቅፍርናሆምን ያመለክታል። 4፥13ን ተመልከት።


<u>9፥2 አይዞህ</u>፤ ቃሉ ሽባው በደሉን እንደተረዳና እምነት እንደነበረው ያሳያል።

<u>9፥3 ይሳደባል</u>፤ ማርቆስ 2፥7ን ተመልከት።

## 29. መንግሥቱ የተስፋፋበት ስልት

**ማቴዎስ 13፥1-23**

መግቢያ፤ ሰዎች በተለይም የሃይማኖት መሪዎች ትምህርቱን ሲቃወሙ (ማቴዎስ 12፥ 22-32)፥ ጌታችን ሕዝቡን በምሳሌዎች አስተማረ፤ ትርጓሜያቸውን ግን ለደቀ መዛሙርቱ ብቻ አብራራ። ሰዎች የመንግሥቱን መልእክት የማይቀበሉበትን ምክንያት ለተከታዮቹ ማስረዳት አስፈላጊ ነበርና።



ጸሎት፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንዴት እንደሚስፋፋ እንድታስተውል ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ፤ ቀጥሎም ቍ.3-9 እና 18-23ን እንደገና መርምር።

ጥያቄ፤

1. ሀ) ዘሪው ማን ነው? ለ) ዘሩስ ምንድን ነው?

______________________________

______________________________

2. በምሳሌው የተጠቀሱትን የአራቱን ዓይነት መሬት ትርጕሞች ግለጥ።

ሀ) በመንገድ ዳር ያለው :- ______________

ለ) የጭንጫማው :- ______________

ሐ) እሾኽማ ቍጥቋጦ ያለበት :- ______________

መ) መልካም መሬት :- ______________

3. አንተ የምትኖርበት ኅብረተሰብ ቃሉን እንዳይቀበል ምን ዐይነት እንቅፋቶች አሉ?

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

4. ልብህ «መልካም መሬት» ነውን? ቃሉን በበጎ አኳኋን እንድትቀበል ልብህን ማለስለስ፥ መኮትኮትና ማረም ትችላለህን?

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

ማስገንዘቢያ፤ የመንግሥቱ ዜጋ ዳግመኛ የሚወለደው «ሕያው በሆነውና ለዘላለም ጸንቶ በሚኖረው በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ ከሚጠፋ ዘር አይደለም»። 1ጴጥሮስ 1፥23።


ማስታወሻ፤

ቍ.21 ወዲያው ይሰናከላሉ፤ ብዙዎች ቃሉን በደስታ ይቀበላሉ (ቍ.20)፤ ያልታሰበ ችግር ሲደርስባቸው ግን ወዲያው ያፈገፍጋሉ።

ቍ.23 ፍሬ ያፈራል፤ የእውነተኛ እምነት ማረጋገጫ ነው። 7፥24፤ 12፥33ን ተመልከት።

## 30. <u>የይፋ የአገልግሎት አከሊል</u>

<u>ዮሐንስ 6፥1-15፡35፡36</u>



<u>መግቢያ</u>፤ በአራቱም ወንጌላት ውስጥ ብቸኛ ተጠቃሽ ተአምር በአምስት እንጀራ አምስት ሺህ ሰዎችን መመገብ ነው። እስከዚህ ተአምር ድረስ የኢየሱስ ተከታዮች እየበዙ መጡ። ከዚህ በኋላ ግን ብዙዎች አፈገፈጉ፥ የኢየሱስ መንግሥት እነርሱ በጠበቁት ዓይነት አልነበረምና።

<u>ራስን ማዘጋጀት</u>፤ ለኢየሱስ ጥሪ ማስተዋል የተሞላበት መልስ ለመስጠት እንድትችል ከእግዚአብሔር ጥበብን ለምን።

<u>ንባብ</u>፤ የተሰጡትን ቊጥሮች ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ተአምሩ በተፈጸመበት በገሊላ ባሕር ግዶ በጋዜጠኝነት ብትገኝ ኖሮ ምን ትጽፍ ነበር?

2. ሀ) ሕዝቡ ምን ለማድረግ ፈለገ? ለ) ለምን?

3. ሀ) ኢየሱስ «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ» በማለቱ ምን አስተማረ (ቊ.35)? ለ) እንግዲህ ይህን የሕይወት እንጀራ እንዴት ነው የምትበላው (35፡36)?

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ ኢየሱስ «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም» (ዮሐንስ 18፥36) በማለት ለጲላጦስ መግለጡ በምድራዊ ወይም በሥጋዊ ሳይሆን በመንፈሳዊ ረገድ መሆኑን ያሳያል።

<u>ማስታወሻ</u>፤


<u>ቊ.4 ፋሲካ</u>፤ ከስቅለቱ አንድ ዓመት በፊት ነው።

<u>ቊ.14 ነቢይ</u>፤ ኦሪት ዘዳግም 18፥15ን ተመልከት።

<u>ቊ.36 አይታችሁኝ እንዳላመናችሁ</u>፤ ካለማመናቸው የተነሣ ብዙዎች ክርስቶስን መከተል ተዉ (ቊ.66)።

## 31. መንግሥቱና መስቀሉ

**ማቴዎስ 16፥13-28**



መግቢያ፤ ምንም እንኳን ኢየሱስ ብዙኃኑን መፈወስና ማስተማር ባይተውም በአገልግሎቱ መጨረሻ ዓመት ዋና ሥራው ሐዋርያትን ማስተማር ነበር። በአንድ በኩል ሐዋርያቱ ለክብር የሚያበቃቸውን መንገድ ይዘው ሲጓዙ፥ በሌላ በኩል በስደት፥ በመከራና በሞት ውስጥ እንኳን ሳይቀር ማለፍ እንዳለባቸው ማስተዋል ነበረባቸው።

ጸሎት፤ የመንግሥቱ ሥራ የሚያመጣብህን መሥዋዕትነትና መከራ ለመቀበል ዝግጁ እንድትሆን ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ሀ) ጴጥሮስ ስለ ክርስቶስ በእርግጠኝነት ምን መሰከረ (ቍ.16)? ለ) ያልተረዳው ነገርስ ምን ነበረ (ቍ.21-27)?

2. የኢየሱስ ዕቅድ ጴጥሮስን አስመልክቶ በቤተ ክርስቲያኑና በመንግሥቱ ውስጥ ምን ነበረ (ቍ.17-19)? ኢየሱስ ስለ ጴጥሮስ ተከታይ (ተተኪ) እዚህ ላይ አንድ ነገር ተናገረን?

3. ሰው ክርስቶስን ለመከተል ምን ያስፈልገዋል (ቍ.24)?

4. ሰው ክርስቶስን እንዲከተል ኢየሱስ ምን ማበረታቻ ሰጠ (ቍ.25-28)?

5. ለክርስቶስና ለወንጌሉ ስትል የራስህን ፍላጎት ምን ያህል ክደሃል፥ መከራንስ እንዴት ትቀበላለህ?

ማስገንዘቢያ፤ መሥዋዕትነት ክብርን ይቀድማል። ሳይሞት የሚሞት ሲሞት አይሞትም (ቍ.25)።

ማስታወሻ፤

ቍ.18 ዓለት፤ አንዳንድ ሊቃውንት ቃሉ ጴጥሮስ የሰጠውን ምስክርነት (ቍ.16)፥ ሌሎች ክርስቶስ ራሱን (1ቆሮንቶስ 3፥11)፥ ሌሎችም ጴጥሮስ እንደ ሐዋርያት መሪ ተደርጎ መሾሙን ያመለክታል እያሉ ይተረጕሙታል (ኤፌሶን 2፥20)።

ቍ.19 የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎች፤ ጴጥሮስ በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ኀላፊነት ነበረውና በተሰጠው ሥልጣን ሰዎችን ወደ ዘላለም መዳን ጠራ (የሐዋርያት ሥራ 2፥37-41፤ 10፥44-48፤ 15፥7)።

የምታስረው ... የምትፈታው፤ እነዚህ ቃላት አንድ ድርጊት ያልተፈቀደ ወይም የተፈቀደ መሆኑን ያመለክታሉ። በሌላ አንቀጽ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር (ማቴዎስ 18፥15-18)።

ቍ.24 መስቀሉን ተሸክሞ ...፤ ሲባል በወንጌል ምክንያት የሚደርሰውን መከራ እስከ ሞት ድረስ መቀበል ማለት ነው።

## 32. <u>ሕግና ባለንጀራ</u>

<u>ሉቃስ 10፥25-37</u>



<u>መግቢያ</u>፤ ማቴዎስና ዮሐንስ ሐዋርያት እንደነበሩ፥ ማርቆስም በአካለ ሥጋ ኢየሱስን ያወቀ ወጣት እንደነበረ ይታሰባል። ሉቃስ የሐዋርያው ጳውሎስ ጓደኛ ነበረ። ይህ ደቀ መዝሙር ወንጌሉን የጻፈው የልዩ ልዩ ክርስቲያኖችን ምስክርነት መሠረት በማድረግ ነው (1፥1-4)፤ በወንጌሉም ውስጥ በሌሎች ወንጌላት ያልተጻፉ ብዙ የክርስቶስን የመጨረሻ አገልግሎት፥ ትምህርትና ተግባር በ9፥31-18፥14 ባሉት ክፍሎች ውስጥ አስፍሮአል።

<u>ጸሎት</u>፤ የዚህን ምሳሌ መልእክት በሥራ ላይ ማዋል እንድትችል ለምን።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. እንደ «ሕጉ» ሰው የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ምን ማድረግ አለበት (ቍ.25-27)?

2. ይህን የፈጸመ ሰው በዓለም ታሪክ ውስጥ የሚኖር ይመስልሃልን (ቍ.28)?

3. ሀ) በመንገድ ሲጣል፥ ለ) ካህኑና ሌዋዊው አልፈውት ሲሔዱ፥ ሐ) ሳምራዊው ሲቀርበው፥ መ) ሳምራዊው ሲረዳው የተደበደበው ሰው ምን የተሰማው ይመስልሃል?

4. ሰውዬውን ሳይረዱት ያለፉት፥ ሀ) ካህኑ፥ ለ) ሌዋዊው ምን የሚያመካኙ ይመስልሃል?

5. ሳምራዊውን ከካህኑና ከሌዋዊው የለየው ጠባይ ምን ነበር (ቍ.33)?

6. የሚገባህን ነገር ስላለማድረግህ ምን ታመካኛለህ?

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ «ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው» ያዕቆብ 2፥26።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.27</u> በመጽሐፍ ቅዱስ ገጽ ግርጌ የሚገኘውን ጥቅስ መግለጫ ተመልከት።

<u>ቍ.32 ሌዋዊ</u>፤ ካህናትን በቤተ መቅደስ ሥርዓት የማገልገል ዕድል ለሌዊ ወገን ሰዎች ተሰጥቶ ነበር።

<u>ቍ.33 ሳምራዊ</u>፤ ሳምራውያን በአይሁድ ዘንድ ይነቀፉ ነበር፤ በመሆኑም የሕግ መምህሩ እንኳን ይህን የተጠላ ስም በአንደበቱ ለመጥራት ፈቃደኛ አለመሆኑ በቍ.37 ይታያል።

## 33. መልካም እረኛና በጎቹ

ዮሐንስ 10፥11-31



መግቢያ፤ መጽሐፍ ቅዱስ በኢየሱስ ክርስቶስና በደቀ መዛሙርቱ መካከል ያለውን ግንኙነት በብዙ ዓይነት ምሳሌ ይገልጣል። እስካሁን ድረስ ይህን አንድነት የተመለከትነው በንጉሥና በዜጋው መካከል ባለ ግንኙነት ነው። በዚህ ጥናት ደግሞ በሌላ መንገድ እንመረምረዋለን።

ጸሎት፤ ከክርስቶስ ጋር ያለህን ግንኙነት በይበልጥ እንድታስተውል ጌታን ለምን።

ንባብ፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. መልካም እረኛ ለበጎቹ ምን ያደርጋል (ቍ.11-17፡27-29)?

2. በጎቹስ ምንን ያውቃሉ (ቍ.14፡27)?

3. ይህ አንቀጽ በኢየሱስና በአባቱ መካከል ስላለው ግንኙነት ምን ያስረዳል (ቍ.15-18፡29፡30)?

4. አይሁድ በክርስቶስ ላይ ለምን ተነሡ (ቍ.19-26፡31)?

5. አንተ፥ ሀ) አሁን የክርስቶስ በግ መሆንህን፥ ለ) ለዘላለም ከበጎቹ አንዱ እንደምትሆን፥ እንዴት ለማወቅ ትችላለህ?

ማስታወሻ፤


ቍ.11 መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ታላቅነት ለማንጸባረቅ ብዙ ምሳሌዎች ቢሰጡም እንኳን በቂ አይደሉም። በዚህ ወንጌል ደግሞ ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ (6፥35)፥ የዓለም ብርሃን (8፥12)፥ የበጎች በር (10፥7)፥ ትንሣኤ (11፥25)፥ መንገድ፥ እውነትና ሕይወት (14፥6) እና እውነተኛ የወይን ግንድ (15፥1)፥ ተብሎ ተገልጦአል።

ቍ.16 ሌሎች በጎች፤ ከአሕዛብ ወገን የሚገኙ ማለት ነው።

ቍ.30 እኔና አብ አንድ ነን፤ ኢየሱስ ይህን በማለቱ አብና ወልድ በመለኮትና በባሕርይ አንድ የሆኑ ሁለት አካላትመሆናቸውንይገልጣል።

## 34. ወደ መጨረሻው መቅረብ

ማቴዎስ 21፥1-17



መግቢያ፤ ኢየሱስ ከሦስት ዓመታት በላይ የፈጀውን ይፋ አገልግሎቱን ከፈጸመ በኋላ፥ የአይሁድ ባለሥልጣኖች እንደ መሲሕ (ክርስቶስ) እንዲቀበሉትና ዓቢይ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ አነሣሣቸው። እርሱም ወደፊት ሊደርስበት የሚችለውን እያወቀ ሁኔታውን እስከ መጨረሻው ይመራና ይቆጣጠር ነበር።

ራስን ማዘጋጀት፤ ዛሬ ስለ ኢየሱስ ማንነት፥ ሥራና ድንቅ ነገሮችም እንድታስተውል ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ኢየሱስ፥ ሀ) ወደ ኢየሩሳሌም በውርንጫ ላይ ተቀምጦ በመግባቱ (ቍ.1-6)፥ ለ) ቤተ መቅደስን በማንጻቱ (ቍ.11-13)፥ ሐ) ምስጋናን በመቀበሉ (ቍ.9፡15-17) ስለ ራሱ ምንን አመለከተ?

2. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱትን የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ዘርዝር። የግርጌውን ማስታወሻ ተመልከት።

3. በዚህ ቀን ስለ ክርስቶስ ከተሰጡ አስተያየቶች ቢያንስ ሦስቱን ጻፍ (ቍ.8-11፡14-17)።

4. ከነዚህ አስተያየቶች ወደ አንተ አስተሳሰብ የሚቀርበው የትኛው ነው?

ማስገንዘቢያ፤ ሀ) ዛሬ ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌሉ የሰዎች አስተያየት እንዴት እንደሆነ አሰላስል፥ ለ) ክርስቶስ በምድር ሳለ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት እያገናዘበ ለራሱ አገልግሎት እንዴት መመሪያ እንዳደረጋቸው አስብ።

ማስታወሻ፤

ቍ.9 ሆሣዕና፤ «አሁን አድን» ወይም «እግዚአብሔር አድነን» የሚለው ቃል ከፍ ያለ የሃይማኖት ስሜት መግለጫ ነው።

ለዳዊት ልጅ፤ ጥናት 12ን ተመልከት።

35. <u>የመጨረሻው እራት</u> ሉቃስ 22፥7-23



<u>መግቢያ</u>፤ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ከገባና ቤተ መቅደሱን ካነጻ በኋላ በየቀኑ በሕዝብ ፊት እያስተማረ ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ተከራከረ። (ሉቃስ 20፥1-47፤ 21፥37:38)፥ እንዲሁም ደቀ መዛሙርቱ ወደ ፊት በዓለም ላይ ስለሚያከናውኗቸው ዋና ዋና ነገሮች አስተማረ (ሉቃስ 21፥5-36)። በክርስቶስ ላይ የሃይማኖት መሪዎች ተቃውሞ እየበዛ ሄደ፤ ይሁዳም ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ከእነርሱ ጋር ተስማማ (ሉቃስ 22፥1-6)። በሐሙስ ዕለት ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የአይሁድን የፋሲካ እራት በላ።

<u>ራስን ማዘጋጀት</u>፤ ክርስቶስ ይህን የመጨረሻውን የፋሲካ እራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሲበላ ዓላማው ምን እንደሆነ እንድታስተውል ጸልይ።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ሀ) ኢየሱስ እራቱን እንዴት አዘጋጀ (ቍ.7-13)? ለ) ለምን በስውር አዘጋጀው?

2. በዚህ እራት ግብዣ ላይ ኢየሱስ ምን ዓይነት ስሜት ይታይበት ነበረ (15:17:19:21:22)?

3. ሀ) ኢየሱስ እንጀራውን ምን አደረገ? ለ) ስለ እንጀራውስ ምን አለ? ሐ) ደቀ መዛሙርቱ ወደፊት ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

4. ሀ) ኢየሱስ ስለ ጽዋ ምን አለ? ለ) «ደም»፥ ሐ) «አዲስ ኪዳን» በማለቱ ያመለከተው ምንድን ነው?

5. ለቅዱስ ቍርባን (ለጌታ እራት) ራስህን እንዴት ታዘጋጃለህ?

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና ሥራውን የፈጸመው በመሞቱ ነበረ።

<u>ማስታወሻ</u>፤

1 ቆሮንቶስ 11፥23-26 የቅዱስ ቍርባንን ሥርዓት ስለ መደንገግ ይበልጥ ይገልጣል።

<u>ቍ.8 ፋሲካ</u>፤ ጥናት 7ን ተመልከት።

<u>ቍ.17 ጽዋንም ተቀበለ ...</u>፤ ከአይሁድ ፋሲካ ሥርዓቶች አንዱ።

<u>ቍ.20 አዲስ ኪዳን</u>፤ ከአዲስ ኪዳን በፊት ብሉይ ኪዳን ከእግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ተመሥርቶ ነበር። ዘጸአት 24፥6-8ን ተመልከት።

<u>ደም</u>፤ ቃሉ ለኃጢአት ይቅርታ የሚሆንን የመሥዋዕት ሞት ያመለክታል። ኤፌሶን 1፥7።

## 36. መንገዱና አጽናኙ

መግቢያ፤ የፋሲካን እራት ከበሉና የአስቆሮቱ ይሁዳ ከቤቱ ከወጣ በኋላ (ዮሐንስ 13፥27-30) ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የመጨረሻ ትእዛዛትን ሰጠ።



ጸሎት፤ በዚህ አንቀጽ የሚገኙትን አስገራሚ የተስፋ ቃላት ተረድተህ በሕይወትህ በሥራ ላይ እንድታውላቸው ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. የክርስቶስ ተከታዮች የመጨረሻ መኖሪያ እንዴት ያለ ነው (ቍ.1-6)?

2. ወደዚያ የሚያደርሰው መንገድ የትኛው ነው? ሌላ መንገድ አለ (ቍ.4-11)?

3. በዚህ መንገድ የሚራመደው «መናኝ» ሕይወቱ እንዴት ያለ ነው (ቍ.12-27)?

4. መንፈስ ቅዱስ፥ ሀ) ከአብ፥ ለ) ከወልድ፥ ሐ) ከደቀ መዛሙርቱ፥ መ) ከዓለም ጋር ያለውን ግንኙነት አብራራ።

ማስገንዘቢያ፤ በእግዚአብሔርና በክርስቶስ ላይ የተጣለ እምነት ብስጭትን፥ ጭንቀትንና ፍርሃትን ያስወግዳል (ቍ.1:27)።

ማስታወሻ፤


ቍ.12 ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፤ በወንጌል ስብከት የሚሆነውን የአሕዛብን መመለስ የሚያመለክት ይመስላል።

ቍ.16 ሌላ አጽናኝ፤ አብንና ወልድን በአካል፥ በክብርና በሥራ የሚተካከል፤ መንፈስ ቅዱስ፤ እርሱ ሁሉን ለሐዋርያት የሚያስተምርና ክርስቶስ የነገራቸውን ሁሉ የሚያሳስብ ነው (ዮሐ.14፥26፤ 15፥26)።

ቍ.18 መሞቱን ያመለክታል።

## 37. እስራትና ፍርድ

ማቴዎስ 26፥47-68



መግቢያ፤ ኢየሱስ ዋናውን ሥራ የፈጸመው በመሞቱ ስለሆነ አራቱ ወንጌላውያን ሰፋ ያለውን ክፍል ለሕማማቱ ይሰጣሉ። በታሪካቸው ብዙ የዝርዝር ልዩነት ቢገኝም አራቱም ዋና ዋና ድርጊቶችን በጽሑፋቸው አስፍረዋል።

ከእራቱ በኋላ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ (ከይሁዳ በስተቀር) ከኢየሩሳሌም ወጥተው የቄድሮንን ወንዝ ሸለቆ ከተሻገሩ በኋላ በደብረ ዘይት ተራራ ዳር ወደ ነበረው ጌቴሴማኒ ወደሚባል አትክልት ግቢ ገቡ። እዚያም ደቀ መዛሙርቱ ተኝተው ሲያንቀላፉ ሳሉ ኢየሱስ ጸለየ (ማቴዎስ 26፥36-46)።

ራስን ማዘጋጀት፤ የክርስቶስን አርአያ ለመከተል ኃይልን እንድትቀበል ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ኢየሱስ፥ ሀ) ለይሁዳ፣ ለ) ለጴጥሮስ፥ ሐ) ለሕዝብ ሲናገር ዓላማው ምን ነበረ (ቍ.52-56)?

2. ኢየሱስ ወደ ሞት ሲቀርብ መመሪያው ምን ነበረ (ቍ.54-56)?

3. የኢየሱስንና የቀያፋን አካሔድ አነጻጽር (ቍ.57-68)።

4. ለቀያፋ የተሰጠው የክርስቶስ መልስ ምንን ያሳያል (ቍ.64)?

5. ኢየሱስ በምን ክስ መሠረት ለሞት ተዳረገ?

ማስገንዘቢያ፤ ኢየሱስ ክፉ ቃል ሳይናገር ራሱን እየገዛ ሕገ ወጥ ነገርን ሁሉ ታገሠ።

ማስታወሻ፤

ቍ.47 ይሁዳ፤ 26፥14:16:21-25ን ተመልከት።

ቍ.51 አንዱ...፤ ጴጥሮስ መሆኑ በዮሐንስ 18፥10 ተገልጦአል።

ቍ.56 ዘካርያስ 13፥7ን ተመልከት።

ቍ.61 ይህ ክስ በዮሐንስ 2፥19-22 የሚገኘውን ትምህርት ካለማስተዋላቸው የተነሣ ተፈጠረ።

ቍ.63 ማቴዎስ 16፥16:20ን ተመልከት።

ቍ.64 የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ፤ መዝሙር 109(110)፥1፤ ዳንኤል 7፥13:14ን ተመልከት።

ማቴዎስ 27፥24-44

## 38. ክህደትና ስቅለት



መግቢያ፤ በዚያ ዘመን በሀገሪቱ የማናቸውም ሰው የሞት ፍርድ የሚፈጸመው ሮማዊ አገረ ገዥ ካጸደቀው በኋላ ነበርና የአይሁድ ባለ ሥልጣኖች ኢየሱስን ወደ ጲላጦስ አደረሱት። ጲላጦስም ኢየሱስ በሕግ በኩል ጻድቅ መሆኑን ተረዳ፥ ነገር ግን አይሁድ ቅር እንዳይላቸው ፈራ።

ጸሎት፤ ክርስቶስ በአንተ ፈንታ መሞቱን ልብ እንድታደርግ ለምን።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ በጥንቃቄ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ ዘርዝር።

---

---

---

2. ሀ) በኢየሱስ ላይ እነማን አፌዙ? ለ) በአንተ አስተሳሰብ ለምን እንደዚህ አደረጉ?

---

---

---

3. ሀ) ከበርባን (ቍ.26)፥ ለ) ከስምዖን ታሪክ (ቍ.32) ምን መንፈሳዊ ምሳሌ ታገኛለህ?

---

---

---

---

4. ኢየሱስ ተሰቅሎ ሲታይህ ምን ይታሰብሃል? ምንስ ይሰማሃል?

---

---

---

ማስገንዘቢያ፤ «ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፥ መከራን ሲቀበል ጻድቅ ፈራጅ በሆነው አምላክ ተስፋ አደረገ እንጂ አልዛተም» 1ጴጥሮስ 2፥23።

ማስታወሻ፤

ቍ.26 በርባን፤ ቍ.15-21ን ተመልከት።

ቍ.27 ጭፍራው፤ 360 ወታደሮች የነበሩበት የሮም ጦር ሠራዊት ክፍል።

ቍ.35 መዝሙር 21(22)፥18ን ተመልከት።

ቍ.37 ይህ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ ነው፤ ሮማውያን በሚገዙአቸው ሕዝቦች ሃይማኖት ላይ ብዙ ጊዜ ተጽዕኖ አላደረጉም። በዚህ ምክንያት የአይሁድ መሪዎች በክርስቶስ ላይ ያቀረቡት ክስ ፖለቲካ ነክ ነበረ፥ ፖለቲካ ነክ ባይሆን ግን ጲላጦስ እንደማይቀበለው ያውቁ ነበረና። ቍ.1:2:29:42ን ተመልከት።

## 39. ሕማምና ሞት

ማቴዎስ 27፥45-66



መግቢያ፤ ኢየሱስ በዕለተ ዓርብ በሦስት ሰዓት ተሰቀለ (ማርቆስ 15፥25)። በመጀመሪያ ብዙ ሰዎች አፌዙበት፥ በኋላ ግን ሁሉንም ከፍተኛ የመጨነቅ፥ የመደናገጥና የመሸበር ስሜት ዋጣቸው።

ጸሎት፤ የልጁን ስቅለት ምክንያት እንድታስተውል እግዚአብሔርን ጠይቅ።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. በክርስቶስ ሞት ወቅት የታዩት አራቱ የተለያዩ ክሥተቶች ምንድን ናቸው (ቍ.45:51-53)?

2. ኢየሱስ በሕይወቱ የመጨረሻ ደቂቃዎች ያደረገውን በዝርዝር ግለጥ (ቍ.46-50)።

3. ክርስቶስ በፈቃዱ እንደሞተ በምን ይታወቃል (50፤26፥53-54)?

4. ኢየሱስ እንደሞተ ሲያውቁ፥ ሀ) መቶ አለቃው (ቍ.54)፥ ለ) መግደላዊት ማርያምና ሌሎቹ ሴቶች (55:56:61)፥ ሐ) የአርማትያሱ ዮሴፍ (ቍ.57-60)፥ መ) ጲላጦስ (ቍ.58)፥ ሠ) የአይሁድ ባለ ሥልጣኖች (ቍ.62-66) ምን አደረጉ?

5. በቍ.46 የሚገኘውን የኢየሱስ ጩኸት እንዴት ትረዳዋለህ?

ማስገንዘቢያ፤ «እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ» 1ጴጥሮስ 2፥24።

ማስታወሻ፤

ቍ.46 ኢየሱስ ሕማሙን ለመግለጥ የመዝሙረኛውን 21(22)፥1 ቃላት ጠቀሰ። ሕማሙ ከስቅለቱ ብርታት ብቻ ሳይሆን ከዚህ በበለጠ በተሸከመው የአዳም ልጅ ዕዳና ከአባቱ በመለየቱ ጭምር ነበር።

ቍ.50 ነፍሱን ተወ፤ ዮሐንስ 10፥17:18ን ተመልከት።

ቍ.51 የቤተ መቅደስ መጋረጃ...ተቀደደ፤ ይህም ኢየሱስ በመሞቱ የብሉይ ኪዳንን የመሥዋዕት ሥነ ሥርዓት ሁሉ ፈጽሞ አሮጌ እንዳደረገውና ወደ እግዚአብሔር አዲሱን መንገድ እንደከፈተ አመለከተ። በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር መኖሪያ ምልክት ወደ ሆነው ታቦት መንበር የገባ ብቸኛ ሊቀ ካህናት ነበር (ዕብራውያን 9፥6-8)።

ቍ.52:53 አያሌ አማኞች ከሞት መነሣት የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ታላቅ የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ያበሥሩ ይመስላል።

## 40. ድልና ታላቁ ተልዕኮ



**መግቢያ፤** ሴቶቹ የኢየሱስን መቀበር ካዩ በኋላ በሰንበት ቀን (ቅዳሜ) አረፉ።

**ጸሎት፤** ሴቶቹና ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን እንደገና ሲያዩ የድንጋጤና የደስታ ስሜት ዋጣቸው፤ የደስታቸው ተካፋይ እንድትሆን ጸልይ።

**ንባብ፤** አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

**ጥያቄ፤**

1. ሀ) ጠባቂዎች ምን አዩ (ቍ.2-4)? ለ) ምንስ አደረጉ (ቍ.11-15)?

2. ሀ) ሴቶቹ ምን አዩ? ለ) ምንስ አደረጉ (ቍ.5-10)?

3. በገሊላ ምን ሆነ (ቍ.16-18)?

4. አሁን የኢየሱስ ሥልጣን ምንድን ነው (ቍ.18)?

5. ሀ) ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ያዘዛቸውን በዝርዝር ግለጥ (ቍ.19-20)፥ ለ) ምንስ ተስፋ ሰጣቸው (ቍ.20)?

6. የጌታችንን ታላቅ ተልእኮ ለመፈጸም ምን እያደረግህ ነው?

**ማስገንዘቢያ፤** የኢየሱስ ትንሣኤ ዋና ማረጋገጫ (ማስረጃ) የተከታዮቹ ለታላቁ ተልዕኮ መታዘዝ ነው።

**ማስታወሻ፤**


**ቍ.6 እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና፤** 16፥21፤26፥32ን ተመልከት።

**ቍ.10 ለወንድሞቼ፤** 12:49:50ን ተመልከት።

**ቍ.16 ወደ ገሊላ፤** ማቴዎስ ይህን ስብሰባ እንደ ኢየሱስ የአገልግሎት አክሊል ይቈጥረዋል።

**ቍ.19 አሕዛብን ሁሉ፤** የኢየሱስ ይፋ አገልግሎት በአይሁድ ዘንድ ብቻ ነበረ (10፥5:6)፥ አሁን ግን ተልእኮው ለዓለም ሁሉ ነው።

# ክፍል 3 የድል ብሥራት



«ጌታ ሆይ ማን ነህ?»


| | | | ገጽ |
|---|---|---|---|
| **የቤተክርስቲያን ታሪክ** | | | |
| 41. | የሐዋርያት ሥራ 1፥1-14 | የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ | 47 |
| 42. | የሐዋርያት ሥራ 2፥1-24 | የመንፈስ ቅዱስ መውረድ | 48 |
| 43. | የሐዋርያት ሥራ 2፥32-47 | የቤተ ክርስቲያን አኗኗር | 49 |
| 44. | የሐዋርያት ሥራ 9፥1-22 | የአሕዛብ ሐዋርያ | 50 |
| 45. | የሐዋርያት ሥራ 10፥30-48 | ከአሕዛብ የመጀመሪያው ክርስቲያን | 51 |
| 46. | የሐዋርያት ሥራ 16፥11-40 | ወንጌል በአውሮፓ | 52 |
| 47. | የሐዋርያት ሥራ 19፥1-22 | ወንጌል በኤፌሶን | 53 |
| 48. | የሐዋርያት ሥራ 28፥11-31 | ወንጌል በሮሜ | 54 |
| **የቤተ ክርስቲያን እምነት** | | | |
| 49. | 1 ቆሮንቶስ 15፥1-22 | የወንጌል መልእክት | 55 |
| 50. | ኤፌሶን 1፥1-14 | የእግዚአብሔር ዕቅድ | 56 |
| 51. | ኤፌሶን 2፥1-10 | የሰው ደኅንነት | 57 |
| 52. | ሮሜ 5፥1-11 | የደኅንነት ውጤት | 58 |
| 53. | ሮሜ 8፥1-17 | የቅድስና መንገድ | 59 |
| 54. | ሮሜ 8፥18-39 | የአማኝ ዋስትና | 60 |
| **የክርስቲያን ሕይወት** | | | |
| 55. | ሮሜ 12 | አማኙና የግል ሕይወቱ | 61 |
| 56. | ቆላስይስ 3፥1-17 | አማኙና ቤተ ክርስቲያኑ | 62 |
| 57. | ኤፌሶን 5፥15-6፥4 | አማኙና ቤተ ሰቡ | 63 |
| 58. | 1 ዮሐንስ 1፥5-2፥6 | አማኙና መተላለፉ | 64 |
| 59. | ዕብራውያን 12፥1-17 | አማኙና ጠባቡ መንገድ | 65 |
| 60. | የዮሐንስ ራእይ 22፥1-5:12-21 | አማኙና ተስፋው | 66 |

## 41. የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ





መግቢያ፤ ሉቃስ ወንጌሉን ከጻፈ በኋላ የቤተ ክርስቲያንን መጀመርና መስፋፋት «የሐዋርያት ሥራ» በተባለው መጽሐፍ ይተርካል። የዚህ መጽሐፍ መነሻ ሀሳብ በምዕራፍ አንድ ቍጥር ስምንት ይገኛል።

ጸሎት፤ እግዚአብሔር ለዓለም፥ ለቤተ ክርስቲያንና ላንተ ያለውን ዕቅድ ለማስተዋል እንድትችል እግዚአብሔርን ጠይቅ።

ንባብ፤ የተሰጠውን አንቀጽ ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. በትንሣኤውና በዕርገቱ መካከል ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ሠራ (ቍ.1-3)?

2. ለሁለተኛው ጊዜ እስኪመጣ ድረስ የክርስቶስ ዓላማ (ዕቅድ) ለተከታዮቹ ምንድን ነው (8)?

3. ይህ ዓላማ እንዴት ይፈጸማል (4:5:8)?

4. አንተ የክርስቶስ ምስክር ስትሆን በዓላማው ውስጥ፥ ሀ)በአጭር ጊዜ፥ ለ) በሕይወትህ ዘመን ሁሉ የአንተ ፈንታ ምን እንደሆነ ታውቃለህን? የዓላማህን (የዕቅድህ) ቅደም ተከተል በጥራት አቅርብ።

«እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና» 2 ጢሞ.1፥7።

ማስታወሻ፤

ቍ.5 በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ፤ ማር. 1፥7-8ን ተመልከት።

ቍ.6 ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ሐዋርያት ከሮም አገዛዝ የእስራኤል ሕዝብ ነፃ ይወጣል ብለው ያስቡ ነበር።

ቍ.8 ይሁዳ፤ በኢየሩሳሌም ዙሪያ የምትገኝ ክፍለ ሀገር።

ሰማርያ፤ በይሁዳና በገሊላ መካከል የምትገኝ ክፍለ ሀገር። የሰማርያ ሕዝብ የተቀየጠ ይሁን እንጂ ይሁዲነትን ይከተል ነበር። በ32ኛው ጥናት የሚገኘውን ማስታወሻ ተመልከት።

ቍ.9 ደመና፤ በ9ኛው ጥናት የሚገኘውን ማስታወሻ ተመልከት።

ቍ.10 ሁለት ሰዎች፤ መላእክት።

ቍ.14 የኢየሱስ እናት ማርያም፤ ከዚህ ጥቅስ በኋላ በአዲስ ኪዳን በስም ተጠቅሳ አትታይም።

## 42. <u>የመንፈስ ቅዱስ መውረድ</u>

**<u>የሐዋርያት ሥራ 2፥1-24</u>**



<u>መግቢያ</u)፤ በዓለ ኀምሳ በግሪክ ቋንቋ ጰንጠቆስጤ የሚባለው ሲሆን፥ ከአይሁድ ሦስት ታላላቅ በዓላት አንዱና ከፋሲካ ኀምሳ ቀን በኋላ በሰንዴ አዝመራ ወቅት የሚከበር በዓል ነው። ከክርስቶስ ተከታዮች 120 ያህሉ ከዕርገቱ ከ10 ቀን በፊት ጀምረው እስከ በዓለ ኀምሳ ዕለት ድረስ በጸሎት ይተጉ ነበር (1፥14:15)።

<u>ጸሎት</u>፤ የዚህ ዕለት ክሥተት ምን ለውጥ እንዳመጣና ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን እንደገለጠ ማስተዋል እንድትችል ጠይቅ።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ያረጋገጡትን ሦስት ምልክቶች ዘርዝር (ቍ.1-4)?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

2. ለበዓሉ ወደ ኢየሩሳሌም የመጡት ሕዝቦች የሆነውን ነገር አይተው ምን አሉ (5-13)?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

3. ጴጥሮስ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ከየትኛው ትንቢት ጋር አመሳከረው (16-21)? ለምንስ ማመሳከር ፈለገ?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

4. ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በፊት መከናወን የነበረባቸውን ዐበይት ነገሮች ዘርዝር (22-24)?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

5. በአንተ ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ምን እየሠራ ነው? መልስህን ከ2፥17:18 እና ከ1፥8 ጋር አነጻጽር።

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

እግዚአብሔርን ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታው እያመሰገንህ በየዕለቱ ኃይሉ በአንተና በአንተም በኩል ለሌሎች በምልዓት እንዲገለጥ ጸልይ።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.1 በዓለ ኀምሳ</u>፤ በቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ «ጰራቅሊጦስ» ማለት «አጽናኝ» በሚል ስም ይታወቃል ዮሐንስ 14፥16ን ተመልከት።

<u>ቍ.5 አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር</u>፤ ብዙዎቹ ለዓመት በዓሉ መጥተው ነበር።

<u>ቍ.14 ጴጥሮስ</u>፤ 31ኛውን ጥናት ተመልከት።

## 43. የቤተ ክርስቲያን አኗኗር



መግቢያ፤ ጴጥሮስ ስብከቱን በመቀጠል ንጉሥ ዳዊት በግምት ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት የክርስቶስን ትንሣኤ (ቍ.25-31) እና ዕርገት (ቍ.33-36) እንደተነበየ አሳየ።

ጸሎት፤ የዚህን ስብከት ዋና ትምህርትና ውጤት እንድታስተውል ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. የመንፈስ ቅዱስ መውረድ በግልጥ ያረጋገጠው ነገር ምንድን ነው (ቍ.33:36)?

2. አንድ ሰው ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ሲሰማ ማድረግ የሚገቡትን ሁለት ነገሮች ጻፍ (38)።

3. እነዚህን ቢያደርግ የሚቀበላቸውን ሁለት ስጦታዎች ለይተህ አመልከት (38)።

4. ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ጠባያት ቢያንስ አሥሩን ዘርዝርና ከነዚህ በተለይ የአንተ ቤተ ክርስቲያን ወይም መንፈሳዊ ማኅበር ጠባያት የሆኑትን ለይተህ አስምርባቸው (41-47)።

በአንተና በቤተ ክርስቲያንህ መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚሠራ አሰላስል።

ማስታወሻ፤

ቍ.33 ከዚህ ጥቅስ ሥላሴ (አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ) እንዴት እንደሚሠሩ አስተውል። ማርቆስ 1፥10:11፤ ማቴዎስ 28፥19ን ተመልከት።

ቍ.34:35 ጌታ (እግዚአብሔር አብ) ጌታዬን (እግዚአብሔር ወልድ - መሲሕ)።

ቍ.38 በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ ሉቃስ ይህን ሲል የጴጥሮስን ስብከት በአጭሩ መግለጡ እንጂ፥ ሐዋርያት በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ በኢየሱስ የታዘዙትን ጥሰዋል ማለቱ አይደለም ማቴ.28፥18-19።

## 44. <u>የአሕዛብ ሐዋርያ</u>





<u>መግቢያ</u>፤ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እያደገ ሲሔድ የአይሁድ ሃይማኖት ባለ ሥልጣኖች ታላቁን የወንጌል ሰባኪ እስጢፋኖስን በድንጋይ እስከ መግደል ድረስ አዲሱን ማኅበር ተቃወሙ። ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላም ማሳደዳቸውን በዕቅድ ተያያዙት። ዋናው አሳዳጅም በኋላ «ሐዋርያው ጳውሎስ» የተባለው ሳውል ነበር። ሳውል በትውልድ አይሁዳዊ ቢሆንም በዜግነት ሮማዊ በመሆኑ ባለሙሉ መብት ዜጋ ሲሆን የሕግ ሊቅና ጠንካራ ፈሪሳዊም ነበር።

<u>ጸሎት</u>፤ ከጳውሎስ ታሪክ ሰው ወደ ክርስቶስ እንዲመለስ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ እንድታስተውል ለምን።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ክርስቶስ የሳውልን የሕይወት በር እንዴት አንኳኳ? በደማስቆ ጉዳና የሆነውን በአጭሩ ግለጥ (ቍ.3-6)።

2. ክርስቶስ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ሲገለጥለት ሳውል ምን ሆነ(7-9፡11)?

3. ጌታ ለሐናንያ ስለ ሳውል ምን አለው (10-16)?

4. ሐናንያ ለሳውል ምን አደረገለት (17፡18)?

5. የራስህን የሕይወት ለውጥ ከጳውሎስ መመለስ ጋር አነጻጽር።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ ክርስቲያን የዳነው ምስክር ለመሆን ነው።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.2 ደማስቆ</u>፤ በሰሜን አቅጣጫ 225 ኪሎ ሜትር ከኢየሩሳሌም የሚርቅና የአንድ ሳምንት ጉዞ የሚፈጅ፥ ከጥንት ጀምሮ የሦርያ መናገሻ ከተማ ነው።

<u>ቍ.5 የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ</u>፤ ኢየሱስ ከተከታዮቹ ጋር ራሱን አንድ ያደርጋል። በአይሁድ ሕግ መሠረት ሰው ከመቀጣቱ በፊት ለተከሰሰበት መልስ የመስጠት መብት ስለ ነበረው፥ ሳውል ብዙ ጊዜ የተሰደዱትን ሰዎች ምስክርነት ሰምቶ ነበር።

<u>ቍ.11 ጠርሴስ</u>፤ በአሁኑ ደቡብ ቱርክ የነበረ መጠነኛ ከተማ፤ ካርታን ተመልከት።

## 45. ከአሕዛብ የመጀመሪያ ክርስቲያን



መግቢያ፤ በመጀመሪያ ወንጌል ለአይሁድ ብቻ ተሰበከ። እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ ወንጌልን አይሁድ ላልሆኑትና አረማውያን ለሚባሉት አሕዛብ የመስበክ ጊዜ ደረሰና ለጴጥሮስ ራእይ ታየው። እርሱም በእግዚአብሔር አመራር ተገርሞ፥ ወደ አረማዊ ቤት በመግባት ሊፈታተነው የሚችለውን የመርከስ ስሜት አሸንፎ የቆርኔሌዎስን ጥሪ ተቀበለ።

ራስን ማዘጋጀት፤ በልዩ ልዩ ሕዝብ መካከል በሃይማኖት፥ በነገድ፥ በባህል ወዘተ እያሰብህ ስለሚታየው መለያየት በማጤን የዚህን ታሪክ ትምህርት እንድታስተውል ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ጴጥሮስ በስብከቱ ያተኰረባቸውን ዐበይት ነጥቦች ዘርዝር (ቍ.34-43)።

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

2. እግዚአብሔር በሰዎች መካከል አለማዳላቱን እንዴት ገለጠ (44-47)?

_______________________________________________

_______________________________________________

3. ጴጥሮስ ይህን አይቶ ምን አደረገ (47:48)? 11፥15-18ን ተመልከት።

_______________________________________________

_______________________________________________

4. በነገድ፥ በጐሣ፥ በሃይማኖትና በባህል ከአንተ ከሚለዩት ሕዝቦች ጋር ያለህ ግንኙነት እንዴት ነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

ማስገንዘቢያ፤ እውነተኛ ክርስቲያን የሚታወቀው ወንጌሉን በማመኑ፥ መንፈስ ቅዱስን በመቀበሉ፥ በመጠመቁና በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል በመገኘቱ ነው።

ማስታወሻ፤

ቍ.30 ቆርኔሌዎስ፤ የሮሜ ጦር መኰንን ሳለ ያለ ግዝረት የአይሁድ ሃይማኖት ተከታይ ነበረ። 10፥1:2ን ተመልከት።

ቍ.32 ኢዮጴ፤ በታላቁ ባሕር ዳር የነበረ ወደብ። ካርታውን ተመልከት።

ቍ.34 ጴጥሮስ፤ 31ኛውን ጥናት ተመልከት።

ቍ.38 እግዚአብሔር...ኢየሱስን...ቀባው፤ ማር.1፥10:11ን ተመልከት።

ቍ.47 እነዚህ እንደ እኛ...የተቀበሉ፤ በጰንጠቆስጤ ቀን ማለቱ ነው።

ቍ.48 በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ፤ የ43ኛውን መጨረሻ ማስታወሻ ተመልከት።

## 46. ወንጌል በአውሮፓ

የሐዋርያት ሥራ 16፥11-40



መግቢያ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ ከተመለሰ በኋላ በትውልድ አገሩ በጠርሴስ መከራን እየተቀበለ ለአሥር ዓመታት ወንጌልን ሰበከ። ከዚያም በአንጾኪያ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ለአንድ ዓመት ካገለገለ በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለሦስት ታላላቅ የወንጌል ጉዞዎች ላከችው። በመጀመሪያ ጉዞው ከበርናባስ ጋር በገላትያ ክፍለ አገር አብያተ ክርስቲያናትን አቋቋመ፤ በልስጥራን በድንጋይ ተወገረ። በሁለተኛው ጉዞ ከሲላስ፥ ከጢሞቴዎስና ከሉቃስ ጋር ወደ መቄዶንያ ተሻገረ።

ጸሎት፤ የጳውሎስን የወንጌል ማስፋፋት ዘዴ እንድታስተውል ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ሀ)የልድያን፥ ለ)የልጃገረዲቱን፥ ሐ)የወህኒ ጠባቂውን ጠባይና ሁኔታ ግለጥ።

2. እያንዳንዳቸው ወደ መዳን እንዴት ደረሱ?

3. ወንጌሉ ለቤተ ሰቦቻቸው ምን ለውጥ አመጣ?

ማስገንዘቢያ፤ «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ብዙ መከራን መቀበል አለብን»። የሐዋርያት ሥራ 14፥22።


ማስታወሻ፤

ቍ.13 አይሁድ የጸሎት ቤት (ምኵራብ) መሥራት ባይችሉም ልዩ ልዩ የማንጻት ሥርዓታቸውን መፈጸም በሚችሉበት ሥፍራ ይሰበሰቡ ነበር።

ቍ.31 አንተና ቤተ ሰቦችህም፤ 2፥39 እና 16፥35 ተመልከት።

## 47. ወንጌል በኤፌሶን

የሐዋርያት ሥራ 19፥1-22



መግቢያ፤ ጳውሎስና ጓደኞቹ ከፊልጵስዩስ ወጥተው ወንጌልን በተሰሎንቄ፥ በቤርያ፥ በአቴናና በቆሮንቶስ ሰበኩ። ከዚያም በመቀጠል ጳውሎስ ኢየሩሳሌምንና አንጾኪያን ከጐበኘ በኋላ፥ ሦስተኛውን ጉዞ ጀመረና፥ ወደ እስያ ዋና ከተማ ወደ ኤፌሶን ደረሰ።

ጸሎት፤ በወንጌል መሠረት ለመኖር ሁል ጊዜ ዝግጁ እንድትሆን ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ብኤፌሶን በጳውሎስ ስብከት ልባቸው የተነካ ሦስቱ ወገኖች እነማን ነበሩ (ቊ.1-10)?

2. እነዚህ «ደቀ መዛሙርት» ያላወቁትና የጐደላቸው ዐቢይ ነገር ምን ነበር (1-6)?

3. በኤፌሶን የኢየሱስን ስም ከፍ ከፍ ካደረጉት ምክንያቶች ቢያንስ አራቱን ግለጥ (6፤ 11-12፤ 13-17፤ 18-20)።

4. በኤፌሶን የነበረችውን ቤተ ክርስቲያንና የአንተን ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ አነጻጽር። በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ለሚገኘው ልዩነት ምን ምክንያት ልትሰጥ ትችላለህ?

ማስገንዘቢያ፤ የወንጌል መስፋፋት ከምእመናን ምስክርነት ጋር የተያያዘ ነው። የሐዋርያት ሥራ 8፥4ን ተመልከት።

ማስታወሻ፤

ቊ.3 በዮሐንስ ጥምቀት፤ ማርቆስ 1፥7:8ን ተመልከት።

ቍ.6 በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ፤ (2፥4፤ 10፥46ን ተመልከት)።
እግዚአብሔር አዲስ ሥራን ሲጀምር ሥራው የእርሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ልዩ ምልክቶችን ሰጠ።

## 48. <u>ወንጌል በሮሜ</u>

<u>የሐዋርያት ሥራ 28፥11-31</u>



<u>መግቢያ</u>፤ ጳውሎስ ሦስተኛውን የወንጌል ጉዞውን ጨርሶ ከአሕዛብ ምእመናን ለድሆች የተሰበሰበውን እርዳታ ለቤተ ክርስቲያን ለማስረከብ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። በዚያም በአይሁድ ተይዞ ሲከሰስ የሮሜ ዜግነት መብቱን በመጠቀም ለቄሣር ይግባኝ አለ። ፍርድ ሲጠባበቅ ሳለም ለኤፌሶን፥ ለፊልጵስዩስና ለቈላስይስ አብያተ ክርስቲያናት እንደዚሁም ለጢሞቴዎስ፥ ለቲቶና ለፊልሞና መልእክቶችን ጻፈ። ከዚህም በፊት በወንጌል ጉዞው ላይ ለሮሜ፥ ለቆሮንቶስ፥ ለገላትያና ለተሰሎንቄ አብያተ ክርስቲያናት ጽፎ ነበር።

<u>ጸሎት</u>፤ እስከ መጨረሻው ታማኝና ታጋሽ እንድትሆን እግዚአብሔርን ጠይቅ፡

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ጳውሎስ ከሮሜ ሊቀበሉት የወጡትን አማኞች ሲያይ ምን ተሰማው (ቍ.13-15)?

2. ጳውሎስ ወደ ሮሜ እንደ ደረሰ ባገኘው ዕድል እንዴት ተጠቀመ (16-31)?

3. የሚከተሉትን ነጥቦች መሠረት በማድረግ የሐዋርያው ጳውሎስን ታላቅነት አመልከት፥ ሀ) የወንጌል ሰባኪ፥ ለ) የቤተ ክርስቲያን መሥራች፥ ሐ) የትምህርተ መለኮት (ቲዎሎጂ) መምህር፥ መ) ጸሐፊ፡-

4. ወንጌልን ለማስፋፋት በምን ዓይነት ሁኔታ ተዘጋጅተህ ትገኛለህ?


<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ ምንም እንኳን ጳውሎስ ከዕቅዱ ውጭ ፍጹም ባልታሰበ መንገድ ወደ ሮሜ ቢወሰድም በጊዜውም አለጊዜውም ወንጌልን ከመስበክ አላቋረጠም። የሐዋርያት ሥራ 19፥21ን ተመልከት።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.13፡14</u> በሮሜ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደ ተቋቋመች መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ አይገልጥም። 2፥10፤ 18፥2ን ተመልከት።

<u>ቍ.31 እየሰበከ...ያስተምር ነበር</u>፤ የወንጌል ማስፋፋት ሥራ አልተቋረጠም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከያዕቆብ በስተቀር ስለ ጳውሎስም ሆነ ስለ ሌሎች ሐዋርያት የሕይወት ፍጻሜ አይገልጥም። የሐዋርያት ሥራ 12፥2ን ተመልከት።

## 49. የወንጌል መልእክት



መግቢያ፤ ሐዋርያት «የሐዋርያት ሥራ» በተባለው መጽሐፍ ወንጌልን እንዴት እንዳስተማሩ ተመልክተናል። አሁን ደግሞ የአዲስ ኪዳን ትምህርተ መለኮት (ቴዎሎጂ) ዋና መምህር በሆነው በሐዋርያው ጳውሎስ የተጻፉ ክፍሎችን በማንበብ የክርስትና እምነት ዋና ትምህርቶችን እንመረምራለን።

ጸሎት፤ ትክክለኛውን ወንጌል በእውነት እንድታስተውል ጌታን ለምን።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ በጥንቃቄ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ሀ)የወንጌል መልእክት በተለይ ማንን ያመለክታል (ቍ.3:4)? ለ)በክርስቶስ ሕይወት ዋና ድርጊቶች የትኞቹ ናቸው? ለምን?

2. «መጽሐፍ እንደሚል» የሚለው ሐረግ ለምን የተደጋገመ ይመስልሃል?

3. በጳውሎስ የተጠቀሱት የክርስቶስ ትንሣኤ ምስክሮች እነማን ናቸው (5-8)?

4. በትንሣኤ ያለማመን ውጤቱ ምንድን ነው (12-19)?

5. ስለ ትንሣኤ ስታስብ ምን የሕይወት መሠረት ታገኛለህ? መልስህን ከቍ.20-22 ጋር አወዳድር።

ማስገንዘቢያ፤ የክርስቲያን ተስፋ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ በሥጋ መነሣት የሚገኝ ትንሣኤ ነው።

ማስታወሻ፤

ቍ.5 ኬፋ፤ ከጴጥሮስ ስሞች አንዱ።

ቍ.6 ከ500 ለሚበዙት... ታየ፤ ይህ የሆነው ጌታችን ታላቁን ተልእኮ ሲሰጥ እንደነበረ ይታሰባል። ጥናት 40ን ተመልከት።

ቍ.7 ያዕቆብ፤ የጌታ ወንድም፥ ከ12ቱ ሐዋርያት መካከል ሳይሆን የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረ ሰው (የሐዋርያት ሥራ 1፥14፤ 12፥17፤ 15፥13፤ 21፥18)።

ቍ.22 በአዳም...በክርስቶስ፤ እነዚህ ሁለት የዓለም ሕዝብ ራሶች ከእነርሱ ጋር የተቈጠሩትን ሕዝቦች ማንነት በአድራጐታቸው ወስነዋል። ሮሜ 5፥12-21ን፥ በተለይም ቍ.15:17:19ን ተመልከት።

## 50. <u>የእግዚአብሔር ዕቅድ</u>

**<u>ኤፌሶን 1፥1-14</u>**



<u>መግቢያ</u>፤ ዓለምን በመፍጠር፥ አብርሃምንና ዘሩን በመምረጥ፥ ሕዝቡን ከግብጽ አውጥቶ መሲሕ እስኪመጣ ድረስ ቤተ እስራኤልን በመጠበቅ እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ፍጹም ባለ ሥልጣንና ገዥ መሆኑ በጠቅላላው የብሉይ ኪዳን ታሪክ ተረጋግጧል።

<u>ጸሎት</u>፤ እግዚአብሔር ስለ ሰው መዳን የገለጠውን ዓላማና ዕቅድ በይበልጥ እንድታስተውል ጌታን ለምነው።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር ለቅዱሳን (ቍ.1) ያደረጋቸው ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው (ቍ.3-5)?

2. የእግዚአብሔር ዕቅድ፥ ሀ) መነሻ (5:9:11)፥ ለ) ዓላማ (5-8:10-12) ምንድን ናቸው?

3. በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ድርሻ (ሥራ) ምንድን ነው (3-7:10:12)?

4. መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ምን ይሠራል (13-14)?

5. የአንተ ዓቢይ ዓላማ ለክርስቶስ የክብርና የምስጋና ዕቃ ሆነህ መገኘት ነውን (6:12)?

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ «የላከኝ (የአብ) ፈቃድ ከሰጠኝ ሁሉ አንድ እንኳ ሳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣ ነው» ዮሐንስ 6፥39።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.1 ቅዱሳን</u>፤ አማኞች ሁሉ በክርስቶስ ነፅተው ከክፉት ተለይተው ለእግዚአብሔር ስለሚቆሙ ቅዱሳን ይባላሉ።

<u>በክርስቶስ ኢየሱስ</u>፤ በእግዚአብሔር ፊት የአማኙን ሁኔታ የሚገልጥ በጳውሎስ እጅግ የተወደደ ሐረግ ቍ.3:4:7፤ 10:11:12:13ና በጥናት 49 ስለ 1 ቆሮንቶስ 15፥22 የሚገኘውን ማስታወሻ ተመልከት።

<u>ቍ.5 አስቀድሞ ወሰነን</u>፤ ይህ ውሳኔ እንደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ሰዎች ወደ መዳን የሚደርሱበትን መንገድ እንደደነገገ ያመለክታል።

<u>ቍ.7 ቤዛነት</u>፤ ቃሉ ዋጋን በመክፈል ሰውን ከባርነት ነፃ የማውጣትን ተግባር ያመለክታል።


<u>ቍ.13 ታተማችሁ</u>፤ የሐዋርያት ሥራ 2፥33፤ 19፥2-6ን ተመልከት።

## 51. የሰው ደኅንነት

መግቢያ፤ ይህ አንቀጽ ከውድቀት በኋላ ያለውን የሰውን ሁኔታና ሰውን ለማዳን እግዚአብሔር ያደረገውን ሥራ በግልጽ ያብራራል።

ጸሎት፤ ለእግዚአብሐር ጸጋ (ተገቢውን) ክብርና ምስጋና የሚሰጥ መንፈስ እንዲኖርህ ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።



ጥያቄ፤

1. ያለ ክርስቶስ የሚኖርን ሰው ሁኔታ የሚገልጡ ቢያንስ አምስት ሐረጎችን ጻፍ (ቍ.1-3)።

2. ሀ) እግዚአብሔር የጠፋውን ሰው ለማዳን የፈቀደበት ምክንያት ምን ነበር (4-5)? ለ) ከዚህ የተነሣ ምን አደረገ (4-7)? ሐ) የመጨረሻ ዓላማውስ ምንድን ነው (6:7)?

3. ሰው በራሱ ደኅንነትን ሊያገኝ የማይችልበት ምክንያት ምንድን ነው (1:2:8:9)?

4. ጸጋ፥ አዲስ ሕይወት፥ እምነትና ሥራ እንዴት እንደሚገናኙ ግለጥ (5:8-10)።

5. ከእግዚአብሔር ጸጋ ጀምሮ እስከ መልካም ተግባራትህ ድረስ በሕይወትህ ያለውን የእግዚአብሔርን ሥራ ለመዘርዘር ሞክር።

ማስገንዘቢያ፤ የወንጌልን ሀሳብ አጠቃልለው የያዙ ሦስት ቃላት :- «ነገር ግን እግዚአብሔር» (ቍ.4)።


ማስታወሻ፤

ቍ.2 በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ፤ ሰይጣን። 6፥12ን ተመልከት።

ቍ.10 ፍጥረቱ ... ተፈጠርን፤ እንደ «ፍጥረቱ»፥ «ሕይወት ሰጠን» (ቍ.5)ና «ዳግመኛ መወለድ» (ዮሐንስ 3፥3:5) ያሉት ሐረጎች በእግዚአብሔር የሚፈጸመውን ሰውን የመለወጥ ሥራ ያብራራሉ።

## 52. የደኅንነት ውጤት

ሮሜ 5፥1-11



መግቢያ፤ ኃጢአተኛ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ያለ ነውር መቆም እንዴት ይችላል? በሌላ አነጋገር ጻድቅ መሆን እንዴት ይችላል ወይም እንዴት ሊጸድቅ እንዴት ይችላል? እግዚአብሔር የትክክለኛነትን ሕግ ሳይጥስ ሰው ኃጢአትን እንዳልሠራ እንደ ፍጹም ጻድቅ ቈጥሮ ሊቀበለው እንዴት ይችላል? ይህ ጥናት ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።

ጸሎት፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሕዝቡ ያስገኘውን በረከት ሁሉ በሕይወትህ እንድታውቅ ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን ሁለት ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ሰው የእግዚአብሔርን ጽድቅ ከማግኘቱ በፊት ሁኔታው ምን ይመስላል (ቍ.1:6-10)?

______________________________

______________________________

______________________________

2. ሰው እንዴት ሊጸድቅ ይችላል (1:9)?

______________________________

______________________________

3. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱትን የጽድቅ ምልክቶች ዘርዝር። ከእነዚህ በሕይወትህ የተለማመድካቸውን ለይተህ አስምርባቸው።

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

4. የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያረጋግጡልን ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው (5:8)?

______________________________

______________________________

ማስገንዘቢያ፤ ሰው የሚጸድቅበትን መንገድ በትክክል መረዳት እግዚአብሔርን ወደ ማክበር ደረጃ መድረስን እንጂ በኃጢአት ቀንበር ሥር መውደቅን አያመጣም።

ማስታወሻ፤

ቍ.3-5 መከራ -› ትዕግሥት -› ፈተና (መጽናት) -› ተስፋ ይመራል። ክርስቲያን በተፈተነ መጠን የቅድስናን ባሕርይ ስለሚላበስና እግዚአብሔር ለእማኝ ያለውን ፍቅር በልቡ ስላፈሰሰ የማይጠፋ ተስፋ አለው።

ቍ.9 በደሙ አጸደቀን፤ ክርስቲያን በጸጋ፥ በደምና በእምነት ይጸድቃል (3፥24፤ 5፥9፤ 5፥1)፤ ማለት ከእግዚአብሔር በሚገኝ፥ በክርስቶስ ሞት ላይ በሚመሠረትና በእምነት አማካይነት በሚቈጠር ጽድቅ ያለ ነውር በእግዚአብሔር ፊት ይቆማል ማለት ነው። 2 ቆሮንቶስ 5፥21ን ተመልከት።

## 53. የቅድስና መንገድ



መግቢያ፤ ጳውሎስ «ጸደቀ፥ ጽድቅ፥ ጻድቅ» በተባሉት ቃላት ሲጠቀም አገባባቸው በፍርድ ቤት አጠቃቀም ዓይነት ነው። ሐዋርያው እግዚአብሔር ሰውን አጸደቀ ሲል አማኙ ከበደል ነፃ፥ በሕግ በኩል ምንም የሌለበት፥ በእርሱ ፊት ያለ ነውር መሆኑን እግዚአብሔር አረጋገጠ ማለቱ ነው። ጽድቅ የሚጨመርበት ወይም የሚቀነስበት ጉዳይ አይደለም፤ ሰው ጻድቅ ነው ወይም ጻድቅ አይደለም፤ ሰው ጻድቅ ነው ሲባል በሕግ ፊት ሁኔታውን እንጂ ጠባዩን አያመለክትም። ሰው በክርስቶስ ከሆነ ጽድቅ ይኖረዋል፤ ሰው በክርስቶስ ባይሆን ግን ምንም ጽድቅ የለውም።

ቅድስና እንደ ጽድቅ አይደለም፤ ያድጋል፤ ይበዛል። በመሆኑም ክርስቲያን በቅድስና እያደገ ይሄዳል። መጀመሪያ እግዚአብሔር ለራሱ ኃጢአተኛውን ይለያል፤ በኋላም የአማኙን ጠባይ ወደ ክርስቶስ ባሕርይ ይለውጣል፤ ይህም ሥራ ክርስቲያን ካመነበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሞት ድረስ በመቀጠል በትንሣኤው ዕለት ይደመደማል።

ጸሎት፤ ሕይወትህ በቅድስና እየተመራ እንዲያድግ ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. ክርስቲያን በመንፈስ መመላለስና ሕግን መፈጸም የሚጀምረው መቼ ነው (ቊ.1-4)?

2. እንደ ሥጋ ፈቃድ በመኖርና እንደ መንፈስ ፈቃድ በመኖር መካከል ያለውን ልዩነት አነጻጽር (5-13)።

3. ተግባረ ሥጋን (የሥጋን ሥራ) ለመግደል ምን ታደርጋለህ (13)?

4. ሀ) የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ በሕይወታቸው ምን ያውቃሉ (14-16)፥ ለ) ተስፋቸውስ ምንድን ነው (17)?

ማስገንዘቢያ፤ ክርስቲያን ቅዱስ ለመሆን የሚጋደለው (የሚጥረው) የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን አይደለም።

ማስታወሻ፤

ቊ.13 የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ፤ አማኙ እንዲህ ቢያደርግ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የኃጢአትን ሥር ሊያዳክምና ሊያስወግድ ይጥራል። ቅድስና የኃጢአትን ሥር ማጥፋትንና አዲስ ሕይወት ማሳደግን ያጠቃልላል።

ቊ.16 ያ መንፈስ ራሱ፤ የእግዚአብሔር መንፈስና የአማኙ መንፈስ (ሕሊና) በአንድነት አማኙ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ይመሰክሩለታል።

## 54. የአማኝ ዋስትና



መግቢያ፤ የሚከተሉት ሁለት ጥያቄዎች አማኙን ሊያውኩ ይችላሉ ፦ በክርስቲያን ላይ ይህን ያህል መከራና ሥቃይ ለምን ይደርስበታል? በመጨረሻስ የአማኙ ደኅንነት ሊጠፋበት ይችላልን? የዛሬው አንቀጽ ወደ እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች መልስ ይመራናል።

ጸሎት፤ እግዚአብሔር ያቀደልህን ታላላቅ ዓላማዎች እንድታስተውል ጌታን ለምን።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. የጠቅላላው ፍጥረት፥ ሀ) ሁኔታ፥ ለ) ተስፋ ምንድን ነው (ቍ.18-25)?

2. በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የሚገኙትን የመዳን ደረጃዎች በቅደም ተከተል ዘርዝር (28-30)?

3. አማኝ በሕይወት ጉዞው የሚያጋጥመው ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሆነ እንዴት እናውቃለን (28-30)?

4. የሚያጋጥምህ ሁሉ ከእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ነው ብለህ ትቀበለዋለህን? ለምን?

5. አማኙን ጳውሎስ በክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለየው ነገር እንደሌለ ያቀረባቸውን ምክንያቶች ጻፍ (31-39)።

ማስገንዘቢያ፤ «ለዘላለም አይጠፉም ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም» ዮሐንስ 10፥28።

ማስታወሻ፤

ቍ.23 የሰውነታችን ቤዛ፤ ከኃጢአት፥ ከሥቃይና ከሞት ሁለንተናችን ነፃ የሚሆነው በትንሣኤ ዕለት ነው። 49ኛውን ጥናት ተመልከት።

ቍ.29 አስቀድሞ ያወቃቸው፤ የእግዚአብሔር እውቀት እንደ ሰው እውቀት የተወሰነ አይደለም። አሞጽ 3፥2ንና 50ኛውን ጥናት ተመልከት።

## 55. አማኙና የግል ሕይወቱ



<u>መግቢያ</u>፤ ይህ ምዕራፍ በሮሜ መልእክት ተደጋግሞ በሚገኘው «እንግዲህ» በሚለው ቃል ይጀምራል፥ ምክንያቱም መልእክቱ ከአንድ ሐሳብ ወደ ሌላ ሐሳብ ስለሚመራ ነው። ከዚህ ቃል አገባብ የተነሣም በጳውሎስ አቀራረብ ተከታታይነትን እንጂ ተቃራኒነትን አናገኝም። ሐዋርያው ሰው ሁሉ እንደተኰነነ (ምዕራፍ 1-3)፥ ክርስቲያን እንዴት እንደጸደቀ (ም.4-7)፥ እንደተከበረና (ም.8) እንደተመረጠ (ም.9-11) ካሳየ በኋላ፥ አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ በተገለጠው በእግዚአብሔር ጸጋ ባለጠግነት መሠረት ለእግዚአብሔር ክብር እንዲኖሩ አደራ ይላቸዋል።

<u>ጸሎት</u>፤ ለእግዚአብሔር ጸጋ ደስ በሚያሰኘው መንገድ መልስ እንድትሰጥ ጸልይ።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. እግዚአብሔር ያደረገልህን ሁሉ ተገንዝበህ፥ ሀ) እግዚአብሔርን ማክበር፥ ለ) ዓለምን ማየት፥ ሐ) አካሔድህን መለወጥ እንዴት ይገባሃል (ቍ.1-2)?

2. ሀ) የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ በምን ምሳሌ ተብራራ? ለ) በቤተ ክርስቲያን አባልነትህ ቤተ ክርስቲያንን እንዴትና በምን ታገለግላለህ (3-8)?

3. በዓለም ስትኖር ሕይወትህን እንዴት መምራት እንዳለብህ ለማሳየት፥ ሀ) ማድረግ የሚገቡህን፥ ለ) ማድረግ የማይገቡህን ነገሮች ለይተህ ዘርዝር (9-21)።

4. ለነዚህ ሦስት ጥያቄዎች የሰጠኸውን መልስ መርምረህ ያለህን አመለካከትና አድራጎት ለማረም በተለይ ምን ማድረግ ይገባሃል?

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ ሰው መለወጡ የሚታወቀው አዲስ አስተሳሰብ (አመለካከት) በማመንጨት ላይ ሲገኝ ነው። ቍ.2ን ተመልከት።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.1 ሕያው ... መሥዋዕት</u>፤ እግዚአብሔር የሚፈልገው እንስሳትን ሳይሆን የመንፈሳችንን፥ የነፍሳችንን፥ የሥጋችንን ማለትም የሁለንተናችንን እሺታ ነው።


<u>ለአእምሮ የሚመች</u>፤ ቅንነት ያለበት፥ ምክንያቱም መሥዋዕታችን ለእግዚአብሔር ጸጋ ተገቢ መልስ ነው።

<u>ቍ.20:21</u> ለክርስቲያን ከሁሉ የተሻለው መንገድ የጠላትን ወዳጅነት በማግኘት ክፋትን በደግነት ማሸነፍ ነው።

## 56. <u>አማኙና ቤተ ክርስቲያኑ</u>

**ቈላስይስ 3፥1-17**

<u>መግቢያ</u)፤ በ43ኛው ጥናት በኢየሩሳሌም የነበረችውን የአዲሲቱን ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ተመልክተን ነበር። አባሎችዋ ሁሉ አይሁድ ነበሩና በአይሁድ ዋና ከተማ ይኖሩ ነበር። በሌላም በኩል በእስያ የነበረችው የቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን በአረማውያን መካከል ትኖር ነበር፥ አብዛኞቹ አባሎችዋም ከአይሁድ የዘር ግንድ ውጭ ነበሩ።



<u>ጸሎት</u>፤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንህን እንደ ፈቃዱ እንዲያድሳት ጌታን ለምን።

<u>ንባብ</u>፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

<u>ጥያቄ</u>፤

1. ሀ) የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባል እምነት በማን ላይ የተመሠረተ ነው? ለ) የወደፊት ሕይወቱና ተስፋውስ (ቍ.1-4)? ሐ) በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ምን ልዩነት አለ (11)?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. ሀ) የቈላስይስን ቤተ ክርስቲያን መጐብኘት ብትችል ኖሮ ልትገነዘብ የምትችለውን ስሕተትና ጕድለት በሙሉ ዘርዝር (5-14)፥ ለ) ከዝርዝሩ በሕይወትህ ወይም በቤተ ክርስቲያንህ የሚታዩትን ለይተህ አስምርባቸው፥ ሐ) እንግዲህ «ግደሉ» (5) እና «ልበሱ» (12) የተሰኙትን ትእዛዛት ለግልህ ልብ አድርግ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

3. ሀ) የእውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን ጠባይት በዝርዝር አመልክት (14-17)፥ ለ) እነዚህ ባሕርያት በቤተ ክርስቲያንህ በይበልጥ እውን እንዲሆኑ ምን ታደርጋለህ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

<u>ማስገንዘቢያ</u>፤ «እናንተ ... የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» 1 ጴጥሮስ 2፥9።

<u>ማስታወሻ</u>፤

<u>ቍ.9 አሮጌ ሰው</u>፤ ከአዳም የተወረሰ የሰው ጠባይ።

<u>ቍ.10 አዲስ ሰው</u>፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በምእመናን ዘንድ (ውስጥ) የሚፈጠር የክርስቶስ ባሕርይ።

## 57. አማኙና ቤተ ሰቡ



መግቢያ፤ እውነተኛ ክርስቲያን ሕይወቱ ሲመረመር ሁለመናው ከክርስቶስ ጌትነት በታች እንዲሆን ይፈልጋል። የማናቸውም ኅብረተሰብ ዋና መሠረት የቤተ ሰብ ሁኔታ ነው።

ጸሎት፤ የቤተ ሰብህ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር እየተስማማ እንዲሔድ ጸልይ።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. አማኙን ለቤተ ሰብ ኑሮ የሚያመቻቹት ድርጊቶችና ሀሳቦች ምንድን ናቸው (5፥15-21)?

2. ሀ) ክርስቶስና ባል፥ ለ) ቤተ ክርስቲያንና ሚስት በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት እንዴት ይነጻጸራሉ (5፥22-33)?

3. ሀ) በቤተ ሰብ ውስጥ የሚስቶች መገዛትና የልጆች መታዘዝ በምን ዓይነት መንፈስ መፈጸም ይገባቸዋል (5፥21:22፤ 6፥1-3)?
ለ) መገዛትንና መታዘዝን ተስማሚና አልፎ ተርፎም አስደሳች የሚያደርጋቸው ምንድን ነው (5፥21:25፤ 6፥4)?

4. አኗኗርህን ወይም አካሔድህን በቤተ ሰብህ ውስጥ እንዴት ማሻሻል ትችላለህ?

ማስገንዘቢያ፤ በወላጆች መካከል ያለው የሰመረ ግንኙነት ለልጆቻቸው እድገት ዋና መሠረት ነው።

ማስታወሻ፤

5፥21 ለእያንዳንዳችሁ ... የተገዛችሁ ሁኑ፤ በአንዲት ሕያው ቤተ ክርስቲያን (ቊ.19:20) አባሎች ሁሉ፥ ሀ) በፍቅርና በብርሃን እየተራመዱ (5፥1-18)፥ ለ) በመንፈስ ቅዱስ እየተሞሉ (5፥18) እርስ በእርሳቸው ይገዛሉ።

## 58. አማኙና መተላለፉ

**1 ዮሐንስ 1፥5-10፤ 2፥1-6**



**መግቢያ፤** ሰው ወደ እምነት ከደረሰና አዲስ ህይወት ካገኘ በኋላ ኃጢአትን ሊሠራ ይችላል፤ እንዲያውም ከእግዚአብሔር ጾጋ መቀበሉን ሊጠራጠር ይችላል።

**ጸሎት፤** በሕይወትህ ያለው የኃጢአት ኃይል እንዲሰበር እግዚአብሔርን ለምን።

**ንባብ፤** አንቀጹን ሦስት ጊዜ አንብብ።

**ጥያቄ፤**

1. አስተዋይ ሰው ሊክዳቸው የማይችል ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው (1፥6-10)?

2. ክርስቲያን ኃጢአትን ቢሠራ፥ ሀ) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ፥ ለ) ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ፥ ሐ) ስለ ግል ሕይወቱ ልብ ማድረግ የሚገባው ምንድን ነው?

3. ኃጢአተኛ ይቅርታንና መንጻትን ለማግኘት ምን ማድረግ ያስፈልገዋል?

4. የክርስቲያን የቃሉ ምስክርነትና አካሔዱ እንዴት መገናኘት ይገባቸዋል (2፥3-6)? ይህንን ከራስህ አኗኗር ጋር አነጻጽር።

**ማስገንዘቢያ፤** የክርስቲያኖች የኅብረት ስምረት እያንዳንዱ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ነው (1፥7)።


**ማስታወሻ፤**

**1፥5 እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤** እንከን የሌለው ፍጹም ቅዱስና ንጹህ ነው።

**2፥1 ጠበቃ፤** ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ በመለኮታዊ ኃይሉና በግርማ ሞገሱ በአብ ዘንድ በመሆኑ የመሥዋዕትነት ውጤቱ ለምእመናን መዳን አቻ የሌለው ዋስትና ነው።

**2፥2 የኃጢአታችን ማስተስሪያ፤** ክርስቶስ በመሞቱ በኃጢአት ምክንያት በሰው ላይ የነበረውን የእግዚአብሔርን ቍጣ አራቀ። 1 ዮሐንስ 4፥10፤ ሮሜ 3፥25ን ተመልከት።

## 59. አማኙና ጠባቡ መንገድ



መግቢያ፤ ይህ መልእክት «የዛሉትን እጆቻቸውንና የደከሙትን ጉልበቶቻቸውን አቅኑ» በተባሉ መሪ ቃላት ተስፋ የቈረጡትን ሰዎች ለማበረታታት ተጻፈ (12፥12)። በ54ኛው ጥናት ለክርስቲያን «ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» የሚለውን ሐረግ መርምረናል (ሮሜ 8፥28)። የዛሬውም አንቀጽ ይህንኑ ሐሳብ በተለያየ መልክ ያብራራል።

ጸሎት፤ እግዚአብሔር ሕይወትህን በመቈጣጠር ለአንተ ያለውን ፍቅር በይበልጥ እንዲገልጥልህ ጌታን ለምን።

ንባብ፤ አንቀጹን አንድ ጊዜ አንብብ።

ጥያቄ፤

1. በፊትህ ያለውን «ሩጫ» ለመሮጥ የክርስቶስን አርአያነት እንዴት ብትገነዘብ ሊረዳህ ይችላል?

2. የጌታ ተግሣጽ፥ ሀ) ለምን ያስፈልጋል? ለ) ውጤቱ ምንድን ነው (ቍ.5-11)፥ ሐ) ይህ ቍጥጥርስ ምን ያረጋግጥልናል?

3. ከቍ.12-17 የተገለጡትን የክፋት ዓይነቶች ዘርዝርና በሕይወትህ የሚገኙትን ለይተህ አስምርባቸው።

4. ከዚህ ጥናት የተነሣ ስለ እግዚአብሔር ያለህን አመለካከት መለወጥ የሚያስፈልግህ ይመስልሃል? ለምን?

ማስገንዘቢያ፤ ተግሣጽን ስትቀበል ስሜትህ እንዴት እንደሚሆን አሰላስል።

ማስታወሻ፤

ቍ.1 ምስክሮች፤ በምዕራፍ 11 የተዘረዘሩት የእምነት ጀግኖች።

ቍ.16 ዔሳው፤ «መራራ ሥር» (ቍ.15) የተገኘበት የሰው ምሳሌ። ዘፍጥረት 25፥30-34፤ 27፥30-40፤ 28፥8:9ን ተመልከት።

## 60. አማኙና ተስፋው

**የዮሐንስ ራእይ 22፥1-5፡12-21**



**መግቢያ፤** ስለ መንግሥተ ሰማያት ራእይ ማየት ለሐዋርያው ዮሐንስ ተሰጠ። ይህ ራእይ ሲገለጥም በብሉይ ኪዳን የተጻፉት አያሌ ታሪኮች፥ ስሞችና ልዩ ልዩ ጉዳዮች ተጠቅሰዋል። ራእዩ በጥቅሉ ሲታይ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጋር የተያያዘ ነው።

**ጸሎት፤** ለኢየሱስ ዳግም ምጽአትና ለመንግሥተ ሰማያት ዝግጁ እንድትሆን ጸልይ።

**ንባብ፤** የተሰጡትን ጥቅሶች ሁለት ጊዜ አንብብ።

**ጥያቄ፤**

1. አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን በማስመልከት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ፈልግ (ቍ.1-5፡14፡15)፡-
ሀ) በራእዩ የሚገኙት ነገሮች የምን ምሳሌዎች ናቸው? ለ) በከተማዋ ማን ይኖራል? ሐ) አማኞች ምን ያደርጋሉ? መ) በከተማዋ የማይገኙ ነገሮች ምንድን ናቸው? ሠ) ከከተማዋ ውጭ ማን ይቀራል?

2. በራእዩ ውስጥ፥ ሀ) ኢየሱስ በምን ይመሰላል? ለ) ምን በመሥራት ላይ ይታያል (12፡13፡16፡20)?

3. ሀ) የክርስቶስን መመለስ እነማን በጉጉት ይጠባበቃሉ (17፡20)? ለ) ይህ የአንተም ምኞትና ናፍቆት ነውን?

4. ሀ) በዚህ መጽሐፍ እንዴት ትጠቀማለህ (18፡19)? በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስን ወደፊት እንዴት ታነባለህ? ሐ) ለምን?

**ማስገንዘቢያ፤** «ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና» ማቴዎስ 5፥8።

**ማስታወሻ፤**

**ቍ.1 በጉ፤** ለኃጢአት የተሠዋ የክርስቶስ ምሳሌ። ዮሐንስ 1፥29ን ተመልከት።

**ቍ.2 የሕይወት ዛፍ፤** ቍ.14፥ ዘፍጥረት 2፥9፤ 3፥24ንና የ3ኛውን ጥናት ማስታወሻ ተመልከት።

**ቍ.13 አልፋና ዖሜጋ፤** በግሪክ ቋንቋ የመጀመሪያና የመጨረሻ ፊደሎች ናቸው።

**ቍ.17 ሙሽራይቱ፤** ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው። 57ኛውን ጥናት ተመልከት።

## የጥናት መልሶች

የጥያቄ መልሶችን በሦስት ክፍሎች መድቦ ማስተዋል ይቻላል።

1ኛ፤ በአንቀጹ ውስጥ የሚገኘው ሐሳብ፥ የታሪክ፥ የትምህርት ወይም የሌላ ጉዳይ ከሆነ መልሱ ዋናውን ሐሳብ በመፈልቀቅ ይገኛል።

2ኛ፤ አንቀጹ ምን ፍሬ ነገር እንዳለው የሚገልጥ መልስ ይሆናል።

3ኛ፤ አንቀጹ ከታየ በኋላ አንባቢው ውሳኔ ላይ እንዲደርስ የሚያበቃ መልስ ሊሆን ይችላል።

ለ1ኛና ለ2ኛ ዓይነት መልሶች አጭር የሆኑ መሪ መልሶችን ከዚህ ቀጥሎ አስፍረናል፤ መልሱ «የግል» ሲባል እያንዳንዱ አንባቢ በግል አስተያየቱ እንደ የሕይወቱ ገጠመኝ ይመልሰዋል ማለት ነው።

1. እግዚአብሔርና ፍጥረቱ

1. 1. ብርሃን 2. ጠፈር 3. ምድርና ባሕር፤ ሣር፥ ቡቃያ፥ ዛፍ። 4. ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብት 5. ዓሦች፥ ወፎች 6. አራዊትና እንስሳት፤ ሰው። እግዚአብሔር ሁሉን በተራ ይሠራል፤ ለሕይወትም አስፈላጊውን ሁሉ ያዘጋጃል።
2. ሀ) ከሁሉ በፊት መኖሩ፤ ለእርሱ መኖር ዓለም አስፈላጊ አለመሆኑ፥ ለ) ሁሉን በቃሉ እንደ ፈቃዱ ፈጠረ፥ ሐ) ሁሉን መልካም አድርጎ ስለፈጠረ በሥራው እንዲከበር።
3. ሀ) በእግዚአብሔር መልክ ወይም አምሳል ተፈጠረ፤ ይህም ሥጋዊውን ሁኔታ ሳይሆን፥ መንፈሳዊውን ሁኔታ ያመለክታል ማለት ለዘላለም የሚኖር፥ ከእግዚአብሔር ጋር መናገር የሚችል፥ በመልካምና በክፉ መካከል ያለውን ልዩነት ለይቶ የሚያውቅ፥ በፍጥረት ላይ የእግዚአብሔር ወኪል ሆኖ የሚያስተዳድር፥ ለ) እንደ ፍጥረታዊ ሁኔታቸው በፍጥረታት ሁሉ ላይ በአግባቡ እንዲጠቀምና እንዲያስተዳድር።
4. መልሱ ከግል እንዲሰጥ ይጠበቃል።

2. ሰው በዓለም ላይ

1. የዕረፍት ቀን (ቍ.1-3)፥ ምቹ ቦታ (8-15)፥ አጥጋቢ መብል (9)፥ ተስማሚ ሥራ (15)፥ የሞራል ምርጫ (9፥16-17)፥ ተገቢ ሥልጣን (19-20)፥ አስደሳች ጓደኛ (21-25)።
2. ሰው የእግዚአብሔርን አርአያ ተከትሎ እግዚአብሔርን በማምለክና ከሳምንቱ ሥራ በማረፍ።
3. «ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ»።
4. የሕይወት ዛፍ ለወደፊት ሞት ሊገኝበት የማይችልበት ሁኔታ እንዳለ፤ መልካሙንና ክፉውን የሚያስታውቅ ዛፍ ሰው ለእግዚአብሔር ቢታዘዝ የዘላለምን ሕይወት እንደሚወርስ።
5. በፍቅርና በደስታ ሲከበር የእግዚአብሔር በረከት፤ ሁለቱም ከወላጆቻቸው ቍጥጥር ሥር ወጥተው ጓደኛቸውን የሕይወታቸው ዋና ክፍል ማድረግ፤ እስከ ሞት ድረስ የማይፈርስ አንድነት፤ የጾታ ግንኙነት (ግብረ ሥጋ) የፍቅርና የጋብቻ ሕግ መደምደሚያና ማኅተም፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሴት ለወንዱ በአባትዋ ሳትሰጥ ወንድ ሴትን ማወቅ አይገባውም፤ ሁለቱም በእግዚአብሔር መልክ ስለ ተፈጠሩ ይተካከላሉ፤ ነገር ግን ሥራቸው የተለያየ ስለሆነ ወንድ የሴት መሪ፥ ኀላፊ፥ ጠባቂ ሲሆን፤ ሴትም የወንድ ተከታይ፥ ረዳት ጓደኛ።

3. ውድቀትና ውጤቱ

1. ሰይጣን በጥርጥር (ቍ.1)፥ በውሸት (4) እና እግዚአብሔርን ጨካኝ በማስመሰል።
2. እራቁታቸውን መሆናቸውን ተገንዝበው፥ ነውራቸው ተሰማቸው፥ ከእግዚአብሔር ሸሹ፥ ሊያመካኙ ጀመሩ፥ ከገነት ተባረሩ።
3. ሀ) ጠላትነት፥ ለ) የመውለድ ምጥ ሥቃይና ከባል በታች መኖር፥ ሐ) የሥራ ድካምና ሞት።
4. ሀ) ዘር እንደሚኖረው፥ ዘሩም ሰይጣንን እንደሚያሸንፍ (ይህ በክርስቶስ ተፈጸመ)፥ ለ) ለሴቲቱ የሰብአዊ ፍጥረት ሁሉ እናት የሚለውን ስም አወጣላት (ሔዋን)።
5. የማሸነፍ ተስፋ ተሰጠው (15)፥ ነውሩን ሸፈነ (21)
6. የግል።

4. የቃል ኪዳን መመሥረት

1. ሀ) አገር እንደሚያገኝ፤ የታላቅ ሕዝብ አባት እንደሚሆን፤ በእርሱም ነገዶች ሁሉ እንደሚባረኩ፥ ለ) ዘሩ ከነዓንን እንደሚወርስ፥ ሐ) መሠዊያን ሠራ።
2. ሀ) ልጅ አልነበረውም፥ ለ) እምነት።
3. ሀ) የብዙ ሕዝብ አባት እንደሚሆን፤ ነገሥታት ከእርሱ እንደሚወጡ፤ ቃል ኪዳኑ ከእርሱና ከዘሩ ጋር ለዘላለም መሆኑ፤ እግዚአብሔር አምላክ እንደሚሆንላቸው፤ የከነዓን ምድር እንደሚሰጣቸው፥ ለ) ወንዶችን ሁሉ ማስገረዝ።
4. የግል።

5. አዲስ ስም

1. ሀ) ብቻውን በሽሽት ላይ፥ ለ) በሕልሙ ከመሬት እስከ ሰማይ በሚደርስ መሰላል ላይ ወይም አጠገብ፥ ሐ) እርሱና ዘሩ አገሩን እንደሚወርሱ፤ ዘሩ እንደ አሸዋ እንደሚሆን፤ የምድርም አሕዛብ በእርሱና በዘሩ እንደሚባረኩ፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሚሆንና ወደ አገሩ እንደሚመለስ፥ መ) ሐውልት አድርጎ ዘይትን አፈሰሰበት፤ ቦታውን ቤቴል ብሎ ሰየመው፤ ስእለትን ስለ ቦታና ዐሥራት ተሳለ።
2. ሀ) ብቻውን የወንድሙን መምጣት እየፈራ፥ ለ) እግዚአብሔር በሰው መልክ ተገልጦ ከያዕቆብ ጋር ታገለ፥ ያዕቆብ ሲሸነፍ ትግልን አልተወምና በመጨረሻ አዲስ ስምን ከእግዚአብሔር ተቀበለ፥ ሐ) ያዕቆብ በትግሉ ከእግዚአብሔር በረከትን እንደተቀበለ።
3. የግል።

6. <u>የነፃ አውጭ ጥሪ</u>

1. የግል።

2. በእሳት ነበልባል ውስጥ፤ እንደ አባቶቹ አምላክ፤ እንደ አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ አምላክ፥ ለ) ፍርሃት፥ ሐ)የግል።

3. ሀ) አካላዊ፥ ኃይል፥ ቅዱስ፥ መሐሪ፥ ሁሉን የሚያውቅ፥ ዕቅድ ያለው፥ ከሚጠራው ጋር የሚሆን፥ ለ) እግዚአብሔርን አክባሪ፥ ትሑት መሆኑ።

4. የግብጽን አገር ትምህርት ሁሉ የተማረ፥ ከሕዝቡ ጋር አንድ መሆኑ፥ ትሑት፥ ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝቶ ጥሪውን ተቀባይ።

5. የግል።

7. <u>የማይረሳ ሌሊት</u>

1. ሀ) በቤት ሁለቱን መቃንና ጉበኑን መቀባት፥ ለ) መጥበስና በዚያ ሌሊት በቤት ውስጥ መብላት።

2. የእስራኤል ሕዝብ ቤት ምልክት ሆኖ ከበኵር ልጅ ሞት አዳናቸው።

3. ፈርተው እስራኤላውያን ከአገር ቶሎ እንዲወጡ አዘዙአቸው።

4. ዘላለማዊ መታሰቢያና ዓመት በዓል።

5. በፋሲካ በግ ደም እስራኤላውያን እንደዳኑ ሁሉ እኛም ከእግዚአብሔር ፍርድ በክርስቶስ ደም (ሞት) ስለምንድን።

6. የግል።

8. <u>የእግዚአብሔር ሕግ</u>

1. ሀ) ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት አውጥቶ ነበር፥ ለ) አምላካቸው በመሆኑ፥ ሐ) እግዚአብሔር በሚጠሉት ላይ በደላቸውን እስከ 4ኛው ትውልድ፥ ለሚወድዱትም በረከትን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚያመጣ መሐሪና ቀናተኛ በመሆኑ፤ ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ባለማንጻቱ፤ በፍጥረት አርአያነት በመስጠቱ፤ መታዘዝ የሰላም መንገድ በመሆኑ (12)።

2. ዘላለማዊ፥ መሐሪ፥ ታማኝ፥ ቀናተኛ፥ ሁሉን የሚያውቅ፥ ሁሉን ቻይና በሁሉ ዘንድ የሚገኝ ብቸኛ አምላክ መሆኑ።

3. በላይ ላሉት መታዘዝ (12)፤ የሌላውን ሕይወት (13)፥ ክብር (14)፥ ንብረት (15)፥ ስም (16)፥ እንደ ራስ ማክበር።

4. ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ይደረጋልና የእውነተኛ አማኝ የልብ ምኞት ትክክለኛ መሆን አለበት።

5. የግል።

9. <u>የማደሪያው ድንኳን</u>

1. ጉዳዩ ሁሉ የእግዚአብሔር መሆኑን ለማስረገጥና ዕቅዱን በልልነት ሳይሆን ልክ እንደ ትእዛዙ ዝርዝር መፈጸም ስለሚያስፈልግ።

2.1. ማደሪያ 2. ታቦት 3. መጋረጃ 4. ገበታው 5. መቅረዙ 6. የወርቅ መሠዊያ 7. መጋረጃ 8. የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ 9. ሰን (ሳሕን) 10. አደባባዩ 11. ደጃፍ።

3. ሀ) ደመናው የመገናኛውን ድንኳን ከደነ፥ ለ) የእግዚአብሔር መገኘት።

4. የግል።

10. <u>ወደ ተስፋው አገር መግባት</u>

1. የግል።

2. 14።

3. አገር ሁሉ እንደሚሰጥ፤ ማንም እንደማይቋቋመው፤ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንደነበረ ከእርሱ ጋር እንደሚሆን፤ እግዚአብሔር እንደማይጥለውና እንደማይተወው፤ ለሕዝቡ አገሩን እንደሚያወርስ።

4. በሙሴ የተሰጠውን ሕግ ሁሉ መጠበቅ፥ ከሕጉ ዝንፍ አለማለት፥ እንደ ሕግ ብቻ መናገር፥ በቀንና በሌሊት ሕግን ማሰብ።

5. የሕዝቡን አለቆች ጠርቶ ወደ አገራቸው ለመግባት ሕዝቡን እንዲያዘጋጁ አዘዛቸው።

6. የግል።

11. <u>የንጉሥ መመረጥ</u>

1. ሳኦልን ሲወድና ለእርሱ ሲያለቅስ ሳለ ይፈራው ነበር።

2. ለመሥዋዕቱ ባለመጠራቱና በታላቅ ወንድሙ ተግሣጽ የተናቀና ያልተወደደ መሆኑ ይታያል።

3. ሀ) በቁመትና በመልክ ሳይሆን በልብ ሁኔታ፥ ለ) የግል።

4. የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በኃይል መጣ።

5. የግል።

12. <u>ለንጉሥ የተሰጠ የተስፋ ቃል</u>

1. ሀ) ለታቦት ቤትን መሥራት፥ ለ) እግዚአብሔር ስለባረከውና እግዚአብሔርን ለማክበር።

2. መንጋውን ከመከተል ንጉሥ እንዲሆን ሾመው፤ ጠላቶቹን ሁሉ አጥፍቶ ነበር፤ ትልቅ ስም እንዲኖረው ተስፋ ሰጥቶት ነበር።

3. ሀ) በአገር በሰላም እንዲኖር፤ ወደ መሳፍንት ዘመን ሁኔታ እንደማይመለስ፥ ለ) ለዘላለም በእስራኤል እንደሚነግሥ፤ ምንም እንኳ ቢያጠፋ እግዚአብሔር እንደ ልጅ ይቀጣዋል እንጂ እንደ ሳኦል ቤት ሰብ ምሕረት እንደማያርቅበት፥ ሐ) የዳዊት ልጅ ቤተ መቅደስን እንደሚሠራ።

4. እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ በመሆኑ፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሕዝብ ሁሉ በላይ የተባረከ፤ እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚፈጽም፤ ሕዝቡንና ቤቱን እንደሚባርክ።

5. የግል።

13. <u>የንስሐ ጸሎት</u>

1. ሀ) መተላለፍ፥ በደል፥ ስሕተት፥ ኃጢአት፥ ክፋት፥ ዓመፅ፥ ለ) እግዚአብሔር፥ ሐ) በፅንስ፥ ከአዳም።

2. እንዲታጠብ (እንዲነጻ)፥ ንጹሕ ልብ እንዲፈጠርለት፥ የቀናው መንፈስ በልቡ እንዲገኝ፥ መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ እንዳይወሰድ።

3. የእግዚአብሔርን መንገድ አስተማረ፥ ምስጋናውን አሰማ።

4. የተሰበረ መንፈስ፥ የተሰበረና የተዋረደ ልብ።

14. <u>የእግዚአብሔር ቤት</u>

1. ሀ) በቅድስተ ቅዱሳን በቤተ መቅደስ፥ ለ) ሁለቱ የድንጋይ ጽላት፥ ሐ) ደመናው ቤቱን ሞላ።

2. የግል መልስ ሲሆን ዋና ዋና ነጥቦቹ፥ እግዚአብሔር ስሙ በኢየሩሳሌም እንዲሆንና ዳዊት በእስራኤል ላይ እንዲነግሥ መረጠ፥
የዳዊት መልካም ምኞት በልጁ ተፈጸመ፥ ሰሎሞን ቤቱን ሠራ፥ ለታቦቱም መኖሪያ ሆነ።

3. ሀ) ለእግዚአብሔር የግዴታ አያስፈልግም፥ ግን ሊያድርበት ይችላል፥ ለ) ሕዝቡ ሲታዘዝለት ስሙን ያስጠራል፥ ሐ) በፊት
አገልግሎት በመገናኛ ድንኳን ነበረ፥ አሁንም በይበልጥ ክቡር ሆነ።

4. ሀ) የግዴታ አስፈላጊነት አይኖረውም፥ ለ) ለመሰብሰቢያ፤ ለማስተማርና ለማምለክ ምቹ ቦታ፤ የሰውን ሀሳብ ወደ አምልኮት
ስለሚመራ፥ ሐ) ሕዝቡ።

15. <u>የባዕድ አምልኮ ከንቱነት</u>

1. ሀ) የበዓልና የዐፀድ፥ ለ) ለእግዚአብሔርና ለበዓል እያመለኩ በሁለት ሐሳብ ያነክሱ (ይዋልሉ) ነበር (ቍ.21)።

2. ዝም አሉ።

3. ይህ ነገር መልካም ነው አሉ።

4. በግምባራቸው ተደፍተው እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው አሉ።

5. እግዚአብሔር እርሱ አምላክ መሆኑና፥ ኤልያስ ታማኝ ባሪያው መሆኑ እንዲገለጥ፤ የሕዝብ ልብ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ።

6. የግል።

16. <u>የሚላክ አገልጋይ</u>

1. ሀ) አስተዋይ፥ መልኩ የተጎሳቆለ፥ ውበት የሌለው፥ ግፍ ያላደረገ፥ ተንኰል ያልነበረበት፥ የተናቀ፥ የተጠላ፥ ለ)ተቸገረ፥ ቆሰለ፥
ደቀቀ፥ ተጨነቀ፥ ተሠቃየ፥ ዝም አለ፥ ተመታ፥ ተቀሠፈ፥ ከሕያዋን ተወገደ፥ ከክፉዎች ጋር ተቈጠረ፥ ተቀበረ፥ ሐ) ነፍሱን
ለሞት አሳልፎ ሰጠ።

2. ደዌአችንን ተቀበለ፥ ሕመማችንን ተሸከመ፥ ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፥ ስለ በደላችን ደቀቀ፥ የደኅንነታችን ተግሣጽ በእርሱ ላይ
ነበረ፥ በእርሱ ቁስል ተፈወስን፥ እግዚአብሔር በደላችንን በእርሱ ላይ አኖረ፥ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ተመታ፥ ነፍሱን ስለ ኃጢአት
መሥዋዕት አደረገ፥ ኃጢአታችንን ተሸከመ፥ ብዙዎችን ያጸድቃል።

3. ዜናው ወደ ዓለም ሁሉ ይደርሳልና ያስገርማል፥ ወደ ሕይወትም ይመለሳል፥ ዘሩን ያያል፥ እድሜው ይረዝማል፥ የእግዚአብሔርን
ፈቃድ ይፈጽማል፥ የድካሙን ፍሬ አይቶ ይደሰታል፥ ብዙዎችን ያወርሳል፥ ሞትን አሸንፎ የምርኮውን ውጤት ከዘሩ ጋር
ይካፈላል።

17. <u>የቃል ኪዳን መታደስ</u>

1. ሀ) እግዚአብሔርን በማወቁና ቤተ መቅደስን የማሳደስ ፍላጎቱ፥ ለ) ካህኑ ኬልቅያስ የሕግን መጽሐፍ ማግኘቱ፥ ለጸሐፊው ለሳፋን
መስጠቱና ሳፋን ለንጉሥ ማንበቡ።

2. ልብሱን ቀደደ፥ ምክንያቱም አባቶች ሕግን ያለመስማታቸው እግዚአብሔርን እጅግ ስላስቈጣ።

3. ንጉሡ በቦታው በቤተ መቅደሱ ደጃፍ ቆሞ ለሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ የቃል ኪዳኑን መጽሐፍ አንብቦ ሕዝቡን ቃል ኪዳን አስገባ፤
የጣዖታትን ምስሎች ሁሉ አቃጠለ፤ የዚህ አምልኮ ካሕናትንና፥ መናፍስት ጠሪዎችን፤ ጠንቋዮችንም አስወገደ።

4. የግል።

18. <u>ቃል ኪዳንን መሻርና ውጤቱ</u>

1. ሀ) በኤርምያስ ፊት ራሱን አላዋረደም፥ መሐላውን አፈረሰ፤ ልቡን አደነደነ፥ ለ) እንደ አሕዛብ ሁሉ አመለኩ፥ ቤተ መቅደስን
አረከሱ፥ በእግዚአብሔር መልእክተኞችና በቃላቸው ላይ ክፋት ተናገሩ።

2. የባቢሎንን ንጉሥ አመጣባቸው፤ ብዙዎች ተገደሉ፤ የቤተ መቅደሱ ዕቃ ወደ ባቢሎን ተወሰደ፤ ቤቱ ተቃጠለ፥ የከተማው ቅጥር
ፍራሽ ሆነ፥ ከሰይፍ ያመለጡ ተማርከው ባሪያዎች ሆኑ።

3. ለንጉሥ የእግዚአብሔርን ቃል ተናገሮ፥ ምርኮውም 70 ዓመት እንደሚሆን ገለጠ።

4. ለንጉሥና ለሕዝብ እያዘነ ነቢያትን እየላከ ፈቃዱን ገለጠ፤ በመጨረሻውም ፈረደባቸው።

5. የግል።

19. <u>የሕዝብ መመለስ</u>

1. ከአሕዛብ መካከል ሕዝቡን ያወጣቸዋል፤ ወደ ገዛ አገራቸው ይመራቸዋል፥ ወደ እውነተኛ ልብ ያደርሳቸዋል፥ ሁሉን ያድሳል፥
አሕዛብ ይህን አይተው የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ያውቃሉ።

2. የእስራኤል ሕዝብ በሄዱበት ሥፍራ ሁሉ ስሙን ስለ አሰደቡ፤ ስሙ በአሕዛብ መካከል እንዲከበርና እርሱ በሥራው እግዚአብሔር
መሆኑን እንዲያውቁ።

3. ሀ) ከኃጢአት ሁሉ እንዲነጹ፤ በአዲስ ልብ እንዲራመዱ፥ በእግዚአብሔር መንፈስ እንዲሞሉ፤ ለ) የግል መልስ።

4. አገራቸው ለምና ፍሬያማ፤ መንጎቻቸው ጥሩዎች፤ ከተሞቻቸው ባለ ዋስትናና ሕዝቡ መንፈሳዊ እንደሚሆኑ።

5. እግዚአብሔር ፈቃዱን እንደሚፈጽም፤ ክብሩን እንደሚጠብቅና ለሕዝቡ እንደሚራራ፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከኃጢአት እንደሚያነጻ

በመንፈሱም እንደሚሞላ መረዳት።

20. <u>አዲሱ ቤተ መቅደስ</u>

1. ሀ) ምንም እንኳን በአንድነት ቢሰበሰቡ በዙሪያቸው የነበሩትን አረማውያን ፈሩ፥ ለ) ኢያሱና ዘሩባቤል።
2. በኢየሩሳሌም ተሰብስበው መሠዊያውን ሠርተው መሥዋዕቶችን አቀረቡ የቤተ መቅደስ መሠረትንም ጣሉ።
3. ሀ) የሙሴ ሕግና የንጉሥ ዳዊት ሥርዓት፥ ለ) የግል።
4. ሀ) ደስታና ሀዘን፥ ለ) አንዳንዶች የእግዚአብሔር አምልኮ እንደገና ሲመሠረት ተደሰቱ፥ ሌሎችም የፊተኛውን መቅደስ ስለሚያውቁ ይኸኛው መቅደስ አነስተኛ በመሆኑ፥ ወይም መቅደሱ የብዙ ዓመታት ባድማ መሆኑን በማሰብ አዝነው አለቀሱ።
ሐ) የግል።

21. <u>የአዳኙ ብሥራተ ልደት</u>

1. አብርሃምና ዳዊት፤ ቃል ኪዳን ለእነርሱ ስለ ተሰጠ።
2. እጮኛሞች ነበሩ።
3. ማርያምን በስውር ሊተዋት አሰበ፤ በኋላ ግን ወሰዳት።
4. ሀ) ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ግብር እንደተፀነሰ፥ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው እንደሚያድን፥ ለ) ከድንግል እንደተወለደ፥ ስሙ አማኑኤል ሆኖ እግዚአብሔር በእርሱ አማካይነት ከሕዝቡ ጋር እንደሚሆን።
5. ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ለማዳን።
6. የግል።

22. <u>የአገልግሎት መግቢያ</u>

1. ሰዎች ለመሲሕ ዝግጁዎች እንዲሆኑ መጠመቅ እንዳለባቸው መሲሑ ከዮሐንስ እጅግ የሚበልጥ በመሆኑ፥ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ።
2. እንደ ኃጢአተኛ ተቈጥሮ ኃጢአተኞችን ለማዳን።
3. መንፈስ ቅዱስ ከአብ ዘንድ ወረደለት፥ አብ የተወደደው ልጁ መሆኑን አረጋገጠለት በሰይጣን ተፈትኖ አሸነፈው።
4. ሦስቱ በአንድ ወቅትና በአንድ ዓላማ መገኘታቸው፤ አብ «የምወደው ልጄ» በማለቱ የወልድ የባሕርይ አባት መሆኑ፤ ወልድ «የምወደው ልጄ» በመባሉ የአብ የባሕርይ ልጅ መሆኑ፤ መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ከሰማይ በመውረዱ ተገለጠ።
5. ሀ) ክርስቶስ ወደ ሥራው በመግባቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ጊዜ ስለ ደረሰ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡና በወንጌል እንዲያምኑ ነው፥ ለ) ዋና የመንግሥቱ ሥራ ሰዎችን «ማጥመድ» ማለት ሰዎችን በወንጌል ቃል ወደ መንግሥቱ ማስገባት ነው።

23. <u>ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት</u>

1. ዳግመኛ ባለመወለዱ የእግዚአብሔር መንግሥት እንዴት እንደሆነ አለመረዳቱና (ቍ.3) ና ወደ መንግሥቱ አለመግባቱ (5)፥ የብሉይ ኪዳንን ቃል መንፈሳዊነትና (ቍ.10) የክርስቶስን ማንነት (ቍ.16) ያለማስተዋሉ።
2. ከእግዚአብሔር መንፈስ።
3. በተሰቀለለት በክርስቶስ ያምናል፤ ለውጥ በሕይወቱ ይታያል።
4. ሰው ከጥፋት የሚድነውና የዘላለም ሕይወትን የሚቀበለው በክርስቶስ በማመን ነው። ማመን ማለት ትምህርቱን ብቻ መቀበል ሳይሆን ተስፋውን ሁሉ በክርስቶስ ሞት መጣል ማለት ነውና በዚህ መሠረት መኖር።
5. ወደ መንግሥቱ በመግባቱ እውነተኛ አማኝ ክርስቶስን እየወደደ እንደ መንግሥት ዜጋ ይኖራል፤ ተስፋው ሁሉ በክርስቶስ ይኖራል፤ ወደ ፊትም ይራመዳል፤ በብርሃንም ይመላለሳል። የግል።

24. <u>የአዲስ ዜጋ ጠባይ</u>

1. ሀ) በመንፈስ ድሃ፥ የሚያዝን፥ የዋህ፥ ጽድቅን የሚራብና የሚጠማ፥ የሚምር (የሚራራ) ልበ ንጹህ፥ የሚያስተራርቅ፥ ስለ ጽድቅ የሚሰደድ፥ ለ) እኔ ስለራሴ ኀላፊ ነኝ ባይ፥ የሚስቅ፥ ራሱን የማያዋርድ፥ ረክቼአለሁ ባይ፥ የሚጨቁን፥ በሐሳብ የሚዋልል፥ የሚያጋጭ፥ ከኀላፊነትና ከመከራ የሚሸሽ።
2. የመንግሥት ሰማያት ዜጋዎችና የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸው፤ መጽናናት፥ ምድርንና ምሕረትን እንደሚያገኙና እግዚአብሔርን እንደሚያዩ።
3. ዓለም ጥሩ ምሳሌ አይቶ እንዳይበላሽና እውነትን እንዲያውቅ ነው።
4. የእርሱ ትምህርት የብሉይ ኪዳኑን ይፈጽማል እንጂ አያፈርሰውም፤ ይህም በብዙ መንገድ ተከናውኗል ፡- ትንቢቱን በመፈጸም፥ የሕጉን መንፈሳዊነት በመግለጥ፥ የብሉይ ኪዳኑን መሥዋዕት በራሱ መሥዋዕት ያለፈ በማድረጉ ...ወዘተ።
5. የግል።

25. <u>የዜጋው ሃይማኖት</u>

1. ምጽዋት፥ ጸሎት፥ ጾም።
2. ሀ) ዋጋው ከእግዚአብሔር ይከፈላል፥ ለ) ከሰው።
3. ሀ) ወደ ሰማያዊ አባት፥ ለ) ብቻውን ሆኖ የዓለምን ጉዳይ ከሐሳቡ በማስወገድ፥ ሐ) ለታይታ፥ በከንቱ ማነብነብ፥ ስለ እግዚአብሔር በትክክል አለማሰብ፥ ይቅር አለማለት።
4. ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤ በደላችንን ይቅር በለን፤ ከክፉ አድነን፤ ወደ ፈተና አታግባን።

26. <u>የዚጋው የዕለት ተዕለት ኑሮ</u>

1. ሀ) ገንዘብ የት እንደሚያከማች (ቍ.19-21) ሕይወቱን በምን እንደሚመራ (ቍ.22-23)፥ የማን አገልጋይ እንደሚሆን (ቍ.24)፥ ለ) ሀብቱ ለጊዜው የሚጠፋ ወይም ለዘላለም የማይጠፋ፥ ጠቅላላው ሕይወቱ ብርሃን ወይም ጨለማ፥ ጌታው እግዚአብሔር ወይም ገንዘብ ይሆናሉ።

2. ተስፋ ባለማድረግ (በሰማያዊ አባቱ)።

3. አባታችን ለትልቅ ነገር (ለሕይወት) ካሰበ ላነሰ ነገር እንዴት አያስብም (25)፤ አባታችን ለአነስተኛ ፍጥረት (ለወፍ) ካሰበ እንዴት አያስብልንም (26)፤ በመጨነቅ ምንም ለውጥ ለማምጣት እንደማይቻል (27)፤ አባታችን ለሚጠፋ አበባ ክብርን ከሰጠ እንዴት ለልጆቹ አብልጦ አይሰጥም (28-30)።

4. የመንግሥቱን ጉዳይና የእግዚአብሔርን ጽድቅ በማስቀደምና ለሚያስፈልገው ሁሉ በአባቱ ላይ ተስፋ በመጣል።

5. የግል።

27. <u>የዚጋው የዕለት ተዕለት ምርጫ</u>

1. ሀ) ጠባብ፥ ሰፊ፥ ለ) የቀጠነ፥ ሰፊ፥ ሐ) ሕይወት፥ ጥፋት፥ መ) ጥቂቶች፥ ብዙዎች።

2. የግል።

3. ሀ) ደህና ይመስላሉ፥ ለ) ነጣቂዎች፥ ሐ) ትክክለኛ ሊመስል ይችላል፥ መ) አመጸኝነት፥ ሠ) ክርስቶስ ከራሱ ያርቃቸዋል።

4. በዘወትር አስተያየት አንድ ይመስላሉ በፈተና ጊዜ ግን ይለያሉ። በዓለት ላይ የተሠራው መሠረት አለው፥ ለክርስቶስ ቃል ሁሉ ይታዘዛል። በአሸዋ ላይ የተሠራው መሠረት የለውም፥ ለክርስቶስ ቃል አይታዘዝም።

28. <u>የሰው ልጅ ሥልጣን</u>

1. በተፈጥሮ፥ በአጋንንት፥ በበሽታና በኃጢአት።

2. ሀ) ሰው፤ የእግዚአብሔር ልጅ፤ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ሥልጣንና ሰውን ለመፈወስ ኃይል ያለው መሆኑ፥ ለ) ሰዎችን ለማስከተል፥ የሰውን እምነትና ሐሳብ ለማወቅ የሚችል።

3. ሀ) ከእንስሳት የሰው መዳን እጅግ ይበልጣል፥ ለ) ከሥጋዊ የመንፈሳዊ ደኅንነት ይበልጣል፥ የተያያዙም ሊሆኑ ይችላሉ።

4. ተገረሙ፤ ፈሩ፤ እግዚአብሔርን አከበሩ።

5. የግል።

29. <u>መንግሥቱ የተስፋፋበት ስልት</u>

1. ሀ) ክርስቶስ ወይም ማናቸውም ወንጌል ሰባኪ፥ ለ) የመንግሥቱ ቃል።

2. ሀ) ደንዳና የሰው ልብ፤ ለቃሉ ምንም ቦታ የሌለው፥ ለ) ለጊዜው የሚቀበል ግን በጥልቀት ቃሉን የማይቀበል፥ ፈሪ ልብ፥ ሐ) የዓለም ጉዳይና የገንዘብ ፍቅር የተሞላበት ልብ፥ መ) አስተዋይ የሆነ ቃሉን የሚቀበል።

3. የግል።

4. የግል።

30. <u>የይፋ አገልግሎት አከሲል</u>

1. የግል አቀራረብ።

2. ሀ) ክርስቶስን ለማንገሥ፥ ለ) በእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን ስላመኑ፥ ምድራዊ ንጉሥ ሆኖ ከሮማ መንግሥት ነፃ እንዲያወጣቸው።

3. ሀ) እውነተኛ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንደሚገኝና እርሱን በመቀበል፥ ማለት በእርሱ በማመን፥ ሰው እንደሚድን፥ ለ) የግል።

31. <u>መንግሥቱና መስቀሉ</u>

1. ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን፥ ለ) የክርስቶስ ሞት አስፈላጊ መሆኑን።

2. ጴጥሮስ የሐዋርያት መሪ ሆኖ ወንጌልን በመስበኩ ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን አግብቶ ቤተ ክርስቲያንን እንዲመሠርት ነው። ስለ ጴጥሮስ ተከታይ ኢየሱስ አልተናገረም።

3. ራሱን መካድና ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል።

4. ይህን አድርጎ ነፍሱን ያድናል፥ እንደ ሥራውም ይቀበላል።

5. የግል።

32. <u>ሕግና ባልንጀራ</u>

1. እግዚአብሔርን በሁለንተናውና ባልንጀራውን እንደራሱ መውደድ።

2. የለም።

3. ሀ) ንዴት፥ ሥቃይ፥ ፍርሃት፥ ለ) ተስፋ ፥ የሃይማኖት ሰዎች ነበሩና፥ ሐ) ተስፋ ቢስነት፥ ሳምራዊ ነውና ምንም አያደርግልኝም፥ መ) መጽናናትና ምስጋና።

4. ሀ) ሌቦች በአካባቢው አሉና ሰውን መርዳት አደገኛ ነው፤ ከመቅደስ አገልግሎት ስለመጣሁ ወደዚህ ጉዳይ መግባት አይገባኝም፤ ቤቴ ሩቅ ነውና የአገልግሎት ዘመን (ስድስት ሳምንት) ከቤተ ሰቤ ተለይቼአለሁ፤ መሸብኝ፤ ከኔ በኋላ የሚከተለኝ ሌዋዊው ሊረዳው ይችላል፥ ለ) እንደ ካህኑ፥ ካህኑ አልረዳውምና፥ ሰውዬውን ብረዳው ካህኑ ይቀየምብኝ ይሆናል።

5. ርኅራኄው።

6. የግል።

33. <u>መልካም እረኛና በጎቹ</u>

1. ነፍሱን ስለ በጎቹ ይሰጣል፤ ያውቃቸዋል፤ ይመራቸዋል፤ ከአደጋ ይጠብቃቸዋል፤ የዘላለም ሕይወት ይሰጣቸዋል፤ አንድ መንጋ

ያደርጋቸዋል።

2. እረኛውንና ድምፁን ያውቃሉ።

3. ይተዋወቃሉ፤ ኢየሱስ አባቱን ያከብራል፤ ከእርሱም ትእዛዝንና ሥልጣንን ተቀበለ፤ ይህን ሲያደርግ በራሱ ፈቃድ ነበር። ኢየሱስ ከአብ ጋር አንድ ሲሆን በመለኮት (በአምላክነት) ና በባሕርይ፥ እንደዚሁም በፈቃድ አይለያዩም፤ ሆኖም በአካል፥ በግብርና በስም አንድ አይደሉም።

4. ከእግዚአብሔር ጋር ራሱን አንድ በማድረጉ።

5. የሚከተሉት ቢገኙበት ጥሩ ነው፥ ሀ) ኢየሱስ ለበጎቹ ሲል ነፍሱን ስለ አኖረ፥ መንገዱን ተከትዬ ድምጹን ስለምሰማ፥ ለ) ኢየሱስ ነፍሱን ስለ አነሣ፥ እንደ አባቱ ፈቃድ ስለሚሠራ፥ ፍጹም ኃይል ስላለውና ማንም ከእጁ በጎቹን ለመንጠቅ ስለማይችል ለዘላለም የእርሱ ስለምሆን።

34. <u>ወደ መጨረሻው መቅረብ</u>

1. ሀ) ኢየሱስ የሰማያዊቷ ጽዮን እውነተኛ ንጉሥ፥ ለ) ከእግዚአብሔር የመጣ መሲሕ፥ ሐ) ትንቢት የተነገረለት የዳዊት ልጅ መሆኑ።

2. ዘካ. 9፥9፤ መዝ. 117(118)፥ 25:26፤ ኢሳ.56፥7፤ ኤር. 7፥11፤ መዝ. 8፥2።

3. ጌታ (ቊ.3)፥ ንጉሥ (5)፥ የዳዊት ልጅ (9:15)፥ ነቢይ (11)።

4. የግል።

35. <u>የመጨረሻው እራት</u>

1. ሀ) ጴጥሮስንና ዮሐንስን ልኮ በድብቅ ከአንድ ሰው ጋር በምልክት ተገናኝተው በሚያሳያቸው ቤት እንዲያዘጋጁ በማዘዝ፥ ለ) ቦታው እንዳይታወቅ አለበለዚያ፥ እራቱን ሳይፈጽም ይያዝ ነበር።

2. ጥልቅ ደስታና ፍቅር፥ ምስጋና፥ ትካዜ።

3. ሀ) እንጀራ አመሰገነና ቆርሶም ሰጣቸው፥ ለ) ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፥ ሐ) ይህን ሥርዓት ለሞቱ መታሰቢያ እንዲያደርጉት።

4. ሀ) ይህ ጽዋ ስለ እናንተ የሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ ለ) ለኃጢአት መሥዋዕት መሆኑ፥ ሐ) አዲስ ኪዳን በሙሴ አማካይነት ተሰጥቶ የነበረውን የብሉይ ኪዳንን ሥርዓት የተካ መሆኑን።

5. የግል።

36. <u>መንገዱና አጽናኙ</u>

1. በአብ ዘንድ የሚገኝ መኖሪያና በክርስቶስ የተዘጋጀ ሥፍራ።

2. ኢየሱስ ራሱ መንገድ ነውና እርሱ ማን እንደሆነና እርሱን ራሱን በማወቅ ወደ አብ ሰው ይደርሳል። ሌላ መንገድ የለም።

3. የክርስቶስን አርአያ ይከተላል፤ ቃሉን ይጠብቃል፤ በክርስቶስ ስም ሲጸልይ መልስን ያገኛል፤ አጽናኝ የሚባለው መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ ሲገኝ በእውነት ይመራል፥ አብና ወልድ ከእርሱ ጋር ይሆናሉ፤ የልብ ሰላም ይኖረዋል።

4. ሀ) በክርስቶስ ጸሎት መሠረት ከአባቱ የተላከ፥ ለ) በክብር በሥልጣን እንደ ወልድ የሚተካከል (ቊ.16)፥ በክርስቶስ ስም የተላከ (26)፥ ሐ) በደቀ መዛሙርት የሚታወቅና የሚገኝ (17)፥ ሁሉን የሚያስተምራቸው፥ የክርስቶስን ቃል የሚያሳስባቸው (26)፥ መ) በዓለም ስለማይታይና ስለማይታወቅ ግንኙነት የለውም (17)።

37. <u>እስራትና ፍርድ</u>

1. ሀ) ኃጢአቱን ተረድቶ ንስሐ እንዲገባ፥ ለ) የክርስቶስ መንግሥት የሚገኘው በኃይል አለመሆኑንና፥ በእግዚአብሔር ኃይል እንዳለና ሁሉ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት በመፈጸም ላይ እንደነበረ እንዲረዳ፥ ሐ) ከፋታቸውን እንዲያስተውሉ።

2. የነቢያት መጻሕፍት።

3. ቀያፋ የሐሰት ምስክሮች አበዛ፥ ብዙ ተናገረ፥ ክርስቶስን በእግዚአብሔር አማለ፥ በአንድ ወቅት ራሱን ከሳሽና ዳኛ አደረገ፥ ልብሱን ቀደደ፥ ሸንጎው የሞት ፍርድ እንዲፈረድበት አደረገ፥ ሰዎች እንዲዘብቱበት ተዋቸው፤ ኢየሱስ ግን ዝም አለ፥ ቀያፋ ሲያምለው ብቻ መልስ ሰጠ፥ እውነተኛን ምስክርነት ሰጠ።

4. መሲህ (ክርስቶስ) እንደነበረና የዳንኤልን ትንቢት በመፈጸም ፍጹም አምላክ እንደነበረ።

5. ራሱን እግዚአብሔር በማድረጉ ተሳድቦአል ተባለ።

38. <u>ክህደትና ስቅለት</u>

1. ተገረፈ፥ ተዘበተበት፥ የእሾህ አክሊል ተደፋበት፥ ተመታ፥ ተሰቀለ።

2. ሀ) ወታደሮች፥ መንገደኞች፥ የካሕናት አለቆች፥ ጸሐፊዎች፥ ሽማግሌዎች፥ ሁለቱ የተሰቀሉት ወንበዴዎች፥ ለ) የክርስቶስ ጽድቅ ሕሊናቸውን ስለ ወቀሰ ደግሞም ይሉኝታ፥ እንዲሁም በወታደሮች ላይ የነበረ ተጽዕኖ።

3. ሀ) ክርስቶስ የበርባንን ሥፍራ እንደወሰደ ሁሉ የእኛንም ወስዶአል፥ ለ) ስምዖን መስቀልን ተሸክሞ ክርስቶስን እንደተከተለ፥ እኛም በክርስቶስ ምክንያት መከራን መቀበል አለብን።

4. የግል።

39. <u>ሕማምና ሞት</u>

1. በምድር ላይ ጨለማ ሆነ፤ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ተቀደደ፤ መሬት ተናወጠች፤ ከሞቱት ቅዱሳን ብዙዎች ተነሡና ታዩ።

2. አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውኸኝ ብሎ ጮኸና ሆምጣጤ ጠጣ፤ እንደገና ጮኾ ነፍሱን ሰጠ (ሞተ)።

3. የሚያሳድዱት ሊይዙት ሲመጡም አልሸሸም፤ ነፍሱን ተወ (ሞተ) በሚለው ቃል።

4. ሀ) የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መሰከረ፡ ለ) መሞቱንና መቀበሩን ተመለከቱ፥ ሐ) ከጲላጦስ የኢየሱስን ሥጋ ለምኖ በክብር

ቀበረው፥ መ) የኢየሱስን ሥጋ ለዮሴፍ ሰጠ፥ ሠ) መቃብሩን አትመው ዘብ አቆሙ።

5. የግል። (ማስታወሻውን ተመልከት።)

40. <u>ድልና ታላቁ ተልእኮ</u>

1. ሀ) የጌታን መልአክ፥ ለ) ለአለቆች ያዩትን ተናገሩ፥ ገንዘብም ተቀብለው እንደ አለቆች ውሸት ተናገሩ።
2. ሀ) መልአኩንና ኢየሱስን፥ ለ) ፈጥነው ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሔዱ! ኢየሱስ ሲያገኛቸው ቀረቡ፥ እግሩን ይዘው ሰገዱለት።
3. አሥራ አንዱና ሌሎች በተራራ ላይ ኢየሱስ ሲታያቸው ሰገዱለት። ኢየሱስ ተናገራቸው አዘዛቸውም።
4. በሰማይና በምድር ያለው ሥልጣን ሁሉ።
5. ሀ) ወደ ዓለም ሁሉ መሔድ፥ ሰዎችን በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ፥ ትእዛዛቱን ሁሉ እንዲጠብቁ ማስተማር ደቀ መዛሙርት ማድረግ፥ ለ) እርሱ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን።
6. የግል።

41. <u>የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ</u>

1. ለደቀ መዛሙርቱ ሕያው መሆኑን በብዙ ማስረጃ አረጋገጠላቸውና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አስረዳቸው።
2. በዓለም ሁሉ ምስክሮች እንዲሆኑ።
3. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል።
4. የግል።

42. <u>የመንፈስ ቅዱስ መውረድ</u>

1. እንደ አውሎ ነፋስ ድምጽ፥ እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች በእያንዳንዱ ላይ ተቀመጡ፥ በሌሎች ልሳኖች ተናገሩ።
2. አንዳንዶች ተገርመው «ይህ ምን ይሆን» ሲሉ፥ ሌሎችም እያፌዙባቸው «ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል» አሉ።
3. ከኢዩኤል 2፥28-32 ጋር፥ ሰሚዎቹ አይሁድ እንደ መሆናቸው መጠን ከሥተቱ የትንቢት ቃል ፍጻሜ መሆኑን ለማረጋገጥ።
4. የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ።
5. የግል።

43. <u>የቤተ ክርስቲያን አኗኗር</u>

1. ክርስቶስ ወደ ሰማይ ዐርጎ በአባቱ ቀኝ መቀመጡን፥ ከአብ መንፈስ ቅዱስን ለማፍሰስ መቀበሉንና እግዚአብሔርን የሁሉ ጌታ ማድረጉን።
2. ንስሐ መግባትና በኢየሱስ ስም መጠመቅ።
3. የኃጢአት ይቅርታና መንፈስ ቅዱስ።
4. ሰዎቹ ሲያምኑ ተጠመቁ፥ የሐዋርያትን ትምህርት ተቀበሉ፥ በኅብረታቸው ተደሰቱ፥ በአንድነት በሉ፥ በጸሎት ተጉ፥ በአንድነት ኖሩ፥ በመቅደስ በየቀኑ ተሰበሰቡ፥ አመሰገኑ፥ በአሕዛብ ፊት ሞገስ ነበራቸው፥ ተአምራት ተደረጉ፥ ሰዎች በየቀኑ ዳኑ።

44. <u>የአሕዛብ ሐዋርያ</u>

1. ወደ ደማስቆ ሲቀርብ በብዙ ብርሃን ውስጥ አነጋገረው። ምእመናንን በማሳደድ ኢየሱስን እንዳሳደደ ገለጠለትና፥ ሳውል ለመታዘዝ ፈቃደኛ መሆኑን ሲገልጥ ወደ ከተማ ገብቶ ምእመናን መንገዱን እንደሚያሳዩት ነገረው።
2. ዕውር ሆኖ ለ3 ቀን፥ ሳይበላና ሳይጠጣ ጸለየ።
3. ሳውል የተባለ በይሁዳ ቤት እንደሚጸልይ፤ ሐናንያ በራእይ እንዳየ፤ በአሕዛብ፥ በነገሥታትና በእስራኤል ሰዎች ዘንድ የክርስቶስን ስም የሚያሳውቅ የተመረጠ ዕቃ መሆኑ፤ ስለ ክርስቶስ ብዙ መከራን እንደሚቀበል።
4. እጁን ጭኖበት ሳውል እንዲያይ፥ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበልና እንዲጠመቅ አደረገ።
5. የግል።

45. <u>ከአሕዛብ የመጀመሪያው ክርስቲያን</u>

1. አሕዛብ በእግዚአብሔር ይወደዳሉ፤ ወንጌል በኢየሱስ ለእስራኤል ተሰበከ፤ እርሱ ግን የሁሉ ጌታ ነው፤ እግዚአብሔር ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስና በኃይል ቀባው፤ እርሱ መልካም አደረገ፥ በሰይጣን የተገዙትን ፈወሰ፤ አይሁድ ሰቅለው ገደሉት፤ እግዚአብሔር ግን አስነሣው፥ ከሐዋርያትም ጋር እየታየ በላ ጠጣም፤ እርሱ በሕያዋንና በሙታን ይፈርዳል፤ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ እንደ ነቢያት ቃል የኃጢአትን ይቅርታ ይቀበላሉ።
2. መንፈስ ቅዱስን ለእስራኤል ሰዎች እንደሰጠ፥ ለአሕዛብም ደግሞ በመስጠቱ።
3. በውኃ እንዲጠመቁ አደረገ።
4. በግል።

46. <u>ወንጌል በአውሮፓ</u>

1. ሀ) እግዚአብሔርን የምታመልክ፥ ሃብታም ነጋዴ፥ ባለ ቤተ ሰብ፥ ለ) አገልጋይ ወደፊት የሚሆነውን ነገር በጥንቆላ የምትናገር፥ ርኩስ መንፈስ ያደረባት፥ ለጌቶችዋ ብዙ ትርፍ የምታስገኝ፥ ሐ) ታዛዥ ሠራተኛ፥ ኃይለኛ፥ ጨካኝ፥ የወህኒ ዘበኛ።
2. ሀ) የጳውሎስን ትምህርት ስትሰማ ጌታ ልብዋን ከፈተላትና ተጠመቀች፥ ለ) ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ርኩስ መንፈሱ እንዲወጣ አዘዘ፥ ሐ) በምድር መናወጥ ነቃ፤ እስረኞች እንዳያመልጡ ፈራ፤ ከጳውሎስም የወንጌልን ቃል ሰምቶ ተቀበለና በዚያ ሌሊት ተጠመቀ።
3. ሀ) ልድያና ቤተ ሰቦችዋ ሁሉ አመኑና ጳውሎስንና ጓደኞቹን ሁሉ ወደ ቤቷ አስገባች፥ ለ) ከጌቶችዋ የተለየች ይመስላል፥ ሐ) በጳውሎስና በሲላስ ላይ የነበራቸውን አስተያየት ሁሉ ለወጡ፤ በወንጌልም ሐሴት አደረጉ።

47. <u>ወንጌል በኤፌሶን</u>

1. በዮሐንስ ጥምቀት የተጠመቁ ደቀ መዛሙርት፣ አይሁድ፣ አሕዛብ።
2. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና ስለ መንፈስ ቅዱስ ግንዛቤ አልነበራቸውም፤ በሕይወታቸው የመንፈስ ቅዱስ መገኘት።
3. መንፈስ ቅዱስ ሲወርድላቸው፣ በትንቢትና በልሳን መናገራቸው፣ ተአምራትና የሰዎች መፈወስ፣ አጋንንት ስለ ኢየሱስ የሰጡት ምስክርነት፣ የአስማተኞች መጻሕፍት መቃጠል፣ የጌታ ቃል መስፋፋት።

48. <u>ወንጌል በሮሜ</u>

1. ደስታ፣ ምስጋና፣ መጽናናት።
2. በራሱ ቤት እየኖረ የአይሁድን አለቆች ጠርቶ ወንጌልን ሰበከላቸው፣ በኋላም ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ እየተቀበለ ስለ ክርስቶስ አስተማረ።
3. ሀ) ወንጌልን መጀመሪያ ለአይሁድ በኋላም ለአሕዛብ በሐደበት ሁሉ ሰበከ፣ ለ) በብዙ ቦታ ቤተ ክርስቲያንን ተከለ፣ በኋላም ጐበኛቸው፣ ጻፈላቸውም፣ ሐ) ሰዎች በእምነት ብቻ እንደሚድኑ ተከራከረና አብያተ ክርስቲያን ሁሉ ይህን እንዲቀበሉ አደረገ (የሐዋርያት ሥራ ም.15)፣ መ) ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ 13ቱ (ወይም ምናልባት 14) በእርሱ ተጻፉ፣ እነርሱም የወንጌልን ትምህርት ሁሉ ያብራራሉ።

49. <u>የወንጌል መልእክት</u>

1. ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስን፣ ለ) መሞቱና መነሣቱ፣ የሰው መዳን በነዚህ ሁለት ነገሮች ስለ ተመሠረተ።
2. የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ድንገተኛ አልነበረም፣ ከጥንት የተተነበየለት የእግዚአብሔር ዕቅድ መሆኑን ለማረጋገጥና አይሁድ የሃይማኖታቸውን ፍጻሜ በክርስቶስ እንዲያገኙ።
3. ጴጥሮስ (ኬፋ)፣ 12ቱ፣ 500 የክርስቶስ ተከታዮች፣ ያዕቆብ፣ ሐዋርያት በሙሉ፣ ጳውሎስ።
4. የጌታን ሕያውነት እንደ መካድ ይቈጠራል፣ የሐዋርያትን ስብከት ከንቱ ያደርጋል ሐሰተኞችም ያደርጋቸዋል፣ እምነትን ከንቱ ያደርጋል፣ አማኞች የኃጢአት ስርዬትን አልተቀበሉም፣ በክርስቶስ እምነት የሞቱ ጠፍተዋል ያሰኛል፣ ምዕመናንን ምስኪኖች ያደርጋቸዋል።
5. የግል።

50. <u>የእግዚአብሔር ዕቅድ</u>

1. በክርስቶስ ባረካቸው፣ መረጣቸው፣ ወሰናቸው።
2. ሀ) በጎ ፈቃዱ፣ ለ) አማኞች የእርሱ ልጆች እንዲሆኑና ለጸጋ ክብር ምስጋና እንዲሆኑ፤ በመጨረሻ ሁሉን በክርስቶስ ለማጠቃለል።
3. አማኞች በክርስቶስ ናቸው ማለት ከእርሱ ጋር አንድ ሆነው ይቈጠራሉ፤ የኃጢአትን ይቅርታ እንዲቀበሉ ሞተላቸው፤ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ በእርሱ ሥር ይገኛል፤ በክርስቶስ ያለው ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ይሆናል።
4. ያትመዋል (የእግዚአብሔር መሆኑን ያረጋግጣል)፤ የሰማያዊ ርስቱ መያዣና ዋስትና ነው።
5. የግል።

51. <u>የሰው ደኅንነት</u>

1. በበደሉና በኃጢአቱ የሞተ፣ በማይታዘዙት መካከል የሚኖር፣ በሰይጣን ፈቃድ የሚመላለስ፣ የሥጋን ፈቃድ የሚያደርግ፣ የቍጣ ልጅ።
2. ሀ) ምሕረቱ፣ ፍቅሩ፣ ጸጋው፣ ለ) ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፣ አስነሣን፣ በሰማያዊ ስፍራ አስቀመጠን፣ ሐ) የጸጋውን ባለጠግነት ማሳየት።
3. በመንፈስ የሞተ ነው፣ በሰይጣን ይመራል፣ በኃጢአት ይገዛል፣ በማይታዘዙት መካከል ይኖራል፤ ደኅንነት ከጸጋ ነው።
4. ጸጋ →አዲስ ሕይወት →እምነት → ሥራ። ይህ አዲስ ሕይወት አማኙ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ መሆኑ ወይም በእርሱ በመፈጠሩ የተገኘ ነው፤ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆኑን በማመኑ ይገልጣል፣ እምነቱ እውነተኛ መሆኑ የሚታወቀው የእግዚአብሔርን ሥራ በመሥራቱ ነው።

52. <u>የደኅንነት ውጤት</u>

1. ሰላም የሌለው፤ ደካማ፣ ኃጢአት ያለበት፣ ከቍጣ በታች፣ የእግዚአብሔር ጠላት።
2. በክርስቶስ ሞት (ደም) መሠረት በእምነት አማካይነት።
3. ሰላም፣ ጸጋ፣ ተስፋ፣ ከመከራ የሚገኝ ትእግሥት፣ መጽናት፣ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ የእግዚአብሔር ፍቅርና አለኝታ።
4. በልባችን ያለ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፣ የክርስቶስ ሞት።

53. <u>የቅድስና መንገድ</u>

1. በክርስቶስ ኢየሱስ ሲገኝ።
2. በሥጋ መኖር ፦ የሥጋን ነገር ማሰብ፣ ውጤቱ ሞት፣ ለሕግ አለመታዘዝ፣ እግዚአብሔርን አለማስደሰት። በመንፈስ መኖር ፦ የመንፈስን ነገር ማሰብ፣ ውጤቱ ሕይወትና ሰላም፣ መታዘዝ፣ እግዚአብሔርን ማስደሰት።
3. የግል። እንደ ቍ.5-8 ትምህርት ሥጋ የሚገደለው በተለይ በሰውነት ውስጥ ለሚገኘው ኃጢአታዊ ምኞት የሚፈልገውን ባለመስጠት ነው።
4. ሀ) በእግዚአብሔር መንፈስ መመራታቸው፣ ከፍርሃት ነጻ መውጣታቸው፣ ከራሳቸው መንፈስና ከእግዚአብሔር መንፈስ ምስክርነት የተነሣ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸው፣ ለ) መከራ ተቀብለው ከክርስቶስ ጋር ደግሞ አብረው የእግዚአብሔር ወራሾች መሆናቸው።

54. <u>የአማኝ ዋስትና</u>

1. ሀ) ሥቃይ፣ ከንቱነት፣ ባርነት፣ መቃተት፣ ሞት፣ ለ) የእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ፣ የሰውነታቸው ቤዛ ማለት የሁለንተናቸው ነፃ መሆን።
2. ማወቅ፣ መወሰን፣ መጥራት፣ ማጽደቅ፣ ማክበር።
3. እግዚአብሔር ስለሚወደንና ሁሉን እንደ ሀሳቡ ስለሚፈጽም በእምነት ልናውቅ ይገባናል።
4. የግል።
5. እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ኃያል ስለሆነ፣ ልጁን አሳልፎ ለእኛ በመስጠቱ ከእርሱ ጋር ሁሉን ስለሚሰጠን፣ እርሱ ስለሚያጸድቀን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ሆኖ ስለሚማልደን።

55. <u>አማኙና የግል ሕይወቱ</u>

1. ሀ) ሁለንተናን ለእግዚአብሔር እንደ ሕያው መሥዋዕት ማቅረብ፣ ለ)የዓለምን ሰዎች አስተሳሰብና አካሔድ አለመምሰልና አለመከተል፣ ሐ) በወንጌል መሠረት አሳብን ለውጦ በቅድስና መንገድ መራመድ።
2. ሀ) በአካልና በሕዋሳቶቹ፣ ለ) እንደ እምነት መጠን፣ በማስተዋል፣ በትህትና በጸጋ እንደተሰጠ ስጦታ፣ በኃይል መንፈስ መሥራት።
3. ሀ) ግብዝነት የሌለበት ፍቅር፣ በጎውን ነገር መውደድ፣ በሙሉ ልብና በኃይል መንፈስ መሥራት፣ ለጌታ መገዛት፣ የሚያሳድዱንን መመረቅ፣ በሰላም መኖር፣ በተስፋ መደሰት፣ በመከራ መታገሥ፣ በጸሎት መጽናት፣ እንግዶችን መቀበል፣ ለጠላት መልካም ማድረግ፣ ለ) ክፉውን ነገር መጥላት፣ ስንፍናን ማስወገድ፣ የሚያሳድዱንን አለመርገም፣ በክፉ ፈንታ ክፉ አለመመለስ፣ አለመበቀል።
4. የግል።

56. <u>አማኙና ቤተ ክርስቲያኑ</u>

1. ሀ) በክርስቶስ ነው፣ ለ) ሕይወቱ መንፈሳዊ ነውና በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ይገለጣል፣ ሐ) በአባሎች መካከል ልዩነት የለም።
2. ልዩ ልዩ ዓይነት ብልግና (ቍ.5)፣ ልዩ ልዩ ክፉ ምኞት (5)፣ ቍጣ፣ ንዴት፣ ስድብ፣ የማይገባ ንግግር፣ ውሸት (8፡9)፣ ኩራት፣ ይቅር አለማለት (12፡13)፣ ለ) የግል ሐ) የግል።
3. ሀ) ፍቅር፣ አንድነት፣ ሰላም፣ የእግዚአብሔርን ቃል በጥበብ እርስ በርስ ማስተማር፣ ከልብ ለእግዚአብሔር መዘመር፣ ምስጋና፣ ሁሉን በክርስቶስ ስም ማድረግ፣ ለ) የግል።

57. <u>አማኙና ቤተ ሰቡ</u>

1. በጥንቃቄና በጥበብ መኖር፣ ጊዜውን በበጎ ነገር ማሳለፍ፣ የጌታን ፈቃድ ማወቅ፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት፣ በኅብረት መዘመር፣ ምስጋናን ማዘውተር፣ ለሌሎች ሁሉ በክርስቶስ ፍርሃት መገዛት።
2. ሀ) በማኅኙነት ፈንታቸው (ድርሻቸው) ራስ ሆነው፣ ሌላውን መውደድ፣ ራሳቸውን አሳልፈው መስጠት፣ ሌላውን ማዳን ነው፣ ለ) በማኅኙነት ድርሻቸው መገዛት፣ ማክበር፣ መፍራት ነው።
3. ሀ) በክርስቶስ ፍርሃት ለጌታ እንደሚገዙ በመቍጠር፣ ለ) ለክርስቶስ ስለሚሆን፣ ባሎችና ወላጆች ስለሚወዱአቸው፣ የበረከት መንገድ ስለሆነ።
4. የግል።

58. <u>አማኙና መተላለፉ</u>


1. ኃጢአት እየሠራ ቢኖር ኅብረት ከእግዚአብሔር ጋር እንደሌለው፤ ኃጢአት እንዳለበት፤ ኃጢአት እንዳደረገ።
2. ሀ) እግዚአብሔር ብርሃን (ቅዱስና ንጹህ) መሆኑን፤ ንስሐ ለሚገቡ ይቅር ማለቱን፣ ታማኝና ጻድቅ መሆኑን፣ ለ) የክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ማንጻቱን፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ጠበቃነቱን፣ ለሰው ሁሉ የኃጢአት ማስተስሪያ፣ ሐ) ኃጢአተኛ መሆኑንና ኅብረት ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ምእመናን ጋር የሚገኘው በብርሃን ሲመላለስ መሆኑን።
3. ኃጢአቱን መናዘዝና ሕይወቱን ሁሉ ለእግዚአብሔር ብርሃን መክፈት።
4. ክርስቶስ እንደኖረ መኖር ያስፈልጋል፣ ይህም ትእዛዛቱን በመጠበቅና እንደ እግዚአብሔር ቃል በመመላለስ ነው።


59. <u>አማኙና ጠባቡ መንገድ</u>


1. ክርስቶስ ነውርን መናቁንና መከራን መታገሡን፣ ወደ ፊት ያለውን ደስታ መመልከቱን ማስተዋል።
2. ሀ) በቅድስና እንድናድግ፣ ለ) ሰላም የሞላበት የጽድቅ ሕይወት፣ ሐ) የጌታ ውድ ልጆች መሆናችን።
3. ተስፋ መቍረጥ፤ ስሕተትን አለማስተካከል፣ ጥሩ መንገድ አለመፈለግ፣ ሰላምን አለመከታተል፣ በቅድስና ለመኖር አለመትጋት፣ መራራነት።
4. የግል።


60. <u>አማኙና ተስፋው</u>

1. በጉ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ወንዙና የሕይወት ዛፍ ፦ የዘላለም ሕይወት፤ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ፦ አማኞች ናቸው፣ ለ) እግዚአብሔር፣ ክርስቶስ፣ መንፈስ ቅዱስና አማኞች ሁሉ፣ ሐ) ክርስቶስን ያመልካሉ፤ ያያሉ፤ ከእርሱም ጋር ይነግሣሉ፣ መ) መርገም፣ ባዕድ አምልኮ፣ ኃጢአት፣ ሠ) ኃጢአትን የሚሠሩ፣ ባዕድ አምልኮን የሚከተሉ ሁሉ።
2. ሀ) አልፋና ዖሜጋ፤ የዳዊት ሥርና ዘር፣ የንጋት ኮከብ፣ ለ) ሽልማት (ዋጋ) ይዞ በፍጥነት በመምጣት ላይ።
3. ሀ) መንፈስ ቅዱስ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ለዮሐንስ የተናገረው መልአክ (ቍ.8)፣ ዮሐንስ። ለ) የግል።
4. ሀ) ሁሉም በመቀበል አንድም ነገር ባለመጨመር፣ ለ) የግል፣ ሐ) የግል።


አብርሃም
የተዘዋወረባቸው አገሮች
ቆጵሮስ
ሜድትራኒያን
መስጴጦምያ
አሦር
አራም
ሜዶን
ደማስቆ
ከለዳውያን
ሞአብ
ኤዶም
ዐረብ
ኪሎሜትር
50 100 200 300 400


ሐዋርያው ጳውሎስ
የተዘዋወረባቸው አገሮች
መቄዶንያ
ቢታንያ
ጳንጦስ
እስያ
ገላትያ
ቀጰዶቅያ
ቀርጤስ
ቆጵሮስ
ሜድትራኒያን
ማልታ
ቀሬና
ግብጽ
ዐረብ
ደማስቆ
እስክንድርያ
ኪ. ሜትር
50 100 200 300 400


1. ሮቤል
2. ስምዖን
3. ይሁዳ
4. ዛብሎን
5. ይሳኮር
6. ዳን
7. ጋድ
8. አሴር
9. ንፍታሌም
10. ኤፍሬም
11. ምናሴ
12. ብንያም
የእስራኤል ነገዶች
የሰፈሩባቸውን በታዎች የሚያሳይ
የእስራኤል አገር ካርታ
5 10 20 40 60 80


የእስራኤል አገር
በዐዲስ ኪዳን ዘመን
5 10 20 40 60 80

## መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ

ክርስትና በኢትዮጵያ ከተሰበከበት ከ4ኛው መቶ ዘመን፣ በተለይም «ዘጠኙ ቅዱሳን» የተባሉት መምህራን ወደ ኢትዮጵያ ከመጡበት ከ5ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት በግዕዝ ቋንቋ ተተርጉመው በየቤተ ክርስቲያኑና በየገዳሙ ተሰራጩ፣ በአገራችን ለክርስትና ሃይማኖት መስፋፋትም መሣሪያ ሆኑ። ግዕዝ በሕዝቡ ዘንድ እየተረሳ፣ አማርኛም በሰሜን ኢትዮጵያ እየተስፋፋ በመሔዱ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ አማርኛ መተርጐም አስፈላጊ ሆነ።

ይህን ሁኔታ የተመለከተው የብሪታኒያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ አባ አብርሃም (አባ-ሮሚ) የተባለ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ካይሮ ውስጥ ወደ አማርኛ የተረጐመውን መጽሐፍ ቅዱስ ገዝቶ፣ በ1832 ዓ.ም. አሳተመው። የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናዊ ማኅበርም መጽሐፉን የሚያስረጩ መልእክተኞችን ወደ ሰሜን ኢትዮጵያና ወደ ሸዋ በመላክ የአማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት ለሊቃውንትና ማንበብ ለሚሉ ኢትዮጵያውያን እንዲደርሱ አደረገ።

በቅርቡ ዘመንም፣ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት፣ በዕብራይስጥ፣ በጽርዕ (በግሪክ)፣ በግዕዝና በአማርኛ ምሁራን አማካይነት አዲስ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ተዘጋጅቶ በ1953 ዓ.ም. አዲስ አበባ ታተመ። ከዚያም በኋላ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አማካይነት ቀለል ባለ አማርኛ ተተርጉሞ በ1980 ዓ.ም. ሌላ ታተመ።

መጽሐፍትን የማሳተም ብልሐት ከተከሠተበት ከ15ኛው መቶ ዘመን ወዲህም መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ወይም በከፊል ከ2000 በላይ በሆኑ የዓለም ኅብረተሰብ ቋንቋዎች ተተርጉሞና በብዙ ሚልዮን ቅጅ ታትሞ በየዓመቱ ለሕዝቦች ሁሉ እንዲደርሱ በመደረግ ላይ ነው።

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች በኩልም መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ወይም በከፊል 20 በሚደርሱ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ይገኛል። በስዊድን ወንጌላዊት ሚስዮን አማካይነት፣ መጽሐፍ ቅዱስ በአናሲሞስ ነሲብ ወደ ኦሮምኛ፣ በ1891 ዓ.ም. ሲተረጐም፣ በአለቃ ተወልደ መድኅን ገብሩ ደግሞ በ1948 ዓ.ም ወደ ትግርኛ ተተርጉሞአል። ዛሬም የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ከአብያተ ክርስቲያናትና ከሌሎችም መሰል ድርጅቶች ጋር በመተባበር መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በመተርጐም ላይ ይገኛል። ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ይበልጥ በሚረዱት ቋንቋ አዘጋጅቶ ለማቅረብ የሚደረገው ጥረት ግቡን እንዲመታ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርን ይርዱ በረከትን ያገኙበታልና።

## በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በምድረ በዳ መና እንዲበሉ በሰጣቸው ጊዜ እያንዳንዱ ሰው ለምግብ የሚያስፈልገውን መጠን እንዲሰበስብ አዘዘ። በዚህ ዓይነት እያንዳንዱ ሰው ለዕለት ምግቡ በእግዚአብሔር ላይ ብቻ በመደገፍ እያንዳንዱን ቀን ጀመረ።ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን «የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ» በማለት ለመጸለይ ባስተማራቸው ጊዜ ይህንን እውነት እንደገና አረጋግጦታል። ዳቦ ለሥጋችን እንደሚያስፈልግ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ለነፍሳችን እጅግ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» ተብሏልና። ስለዚህ እዚህ ላይ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት መሠረታዊ የሆነ መመሪያ እንዳለ መረዳት እንችላለን። ክርስቲያን ሁሉ ለእግዚአብሔር በመታዘዝና በእርሱም ተደግፎ መኖርን እንዲማር በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊ ምግብ ማግኘት ያስፈልገዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሕያው ቃል ሲሆን በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ በወተት (1ጴጥ.2፣2-3)፣ የአኗኗራችንን መንገድ በሚያሳይ እውነተኛ ብርሃን (መዝ.118፣105)፣ የሰይጣንን ውጊያ ለመመከት በሚያስችል ሰይፍ (ኤፌ.6፣17)፣ መንፈሳዊ ደንዳንነታችንን በሚሰብር መዶሻና ልባችንን በሚያቃጥልና በሚያነፃ እሳት (ኤር.23፣29) ተመስሏል።

ይህ የጥናት መጽሐፍ ጥያቄዎችንና ማስታወሻዎችን በማከተት በየዕለቱ በሚከናወኑ የማንበብ መርሐ ግብሮች አማካይነት መላውን መጽሐፍ ቅዱስ የሚሸፍን «በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር» ለተሰኘው የአራት ዓመት ኮርስ መግቢያ በመሆን ተዘጋጅቶአል። ይኸውም በዘወትር ሕይወትህ አንተም አምላክህን በብቃትና በታማኝነት ለማገልገል የሚያስፈልግህን ምግብና መሣሪያ ማግኘት እንደሚያስችልህ ተስፋ በማድረግ ነው።

ጥናቱን ለመጀመር እንዲረዳህ የመጀመሪያው ዓመት የጥናት ቅደም ተከተል (ዝርዝር) በየዕለቱ ለምታደርገው ንባብ የምትጠቀምበት ቀላል መመሪያ በሚቀጥሉት ሁለት ገጾች ላይ ይገኛል። ይህንኑ የጥናት ዝርዝርና መመሪያ ለይተህ በማውጣትና በመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ አጥፈህ በማስቀመጥ ብትጠቀምበት ሊረዳህ ይችላል።

# በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር - 1ኛ ዓመት

የዚህ ፕሮግራም (መርሐ-ግብር) ዓላማ፥ እንደ ክርስቲያን [illegible] መጽሐፍ ቅዱስ [illegible] የእግዚአብሔርን [illegible] እንድናድግ እንዲረዳ ነው።

ፕሮግራሙ [illegible] ለአራት ዓመታት [illegible] ከእግዚአብሔር ጋር [illegible]።

## የንባብ ቅደም ተከተል

1. መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ በአራት ዓመታት ይነበባል።
2. እያንዳንዱ መጽሐፍ [illegible] ... [illegible] የንባብ [illegible]።
3. [illegible] ጊዜ መዝሙረ ዳዊት [illegible] ይነበባል።

## የዕለት የንባብ መመሪያ

ጸልዩ! [illegible] እግዚአብሔር [illegible]።
[illegible] ምንባቡን [illegible] ጊዜ [illegible]።
መጠይቅ

1. ምንባቡ ፦
   ሀ) ስለ [illegible] ስለ [illegible] ስለ [illegible]።
   ለ) ስለ ሰው ስለ ኃጢአት ስለ ፍርድ።
   ሐ) ስለ መዳን ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ።
   መ) ስለ ክርስቲያን ኑሮ ምን ያስተምራል?
2. ምንባቡ [illegible]?
3. [illegible]?
   ጸልዩ! [illegible]።
   ጸልዩ! [illegible] እግዚአብሔር [illegible]።

## የምንባብ አጠቃቀም

መዝ.1. ማለት መዝሙረ ዳዊት መዝሙር አንድ ማለት ነው። ዘፍ.1፥1-25 ማለት ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ከቁጥር 1 እስከ ቁጥር 25 ማለት ነው። ዘፍ.11፥27-12፥20 ማለት ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 11 ከቁጥር 27 እስከ ምዕራፍ 12 ቁጥር 20 ማለት ነው።

በዚህ ዓመት የሚነበቡ መጻሕፍት መዝሙረ ዳዊት(መዝ.) 1-50(51)፥ ኦሪት ዘፍጥረት(ዘፍ.)፥ የሉቃስ ወንጌል (ሉቃ.)፥ [illegible]፥ [illegible]፥ [illegible]፥ [illegible]፥ [illegible] 1ኛ [illegible]፥ 2ኛ [illegible]፥ [illegible] 1ኛ [illegible] ናቸው።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
የፖ.ሣ.ቁ. 1252
ስ.ቁ. 518233
አዲስ አበባ

| ቀን | ሳምንት 1 | ሳምንት 2 | ሳምንት 3 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.1 | መዝ.2 | መዝ.3 |
| ሰ | ዘፍ.1፥1-25 | ዘፍ.4 | ዘፍ.10 |
| ማ | ዘፍ.1፥26-31 | ዘፍ.5 | ዘፍ.11፥1-26 |
| ረ | ዘፍ.2፥1-17 | ዘፍ.6 | ሉቃ.1፥1-25 |
| ሐ | ዘፍ.2፥18-25 | ዘፍ.7 | ሉቃ.1፥26-56 |
| ዓ | ዘፍ.3፥1-13 | ዘፍ.8 | ሉቃ.1፥57-80 |
| ቅ | ዘፍ.3፥14-24 | ዘፍ.9 | ሉቃ.2፥1-20 |
| | **ሳምንት 4** | **ሳምንት 5** | **ሳምንት 6** |
| እ | መዝ.4 | መዝ.5 | መዝ.6 |
| ሰ | ሉቃ.2፥21-39 | ዘፍ.11፥27-12፥20 | ዘፍ.18 |
| ማ | ሉቃ.2፥40-52 | ዘፍ.13 | ዘፍ.19 |
| ረ | ሉቃ.3፥1-20 | ዘፍ.14 | ዘፍ.20 |
| ሐ | ሉቃ.3፥21-38 | ዘፍ.15 | ዘፍ.21 |
| ዓ | ሉቃ.4፥1-15 | ዘፍ.16 | ዘፍ.22 |
| ቅ | ሉቃ.4፥16-30 | ዘፍ.17 | ዘፍ.23 |
| | **ሳምንት 7** | **ሳምንት 8** | **ሳምንት 9** |
| እ | መዝ.7 | መዝ.8 | መዝ.9፥1-20 |
| ሰ | ዘፍ.24 | ዘፍ.30 | አሞ፡ 1፥1-2፥5 |
| ማ | ዘፍ.25 | ዘፍ.31 | አሞ፡ 2፥6-16 |
| ረ | ዘፍ.26 | ዘፍ.32 | አሞ፡ 3 |
| ሐ | ዘፍ.27 | ዘፍ.33 | አሞ፡ 4 |
| ዓ | ዘፍ.28 | ዘፍ.34፥1-35፥15 | አሞ፡ 5 እና 6 |
| ቅ | ዘፍ.29 | ዘፍ.35፥16-36፥43 | አሞ፡ 7፥1-8፥3 |
| | **ሳምንት 10** | **ሳምንት 11** | **ሳምንት 12** |
| እ | መዝ.9(10)፥21-38 | መዝ.10(11) | መዝ.11(12) |
| ሰ | አሞ፡ 8፥4-14 | ሉቃ.6፥12-36 | ሉቃ.8፥22-39 |
| ማ | አሞ፡ 9 | ሉቃ.6፥37-49 | ሉቃ.8፥40-56 |
| ረ | ሉቃ.4፥31-44 | ሉቃ.7፥1-17 | ሉቃ.9፥1-27 |
| ሐ | ሉቃ.5፥1-11 | ሉቃ.7፥18-35 | ሉቃ.9፥28-62 |
| ዓ | ሉቃ.5፥12-26 | ሉቃ.7፥36-50 | ዘፍ.37 |
| ቅ | ሉቃ.5፥27-6፥11 | ሉቃ.8፥1-21 | ዘፍ.38 |
| | **ሳምንት 13** | **ሳምንት 14** | **ሳምንት 15** |
| እ | መዝ.12(13) | መዝ.13(14) | መዝ.14(15) |
| ሰ | ዘፍ.39 | ዘፍ.45 | ሉቃ.10፥1-24 |
| ማ | ዘፍ.40 | ዘፍ.46 | ሉቃ.10፥25-42 |
| ረ | ዘፍ.41 | ዘፍ.47 | ሉቃ.11፥1-13 |
| ሐ | ዘፍ.42 | ዘፍ.48 | ሉቃ.11፥14-36 |
| ዓ | ዘፍ.43 | ዘፍ.49 | ሉቃ.11፥37-12፥3 |
| ቅ | ዘፍ.44 | ዘፍ.50 | ሉቃ.12፥4-34 |
| | **ሳምንት 16** | **ሳምንት 17** | **ሳምንት 18** |
| እ | መዝ.15(16) | መዝ.16(17) | መዝ.17(18) |
| ሰ | ሉቃ.12፥35-59 | ሉቃ.16፥1-15 | ሉቃ.18፥31-43 |
| ማ | ሉቃ.13፥1-21 | ሉቃ.16፥16-31 | ሉቃ.19፥1-10 |
| ረ | ሉቃ.13፥22-35 | ሉቃ.17፥1-19 | ሉቃ.19፥11-28 |
| ሐ | ሉቃ.14፥1-35 | ሉቃ.17፥20-37 | ዮና.1 |
| ዓ | ሉቃ.15፥1-10 | ሉቃ.18፥1-17 | ዮና.2 |
| ቅ | ሉቃ.15፥11-32 | ሉቃ.18፥18-30 | ዮና.3 |

| | ሳምንት 19 | ሳምንት 20 | ሳምንት 21 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.18(19) | መዝ.19(20) | መዝ.20(21) |
| ሰ | ዘጸ.4 | ዘጸ.10 | ዘጸ.17 |
| ማ | ዘጸ.5 | ዘጸ.11፥1-12፥20 | ዘጸ.18 |
| ረ | ዘጸ.6 | ዘጸ.12፥21-13፥16 | ሆሴዕ 1 እና 3 |
| ሐ | ዘጸ.7 | ዘጸ.13፥17-14፥31 | ሆሴዕ 2 |
| ዓ | ዘጸ.8 | ዘጸ.15፥1-21 | ሆሴዕ 4 |
| ቅ | ዘጸ.9 | ዘጸ.15፥22-16፥36 | ሆሴዕ 5 እና 6 |

| | ሳምንት 22 | ሳምንት 23 | ሳምንት 24 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.21(22) | መዝ.22(23) | መዝ.23(24) |
| ሰ | ሆሴዕ 7 እና 8 | ዘጸ.19 | ዘጸ.25 |
| ማ | ሆሴዕ 9 | ዘጸ.20 | ዘጸ.26 |
| ረ | ሆሴዕ 10 | ዘጸ.21 | ዘጸ.27 |
| ሐ | ሆሴዕ 11 እና 12 | ዘጸ.22 | ዘጸ.28 |
| ዓ | ሆሴዕ 13 | ዘጸ.23 | ዘጸ.29፥1-37 |
| ቅ | ሆሴዕ 14 | ዘጸ.24 | ዘጸ.29፥38-30፥38 |

| | ሳምንት 25 | ሳምንት 26 | ሳምንት 27 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.24(25) | መዝ.25(26) | መዝ.26(27) |
| ሰ | ዘጸ.31፥1-32፥14 | ሉቃ.19፥29-48 | ሉቃ.22፥24-46 |
| ማ | ዘጸ.32፥15-33፥23 | ሉቃ.20፥1-26 | ሉቃ.22፥47-71 |
| ረ | ዘጸ.34 | ሉቃ.20፥27-47 | ሉቃ.23፥1-12 |
| ሐ | ዘጸ.35 | ሉቃ.21፥1-19 | ሉቃ.23፥13-31 |
| ዓ | ዘጸ.36፥1-40፥16 | ሉቃ.21፥20-38 | ሉቃ.23፥32-43 |
| ቅ | ዘጸ.40፥17-38 | ሉቃ.22፥1-23 | ሉቃ.23፥44-56 |

| | ሳምንት 28 | ሳምንት 29 | ሳምንት 30 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.27(28) | መዝ.28(29) | መዝ.29(30) |
| ሰ | ሉቃ.24፥1-12 | መክ.3፥1-4፥3 | መክ.9 |
| ማ | ሉቃ.24፥13-35 | መክ.4፥4-16 | መክ.10 |
| ረ | ሉቃ.24፥36-53 | መክ.5 | መክ.11 |
| ሐ | መክ.1፥1-11 | መክ.6 | መክ.12 |
| ዓ | መክ.1፥12-2፥11 | መክ.7 | ሐ.ሥ.1፥1-12 |
| ቅ | መክ.2፥12-26 | መክ.8 | ሐ.ሥ.1፥13-26 |

| | ሳምንት 31 | ሳምንት 32 | ሳምንት 33 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.30(31) | መዝ.31(32) | መዝ.32(33) |
| ሰ | ሐ.ሥ.2፥1-13 | ሐ.ሥ.4፥13-31 | ሐ.ሥ.8፥1-25 |
| ማ | ሐ.ሥ.2፥14-36 | ሐ.ሥ.4፥32-5፥11 | ሐ.ሥ.8፥26-40 |
| ረ | ሐ.ሥ.2፥37-47 | ሐ.ሥ.5፥12-42 | ሐ.ሥ.9፥1-19 |
| ሐ | ሐ.ሥ.3፥1-10 | ሐ.ሥ.6፥1-15 | ሐ.ሥ.9፥20-31 |
| ዓ | ሐ.ሥ.3፥11-26 | ሐ.ሥ.7፥1-29 | ሐ.ሥ.9፥32-43 |
| ቅ | ሐ.ሥ.4፥1-12 | ሐ.ሥ.7፥30-60 | ሐ.ሥ.10፥1-33 |

| | ሳምንት 34 | ሳምንት 35 | ሳምንት 36 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.33(34) | መዝ.34(35) | መዝ.35(36) |
| ሰ | ሐ.ሥ.10፥34-48 | ሐ.ሥ.13፥14-41 | ገላ.2፥1-10 |
| ማ | ሐ.ሥ.11፥1-18 | ሐ.ሥ.13፥42-14፥7 | ገላ.2፥11-20 |
| ረ | ሐ.ሥ.11፥19-30 | ሐ.ሥ.14፥8-28 | ገላ.2፥21-3፥9 |
| ሐ | ሐ.ሥ.12፥1-17 | ሐ.ሥ.15፥1-21 | ገላ.3፥10-14 |
| ዓ | ሐ.ሥ.12፥18-25 | ገላ.1፥1-10 | ገላ.3፥15-18 |
| ቅ | ሐ.ሥ.13፥1-13 | ገላ.1፥11-24 | ገላ.3፥19-29 |

| | ሳምንት 37 | ሳምንት 38 | ሳምንት 39 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.36(37) | መዝ.37(38) | መዝ.38(39) |
| ሰ | ገላ.4፥1-11 | ገላ.6፥11-18 | ዘኁ.9፥15-10፥36 |
| ማ | ገላ.4፥12-20 | ዘኁ.1 እና 2 | ዘኁ.11 |
| ረ | ገላ.4፥21-5፥1 | ዘኁ. 3 እና 4 | ዘኁ.12 |
| ሐ | ገላ.5፥2-12 | ዘኁ.5፥1-6፥21 | ዘኁ.13 |
| አ | ገላ.5፥13-26 | ዘኁ.6፥22-7፥89 | ዘኁ.14 |
| ቅ | ገላ.6፥1-10 | ዘኁ.8፥1-9፥14 | ዘኁ.15 |

| | ሳምንት 40 | ሳምንት 41 | ሳምንት 42 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.39(40) | መዝ.40(41) | መዝ.41(42) |
| ሰ | ዘኁ.16 | ዘኁ.23 | ዘኁ.30፥1-31፥24 |
| ማ | ዘኁ.17፥1-18፥7 | ዘኁ.24 | ዘኁ.31፥25-32፥42 |
| ረ | ዘኁ.18፥8፥19፥22 | ዘኁ.25 | ዘኁ.33 እና 34 |
| ሐ | ዘኁ.20 | ዘኁ.26 | ዘኁ.35 እና 36 |
| አ | ዘኁ.21 | ዘኁ.27 | ሐ.ሥ.15፥22-35 |
| ቅ | ዘኁ.22 | ዘኁ.28 እና 29 | ሐ.ሥ.15፥36-16፥10 |


| | ሳምንት 43 | ሳምንት 44 | ሳምንት 45 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.42(43) | መዝ.43(44) | መዝ.44(45) |
| ሰ | ሐ.ሥ.16፥11-24 | 1 ተሰ.1 | 2 ተሰ.1 |
| ማ | ሐ.ሥ.16፥25-40 | 1 ተሰ.2፥1-16 | 2 ተሰ.2፥1-12 |
| ረ | ሐ.ሥ.17፥1-15 | 1 ተሰ.2፥17-3፥13 | 2 ተሰ.2፥13-3፥5 |
| ሐ | ሐ.ሥ.17፥16-34 | 1 ተሰ.4፥1-12 | 2 ተሰ.3፥6-17 |
| አ | ሐ.ሥ.18፥1-11 | 1 ተሰ.4፥13-5፥11 | ሐ.ሥ.19፥1-10 |
| ቅ | ሐ.ሥ.18፥12-28 | 1 ተሰ.5፥12-28 | ሐ.ሥ.19፥11-22 |

| | ሳምንት 46 | ሳምንት 47 | ሳምንት 48 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.45(46) | መዝ.46(47) | መዝ.47(48) |
| ሰ | ሐ.ሥ.19፥23-41 | ሐ.ሥ.22፥30-23፥11 | ሐ.ሥ.28፥1-16 |
| ማ | ሐ.ሥ.20፥1-16 | ሐ.ሥ.23፥12-35 | ሐ.ሥ.28፥17-31 |
| ረ | ሐ.ሥ.20፥17-38 | ሐ.ሥ.24 | ኢያሱ 1 |
| ሐ | ሐ.ሥ.21፥1-16 | ሐ.ሥ.25 | ኢያሱ 2 |
| አ | ሐ.ሥ.21፥17-39 | ሐ.ሥ.26 | ኢያሱ 3 |
| ቅ | ሐ.ሥ.21፥40-22፥29 | ሐ.ሥ.27 | ኢያሱ 4 |

| | ሳምንት 49 | ሳምንት 50 | ሳምንት 51 |
|---|---|---|---|
| እ | መዝ.48(49) | መዝ.49(50) | መዝ.50(51) |
| ሰ | ኢያሱ 5 | ኢያሱ 11 እና 12 | ኢያሱ 23 |
| ማ | ኢያሱ 6 | ኢያሱ 13 | ኢያሱ 24 |
| ረ | ኢያሱ 7 | ኢያሱ 14 እና 15 | 1ጴጥ.1፥1-5 |
| ሐ | ኢያሱ 8 | ኢያሱ 16-19 | 1ጴጥ.1፥6-12 |
| አ | ኢያሱ 9 | ኢያሱ 20 እና 21 | 1ጴጥ.1፥13-25 |
| ቅ | ኢያሱ 10 | ኢያሱ 22 | 1ጴጥ.2፥1-10 |

| | ሳምንት 52 |
|---|---|
| እ | መዝ.51(52) |
| ሰ | 1ጴጥ.2፥11-17 |
| ማ | 1ጴጥ.2፥18-25 |
| ረ | 1ጴጥ.3፥1-12 |
| ሐ | 1ጴጥ.3፥13-4፥6 |
| አ | 1ጴጥ.4፥7-19 |
| ቅ | 1ጴጥ.5 |

ማስታወሻ፦ ለ2ኛ፣ ለ3ኛና ለ4ኛ ዓመታት ማውጫዎች ይዘጋጃሉ። እንዲሁም የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ለ[illegible] ከእግዚአብሔር ጋር [illegible] ማስታወሻዎች የሚገኙበትን መጽሐፍ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል።



«የሰው ልጅ ሆይ ... ይህን መጽሐፍ ብላ፥ ... እኔም በላሁት፥ በአፌም ውስጥ እንደ ማር ጣፈጠ።» ሕዝ. 3፥1-3

የእግዚአብሔር ቃል ተጣጥሞ በተበላ ቍጥር እንደ ማር ይጣፍጣል። ቃሉ ሕይወትን የሚያድሰው፥ «የሕይወት ራስ» ወደ ሆነው ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አመልካች በመሆኑ ነው።

ታላቁ ቃል በቅን ልቦናና በትጋት ሲታይ፥ ምን ያህል በረከት እንደሚገኝበት ለመጠቆም፥ እነሆ፥ ይህ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቀርቧል።

ዋጋው ብር 5.00

MKT GEBIYA

አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት
ARTISTIC PRINTERS